የሚጠይቅ ተግባር ነው። የተቻለንን ያህል ትልቅ ትምህርት ቤት በመገንባት ብዙ ሰዎችን (አብያተ ክርስቲያናትን የመምራት ብቃት ባይኖራቸውም እንኳን) እናስመርቃለን።

5) ለሁሉም ሰው አንድ ዓይነት ሥልጠና እንሰጣለን። በክፍላችን ውስጥ ለሁሉም ሰው እኩል መረጃ እንሰጣለን። አንዳንዶች ያንን መረጃ ሊፈልጉ ቢችሉም፣ አንዳንዶቹ መረጃውን አይጠቀሙም። መምህሩ የበሰጠ እምቅ ችሎታ ወይም መንፈሳዊ ግንዛቤ ያላቸውን ሰዎች በመምረጥ የግል የሆነ ትኩረትና ሥልጠና ሊሰጣቸው አይችልም። «ሁሉንም በእኩል ዓይን መመልከት አለብን» እንላለን። ይህ ግን ልዩ ስጦታ ያላቸውን ሰዎች ለማሳደግ እያስቸለንም።

ሰዎችን እንደ ዓለም ዘዴ ማሠልጠኑ ምንኛ ቀላል ነው? ጳውሎስ «እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ» (1ኛ ቆሮ. 11:1) ቢላቸውም፣ እኛ ግን ከሥራችን ያሉት ሰዎች ወደ እኛ እንዲቀርቡና ምን እንደምንመስል እንዲያውቁ አንፈልግም። ስጦታ ያላቸው ሰዎች ከአጠገባችን እንዲደርሱ አንፈልግም። ምክንያቱም እነርሱ ማገልገል ከጀመሩ፣ ምእመናን እኛን አይሰሙንም ብለን እናስባለን። ነገር ግን ፍላጎታችን ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ እንደምትፈልገው እንድታድግ ቢሆን፣ እግዚአብሔር ብዙ ስጦታ ያላቸውን ሰዎች በሚያመጣበት ጊዜ የበለጠ ደስተኞች እንሆን ነበር። የዓለምን የትምህርት ዘዴ ስለ ለመድን፣ ሰው ሊማር የሚችለው በትምህርት ቤት ብቻ ነው ብለን እናስባለን። መደበኛውን የትምህርት መመዘኛ ያሟሉትን ሰዎች ነው የምንፈልገው። ወጣትና ያልተሞከሩ መሪዎችን በመቅጠር ወዲያውኑ በመሪነት አገልግሎት ላይ እናስቀምጣለን። በመንፈሳዊ ባሕርይ ወይም በብስለት ላይ እምብዛም አናተኩርም። ቀስ በቀስ አነስተኛ ኃላፊነት እየሰጠንና በታማኝነታቸው መጠን እያሳደግን አንሄድም።

14ኛ ጥያቄ፡- ከኢየሱስ ሕይወትና ትምህርቶች ስለ አመራር የምንመለከታቸውን ዐበይት ነገሮች ከልስ። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የኢየሱስን የአመራር ምሳሌነት ቢከተሉ አመራር (መሪዎችም ሆኑ መዋቅሮች) እንዴት እንደሚቀየሩ ከልስ።



ኢየሱስ ምሳሌያችን ከሆነ፣ አብያተ ክርስቲያኖቻችን በአመራር ረገድ እርሱን ለመምሰል አልቻሉም ማለት ነው። ስለ መሪነት ባለን ግንዛቤ ላይ የዓለምና የባህላችን አመለካከት ከፍተኛ ጫና ይፈጥርብናል። እግዚአብሔር ይቅር ይበለን! ዛሬ ለቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጓት እንደ ዓለም ዓይነት ብዙ መሪዎች አይደሉም። የሚያስፈልጉን ታላቅነታችን በትሕትና ከምናበረክተው አገልግሎት ይመነጫል የሚል እምነት ያላቸው መሪዎች ናቸው። ቤተ ክርስቲያን ኢየሱስ ከሞተ በኋላ በሐዋርያቱ አማካኝነት እንዳደረገችው፣ በዓለም ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ልታመጣ የምትችለው በዚህ ጊዜ ብቻ ነው።

## ሁለተኛ ቀን

15ኛ ጥያቄ፡- መንፈስ ቅዱስ በሁሉም አማኞች ላይ ከመጣ በኋላ በብሉይ ኪዳን ዘመን ከነበሩት አይሁዶች በተለየ የአዲስ ኪዳን አማኞች ያገኟቸውን የተለዩ ነገሮች ዘርዝር።

ኢየሱስ ከሞት ተነሥቶ ወደ ሰማይ ካረገና በአማኞች ውስጥ ይኖር ዘንድ መንፈስ ቅዱስን ከላከ እነሆ 2000 ዓመታት ሊሆኑ ተቃርበዋል። ይህ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ውስጥ የማደሩ ጉዳይ ካመንንበት ጊዜ ጀምሮ ስንሰማው የኖርነው በመሆኑ፣ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ከአማኞች ጋር ባለው ግንኙነት ላይ የሚያመጣቸውን ታላላቅ ነገሮች ሳናስብ እንቀራለን። አሁን የእግዚአብሔር ሕዝብ በአንድ መልክዓ ምድራዊ አካባቢ የሚኖሩ «አካላዊ ሰዎች» ሳይሆኑ፣ የኢየሱስ ተከታዮች የሆኑትን ወገኖች ሁሉ የሚያካትቱ «መንፈሳዊ ሰዎች» ናቸው። እግዚአብሔር ከእንግዲህ በአንድ የአይሁድ ጎሳ ላይ ማተኮሩ ቀርቶ፣ ሰዎችን ሁሉ ወደ ራሱ ይስባል። መንፈስ ቅዱስንም ቢሆን የሚሰጠው ሕዝቡን እንዲመሩ ለሚፈልጋቸው የተወሰኑ ሰዎች ብቻ ሳይሆን፣ ለሁሉም እውነተኛ የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች ነው። ሁሉን ቻይ የሆነው እምላክ በእያንዳንዱ አማኝ ልብ ውስጥ የማደሩ እውነታ የእግዚአብሔር ሕዝብ በሚመራበትና በሚተዳደርበት ሁኔታ ላይ ከፍተኛ ልዩነት ይፈጥራል።

## የቤተ ክርስቲያን አመራርና አስተዳደር መዋቅሮች ከእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪክ (ክፍል 4 - የቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን)

1. በአዲስ ኪዳን ዘመን የነበሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች:-

> 16ኛ ጥያቄ:- ዮሐ. 14:26፤ 16:13-15ን አንብብ:: እያንዳንዱ አማኝ የሚያስተምረውና የሚመራው መንፈስ ቅዱስ አለው:: ይህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን አመራር መለወጥ ያለበት እንዴት ነው?

በመንፈስ ቅዱስ ምሪትና በኢየሱስ ራስነት የቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በነበሩት 30 ዓመታት ውስጥ ማኅበረሰቧን በከፍተኛ ደረጃ በመለወጥ ከኢየሩሳሌም በሺ. ዎች የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮች ርቀው ለነበሩት ሰዎች ወንጌሉን አድርሰዋል:: ይህን ለማድረግ የቻሉት እንዴት ነበር? ይህ የሆነው ሐዋርያት ከኢየሩሳሌም ሆነው ሁሉንም ሥራ የሚያስተዳድሩበት ከፍተኛ መዋቅር በመዘርጋታቸው ነበር? አልነበረም:: ነገር ግን ውጤቱ ሊገኝ የቻለው የቤተ ክርስቲያን መሪዎቹ መንፈስ ቅዱስ እያንዳንዱን አማኝ እንደሚመራና በውስጡ እንደሚሠራ በማመናቸው ምክንያት ነበር:: ሁሉም ምእመን እንዲያገለግል ያበ ረታቱ ነበር:: ሁሉም ምእመን በሄደበት ሁሉ ስለ ክርስቶስ በግልጽ ይመሰክር ነበር:: እያንዳንዷ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ በራሷ መንገድ የማገልገል ነጻነት ነበራት:: ለዚህ ነበር ፊልጶስ በኢየሩሳሌም ከነበሩት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ፈቃድ ሳይጠይቅ በሰማርያና ለኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ለማገልገል የቻ ለው:: ጳውሎስ በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ቢመሠርትም፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት ከማንም ፈቃድ ሳይጠይቁ በሄዱበት ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ተከላ ተግባር ያከናውኑ ነበር:: እነዚህ አማኞች ጳውሎስ ወዳልሄደባቸው እንደ ቈላስይስ ያሉ አገሮች ወንጌሉን አዳ ረሱ (ቈላ. 1:3-8፣ 2:1):: ጳውሎስ በኤፌሶን በቆየባቸው ሁለት ዓመታት ውስጥ በእስያ አውራጃ (ከአዲስ አበባ እስከ ዲላ የሚያክል) የሚገኙ ሰዎች ሁሉ ወንጌል እንደ ሰሙ ተመልክቷል:: በእነዚህ አካባቢዎች አብያተ ክርስቲያናትም ተመሥርተዋል (የሐዋ. 19:10):: ይህንን እውነት በደርግ ዘመን ተመልክተናል::



ማዕከላዊ ቁጥጥር ማድረግ በሚያዳግትበት በዚህ ዘመን አማኞች እምነታቸውን ለሌሎች በማካፈላቸው በብዙ ስፍራዎች አብያተ ክርስቲያናት ተመሥርተዋል::

በአሁኑ ሰዓት ግን ሽማግሌዎች የምእመናንን ተግባራት ለመቆጣጠር ይፈልጋሉ:: ይህ ደግሞ ጥንቃቄ ካልታከለበት፣ ምእመናን መንፈስ ቅዱስንና ጌታችን ኢየሱስን ከማዳመጥ ይልቅ ማዕከላዊ ቁጥጥር የሚያደርገውን ቤተ እምነታቸውን እንዲያዳምጡ የሚያደርግ ነው:: እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ያደናቅፋል:: ምእመናን እግዚአብሔር እንድናደርግ ይፈልጋል ብለው የሚያምኑትን ተግባር የማከናወን ነጻነት በማሳጣት ቤተ ክርስቲያኒቱን ይጎዳታል:: በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደ ታየው፣ ቤተ ክርስቲያን ማዕከላዊነትን ስታጠብቅና ከአገልግሎቱ ርቀው ባሉት ጥቂት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቁጥጥር ሥር ስትወድቅ፣ ትዳከማለች:: ብዙውን ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር ጠንካራ ግንኙነት ከመፍጠር ይልቅ፣ የራሷን ቤተ እምነታዊ ትምህርቶች ለመጠበቅ ደፋ ቀና በምትልበት ጊዜ፣ አዳዲስ ቤተ እምነቶች ይጀመራሉ::

> 17ኛ ጥያቄ:- ኤፌ. 4:11-16ን አንብብ:: ሀ) በዚህ ስፍራ የተጠቀሱትን የተ ለያዩ መሪዎች ዘርዝር:: ለ) እነዚህ እያንዳንዳቸው ዓይነት መሪዎች ምን ተግባአገለገላቸው::ር የሚያከናውኑ ይመስልሃል? ሐ) 1ኛ ቆሮ. 12:27-28ን አንብብ:: በዚህ ስፍራ የተጠቀሱትን ሌሎች የመሪነት ስጦታ ዎች ዘርዝር::

በአዲስ ኪዳን አብያተ ክርስቲያናት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ ልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነበሩ:: አንዱ መሪ ሁሉንም ዓይነት አገልግሎት ከሚያከናውን ወይም ከሚቆጣጠር ይልቅ፣ በቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ለሁሉም ክፍት ነበር:: ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ የፈለገውን ሰው እንዲመርጥ፣ እንዲጠራ፣ ኃይልን እንዲሰጥና እንዲጠቀም ትፈቅድ ነበር:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሱት ዋና ዋና መሪዎች የሚከተሉት ናቸው::

ሀ. ሐዋርያት፦ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተገለጸው እጅግ አስፈላጊ «መንፈሳዊ ስጦታ» ሐዋርያነት ነው (1ኛ ቆሮ. 12:28)። ዛሬ ይህ ስጦታ ምን እንደ ሆነ በአግባቡ ያልተረዱና በቤተ ክርስቲያን ላይ ልዩ ሥልጣን ያለን ሐዋርያት ነን የሚሉ አብያተ ክርስቲያናት ስላሉ፣ አዲስ ኪዳን ይህንን የመሪነት ስፍራ እንዴት እንደሚገልጽ መመርመር ጠቃሚ ይሆናል።

በአዲስ ኪዳን፣ ሐዋርያ የሚለው ቃል «በሌላ ሰው ሥልጣን የተላከ» ማለት ነው። ይህ ቃል የተለያዩ ትርጉሞች ይኖሩታል።

በመጀመሪያ፣ ይህ የሌሎች መልእክተኛ ሆኖ የሚሠራውን ማንኛውም ሰው ሊያመለክት ይችላል። በግሪክ አዲስ ኪዳን ውስጥ ቲቶ እና አፍሮዲጡ ሐዋርያት ወይም የተላኩ ተብለው ተጠርተ ዋል (2ኛ ቆሮ. 8:23፤ ፊልጵ. 2:25)። ጳውሎስ ቲቶን ወደ ቆሮንቶስ ልኮት ነበር፤ የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ አፍሮዲጡ ጳውሎስን እንዲረዳው ልካው ነበር።

ሁለተኛ፣ ወንጌሉን ወደ አዳዲስ አካባቢዎች በማዳረስ ቤተ ክርስቲያን የመሠረቱትን ልዩ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ያመለክታል። በቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን በዚህ መልኩ ያገለገሉ ምን ያህል ሐዋርያት እንደ ነበሩ በትክክል አይታወቅም። ነገር ግን እንድሮኒቆን እና ዮልያን የሚባሉ ሁለት ሐዋርያት ከጳውሎስ በፊት እንደ ነበሩ ተመልክቷል (ሮሜ 16:7)። አዲስ ኪዳን ከልዩ ሐዋርያት መካከል እነዚህን ሰዎች አለማካተቱ ከ12ቱ ሐዋርያት የተለዩና ዳሩ ግን ጠቃሚ አገልግሎት ያበረከቱ ሌሎች ሐዋርያትም እንደ ነበሩ ያመለክታል።

ሦስተኛ፣ በአመዛኙ፣ ይህ ቃል ኢየሱስ ያሠለጠናቸውንና በምድር ላይ ወኪሉ እንዲሆኑ የላካቸውን 12 ደቀ መዛሙርት ያመለክታል። ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ፣ ብዙ ተከታዮች ነበሩት። ከእነዚህ ተከታዮቹ መካከል 12ቱን መርጦ አሠለጠናቸው። እነዚህ 12ቱ ብዙውን ጊዜ 12ቱ ደቀ መዛሙርት በመባል የሚታወቁ ሲሆን፣ ኢየሱስ ሐዋርያቱ መሆናቸውን ተናግሯል (ሉቃስ 6:13-16)። ለምን 12? የብሉይ



ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑት እያሁዶች 12 ነገዶች እንደ ነበሯቸው ሁሉ፣ አዲስ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆነችው ቤተ ክርስቲያንም 12 መሪዎች አሏት። የእነዚህ 12 ሐዋርያት ተግባር ምን ነበር? ማርቆስ 3:13-15 እንደሚነግረን፣ «ከእርሱም ጋር እንዲኖሩና ስመስበክ እንዲልካቸው፣ ድውዮችንም ሊፈውሱ፣ አጋንንትንም ሊያወጡ ሥልጣን ይሆንላቸው ዘንድ አሥራ ሁለት አደረገ።» እነዚህ 12ቱ ከአገልግሎቱ መጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድ ረስ ከኢየሱስ ጋር የነበሩ ልዩ የመሪዎች ቡድን ነበሩ (የሐዋ. 1:21-22)። ኢየሱስን ወክለው እንዴት እንደሚያገለግሉ ተምረዋል። ኢየሱስ ያደረጋቸውን ነገሮች ሁሉ በምድር ላይ እንዲያከናውኑ ተ ልከው ነበር። እነዚህ 12ቱ በኢየሱስ ፈንታ ወንጌሉን ሰብከዋል። የኢየሱስን ኃይል በመጠቀም (አንድን ነገር «በኢየሱስ ስም» ማድ ረግ ማለት ይህ ነው) ወንጌሉ ስመፈወስና በአጋንንት ላይ መንፈሳዊ ሥልጣን ስማሳየት የሚችል መሆኑን አረጋግጠዋል።

ከኢየሱስ ትንሣኤና ዕርገት በኋላ፣ የቀሩት 11 ደቀ መዛሙርት በመንፈስ ቅዱስ ምሪት በአስቆሮቱ ይሁዳ ቦታ ሌላ ደቀ መዝሙር መረጡ። ስመመረጥ ከሚያስፈልጉት መስፈርቶች እንዱ ኢየሱስ ከተጠመቀበት ጊዜ እንሥቶ ወደ ሰማይ እስካረገበት ጊዜ ድረስ አብሮት መሆን ነበር። (የሐዋ. 1:21-22ን እንብብ።) ጳውሎስ ኢየሱስን ስላየና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ልዩ ሥልጣን ስለ ነበ ረው፥ ከዚህ ልዩ የሐዋርያት ቡድን ውስጥ እንደሚገባ ተናግሯል። የእነዚህን ዓይነት ሥልጣን ያላቸው ሐዋርያት ከዚያ በኋላ የሚደገሙ አይደሉም። እነዚህ ልዩ ኃይል የተሰጣቸው ብቻ ሳይሆኑ፣ የቤተ ክርስቲያን መሠረት መሆናቸውም ተመልክቷል (ኤፌ. 2:20፤ ራእይ 21:14)። የአዲስ ኪዳን የአማኞችን አካል መሠረት ስመምራት አገልግለዋል። የአዲስ ኪዳን ትምህርት ምን እንደ ሆነም አብራርተዋል። ይህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ልዩ ቡድን በጣም አስፈላጊ በመሆኑ፣ ዮሐንስ ስለ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ባየው ራእዩ 12ቱ ሐዋርያት የከተማይቱ 12 ዐበይት የመሠረት ድንጋዮች እንደሚሆኑ ተመልክቷል።

ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሐዋርያት አሉ? ሐዋርያ የሚለው ቃል በሦስት የተለያዩ መንገዶች አገልግሎት ሊሰጥ እንደሚችል ታስታውሳለህ። «ሐዋርያት» የሚል የአመራር ቦታ ካለ፣ ሊያገለግል የሚችለው ከላይ በተመለከቱት ሁለት መንገዶች ብቻ ነው። አንደኛ፣ ይህ ቃል አንዲት ቤተ ክርስቲያን ወክላ የምትልካቸውን መልእክተኞች ሊያመለክት ይችላል። እንዲያውም፣ ሁላችንም ታላቁን ተልዕኮ ስለ ተቀበልን (ማቴ. 28:19-20)፣ አማኞች ሁሉ በዚህ መልኩ «ሐዋርያት» ናቸው። ሁሉም ወንጌሉን እንዲያካፍሉና በዓለም ውስጥ በእርሱ ፈንታ እንዲያገለግሉ ኢየሱስ ክርስቶስ የወከላቸው ናቸው።

ሁለተኛ፣ በሁለተኛው ተራ ቁጥር የተመለከቱትን ዓይነት መሪ ዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህ እግዚአብሔ ር በአዳዲስ ቦታዎች ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት የሚጠቀምባቸው ናቸው። ብዙውን ጊዜ እነዚህን «ቤተ ክርስቲያን ተካዮች» ብለን እንጠራቸዋለን። እነዚህ እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን ተከላ ስጦታ የሰጣቸው ናቸው። የቤተ ክርስቲያን ተካዮች ወደ አዳዲስ ባህሎች በመሄድ፣ አዳዲስ ቋንቋ ዎችን በመማር የምስክርነት አገልግሎት ሰጥተው አማኞችን የሚያፈሩና ቤተ ክርስቲያን የሚመሠርቱ ናቸው። ቤተ ክርስቲያኒቱ የራሷን ሽማግሌዎች ከሾመች በኋላ፣ ቤተ ክርስቲያን ተካዮች ወደ ሌሎች ቦታዎች በመሄድ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትን ይመሠርታሉ።

ይሁን እንጂ፣ አዲስ ኪዳን ኢየሱስ የጠራቸውንና የላካቸውን 12 ሐዋርያት ሥልጣን የሚተኩ ሐዋርያት መኖራቸውን አያመለክትም። የቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን የመጨረሻው ሐዋርያ (ሐዋርያው ዮሐንስ) ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ፣ ይህ የሐዋርያነት አገልግሎት እንዳበቃ አስተምራለች። የጴጥሮስ ወይም የሌላ ሐዋርያ ሥልጣን ለካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ወይም ለኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ መተላለፉን የሚያሳይ መ ረጃ የለም። ዛሬ ሐዋርያት ነን የሚሉ ሰዎች ሐዋርያነታቸው ልክ እንደ 12ቱ ሐዋርያት እንደ ሆነ የሚያስቡ ከሆነ፣ ተሳስተዋል



ማለት ነው። ምክንያቱም በሐዋርያት ሥራ 1:21-22 የተጠቀሰውን የሐዋርያነት መስፈርት ሊያሟሉ አይችሉም። አንድ ሰው ከ12ቱ ሐዋርያት መካከል አንዱ ለመሆን ኢየሱስ በመጥምቁ ዮሐንስ ከተ ጠመቀበት ጊዜ አንሥቶ ወደ ሰማይ እስካረገበት ጊዜ ድረስ አብሮት ሊሆን ይገባል። ከሞት የተነሣውን ጌታም ማየት ይጠበቅበታል።

18ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የሆነ ሰው «ሐዋርያ» ነኝ ሲል ሰምተህ ታውቃለህ? ሰምተህ ከሆነ፣ ከሐዋርያ ሦስት ትርጉሞች የትኛውን ማለቱ ነበር? ለ) ሁለተኛውን የሐዋርያነት ትርጉም ምሳሌዎች ከኢትዮጵያ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ስጥ።

19ኛ ጥያቄ፡- ሀ) «ነቢይ» ነኝ የሚል ክርስቲያን ገጥሞህ ያውቃል? ይህ ሰው ብሉይ ኪዳን ወይም አዲስ ኪዳን በሚያስተምረው የነቢይነት መስፈርት መሠረት ነቢይ ይመስልሃል? ሐ) ክርስቲያኖች የትንቢት ቃል ሲናገሩ ሰምተህ ታወቃለህ? ትንቢቱ ምን ነበር? እንደተተነበየው ተ ፈጸመ? እውነት መሆኑን ቤተ ክርስቲያን የገመገመችው እንዴት ነው? (1ኛ ተሰ. 5:20-22፤ 1ኛ ቆሮ. 14:29ን አንብብ።)

ለ. ነቢያት፡-

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሁለተኛው ከፍተኛ የአመራር ስፍራ «ነቢይነት» ነበር። የ«ነቢይነት» አመራርና መንፈሳዊ ስጦታ በዛሬው ዘመን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከፍተኛ ክርክር የፈጠ ረ ጉዳይ ነው። ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ነቢይነት በብሉይም ሆነ አዲስ ኪዳን አስፈላጊ ስጦታ መሆኑን ቢቀበሉም፣ ዛሬ ምን ያህል ተዛማጅነት አለው? በሚለው አሳብ ላይ የተለያየ አቋም አላቸው። በዚህ ጉዳይ ላይ ያሉትን የተለያዩ አቋሞች መተንተኑ ከዚህ መጽሐፍ የእይታ አድማስ ውጭ ነው።

አመለካከታቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ለመመሥረት የሚፈልጉ ወገኖች ማስወገድ ያለባቸው ሦስት አክራሪ አቋሞች አሉ።

በመጀመሪያ፣ ዛሬ የትንቢትን ቃል በጽሑፍ ከሰፈረው የእግዚአብሔር ቃል እኩል መመልከት የለብንም። ክርስቲያኖች 66ቱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ተጽፈው እንዳለቁ፣ እነዚህም

ሙሉ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆኑና ምንም እንከን እንደሌ ለባቸው ያምናሉ:: ስለሆነም፣ ዛሬ ለአማኞች የሚሰጥ ማንኛውም ልዩ ቃል ከተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ጋር በእኩልነት ሊታይ አይገባውም:: ይልቁንም፣ በተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል መገምገም አለበት ብለው ያምናሉ::

ሁለተኛ፣ ሁልጊዜም ሕይወታችንን ለመምራት ከእግዚአብሔር ልዩ የትንቢት ቃል መፈለግ የለብንም:: በብሉይና አዲስ ኪዳን ውስጥም ነቢያት ለሰዎች ዕለታዊ መልእክቶችን ሲያስተላልፉ ወይም ማንን ማግባት እንዳለባቸውና ማንን ማግባት እንደሌ ለባቸው ሲናገሩ እንመለከትም:: እግዚአብሔር ነቢያትን የሚጠራውና የሚልከው ልዩና ከባድ መልእክት ለማስተላለፍ በሚፈልግበት ጊዜ ነው:: ስለሆነም፣ ትኩረታችን እንከን የሌለውን የእግዚአብሔርን ቃል በጥንቃቄ በማጥናት ከሕይወታችን ጋር ማዛመድ ሊሆን ይገባል:: ዛሬም እግዚአብሔር ልዩ መልእክት ለማስተላለፍ ግለሰቦችን ይመርጣል:: ይህ ማንም የማይከለክለው መብቱ ነው:: ይህ ማለት ግን ሁልጊዜም ነቢይ ነኝ የሚል ሰው ልዩ መልእክት እንዲነግረን መጠበቅ አለብን ማለት አይደለም::

ሦስተኛ፣ ዛሬ እግዚአብሔር ነቢያትን ወይም የትንቢትን ቃል ወደ ሰዎች አይልክም የሚል ጠንካራ አቋም መያዝ የለብንም:: አዲስ ኪዳን ይህ ስጦታ እንዳበቃ በግልጽ አያሳይም::

ምንም እንኳን አዲስ ኪዳን ይህ የነቢይነት አመራር ከሐዋርያነት ቀጥሎ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደ ነበረው ቢያሳይም፣ ይህ የመሪነት አገልግሎት በተግባር የታየበት ሁኔታ እምብዛም አልተመለከተም:: (ኤፌ. 2:20፤ 4:11፤ 1ኛ ቆሮ. 12:28ን አንብብ::) እነዚህ እንደ ኤልያስ ወይም እንደ ኢሳይያስ ነበሩ? እንዴት ነበር የመሩት? ምን ዓይነት ሚና ነበራቸው? መጽሐፍ ቅዱስ ነቢያት በቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያገለገሉበትን ሁኔታ በግልጽ ስለማያብራራ፣ ዛሬ ነቢያትንና ነቢይነትን በተመለከተ የተለያዩ አመለካከቶች ሊፈጠሩ ችለዋል::



ይሁን እንጂ፣ አዲስ ኪዳንን በጥንቃቄ ማጥናት የሚከተሉትን ነጥቦች የሚያሳይ ይመስላል:-

1) አንድ የትንቢት ቃል (ለምሳሌ፣ ስምዖን፣ ሉቃስ 2:25-32) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የአመራር አገልግሎት ካለው ቋሚ ነቢይ የተለየ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል:: (ለምሳሌ፣ አጋቦስ፣ የሐዋ. 21:10):: ሁሉም አማኞች ከእግዚአብሔር ዘንድ የትንቢት ቃል ሊያገኙ ይችላሉ (ኢዩ. 2:28-29፤ 1ኛ ቆሮ. 14:29-31):: ነቢያት ተ ብለው የሚጠሩት ግን በጣም ጥቂት ክርስቲያኖች ብቻ ናቸው::

2) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትንቢት የሚለው ቃል የሚያመለክተው ወደፊት የሚከሰቱትን ነገሮች መተንበይን ብቻ አይደለም:: በብሉይና አዲስ ኪዳን ውስጥ ነቢያት ብዙውን ጊዜ ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን ቃል ለሕዝቡ የሚናገሩ ናቸው:: ከዚህ መልእክት ውስጥ አንዳንዱ ስለ ወደፊት የሚናገር ሊሆን ይችላል (ራእይ 6-22):: በይበልጥ ግን መልእክቱ ለሕዝቡ የሚሰጥ ትምህርት ወይም ማስጠንቀቂያ ነው (ራእይ 2-3):: ትንቢት የእግዚአብሔርን ቃል አጥንቶ ይህንኑ ለሰዎች በማብራራት የሚመጣ ነገር አይደለም:: ይህ የማስተማር ስጦታ ነው:: ትንቢት እግዚአብሔር ለአንድ ሰው ወይም ለሰዎች ስማስተላለፍ የሚፈልገውን መልእክት በሰው አእምሮ ውስጥ የሚያኖርበት መንገድ ነው:: ብዙውን ጊዜ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ የሚፈጠረው በችግር ወቅት ነው:: እግዚአብሔር ሕዝቡ ከእርሱ ስመራቅ ጣዖታትን በሚያመልክበት ጊዜ ነቢያትን ይልክላቸው ነበር:: ወይም ደግሞ ረሃብ ከመምጣቱ በፊት እግዚአብሔር ነቢይ በመላክ ሕዝቡን ያስጠነቅቅ ነበር (ለምሳሌ፣ የሐዋ. 11:27-30):: ዛሬ አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የትንቢት ስጦታ ከልሳን ጋር የተያያዘ አልነበረም፣ ወይም ነቢያት መልእክታቸውን ለመናገር በልሳን አልተጠቀሙም::

3) በብሉይ ኪዳን ውስጥ ነቢያት እንከን የሌለው የእግዚአብሔር ቃል ጽፈዋል (ከኢሳይያስ እስከ ሚልክያስ):: በአዲስ ኪዳን ግን ነቢያት ናቸው የተባሉ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል አልጻፉም:: ከአዲስ ኪዳን ነቢያት ማናቸውም «እኔ ነቢይ ስለሆንኩ

የእግዚአብሔርን ቃል እየጻፍኩላችሁ ነው» አላሉም። ከዚህ ይልቅ፣ ሥልጣናቸውን የሚመሠርቱት በሐዋርያነታቸው ላይ ነበር (ሮሜ 1:1፣ 1ኛ ጴጥ. 1:1)። ሐዋርያው ዮሐንስ የጻፍኩት መልእክት ትንቢት ነው ቢልም (ራእይ 1:3)፣ በቀጥታ ነቢይ ነኝ አላለም። ይህ አንዳንድ ምሑራን ሐዋርያት የብሉይ ኪዳንን የሚጽፉ ነቢያትን ሚና መያዛቸውን ያሳያል እንዲሉ አድርጓቸዋል።

4) የትንቢት ቃል የመናገር ችሎታ ለሁሉም አማኞች የተሰጠ ነው። መንፈስ ቅዱስ ወደ አማኞች በመምጣቱ ትንቢት የተናገሩባቸው ጊዜያት ነበሩ (የሐዋ. 19:6)። ምን እንደ ተናገሩ አልተገለጸም። ይህ የትንቢት ስጦታ ከቢያ ክስተት በኋላ ይቀጥል አይቀጥል የተገለጸ ነገር የለም። ይህ ምናልባት እግዚአብሔር በዘ ኍልቁ 11:25 ለሰባ ሰዎች አንድ ጊዜ (የማይደገም) በትንቢት የመናገር ስጦታ በመስጠት መንፈስ ቅዱስ እንደ ሞላባቸው ዓይነት ሊሆን ይችላል። በ1ኛ ቆሮንቶስ 14:1፣ 5፣ 26፣ 29-33 ጳውሎስ እያንዳንዱ አማኝ ለሌሎች የሚያካፍለውን የትንቢት ቃል ከእግዚአብሔር ዘንድ ሊቀበል እንደሚችል ተናግሯል።

5) ትንቢት ወይም ነቢይ የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሁለት ደረጃዎች ያሉት ትርጉም የያዘ ይመስላል። ብዙውን ጊዜ የሚያገለግለው ጠቅለል ባለ ትርጉም ነው። ለምሳሌ፣ ጳውሎስ የግሪክን አረማዊ ምሑር ነቢይ ብሎ ጠርቶታል (ቲቶ 1:12)። ትንቢት የሚለው ቃል እግዚአብሔር ቃሉን ወደ ልባቸውና አእምሯቸው ያስተላለፈላቸውን ሰዎች የሚያሳይ ነው። ሁሉም አማኞች በዘለቄታው ከእግዚአብሔር ስለ ወደፊት የሚናገሩ የትንቢት መልእክቶች መጠበቅ ባይኖርባቸውም፣ መንፈስ ቅዱስ ለሌሎች እንዲተላለፍ የሚፈልገውን መልእክት ሊሰጣቸው እንደሚችል ማሰብ አለባቸው። (ይህ በብሉይ ኪዳን ካህናት ከተ ወሰኑ ወገኖች ከሚመረጡበትና በአዲስ ኪዳን ግን ሁሉም አማኞች ካህናት ከሆኑበት ሁኔታ ጋር የሚመሳሰል ነው። በብሉይ ኪዳን የነቢይነት አገልግሎት የተሰጠው ለተወሰኑ ሰዎች ሲሆን፣ በአዲስ ኪዳን ግን ሁሉም አማኞች «ትንቢት የመናገር» ችሎታ አላቸው።)



ነገር ግን ከኤፌሶን 4:11፣ 1ኛ ተሰሎንቄ 5:20-21 እና 1ኛ ቆሮንቶስ 14:1፣ 5፣ 26፣ 29-33 እንደምንመለከተው፣ በብዙ አብያተ ክርስቲያናት እግዚአብሔርን የመስማትና መልእክቱን የመናገር ችሎታ ያላቸው ነቢያት የነበሩ ይመስላል። እነዚህ ነቢያት የቤተ ክርስቲያን አመራር አካል ነበሩ። እነዚህ ወገኖች በአንድ ሁኔታ ውስጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መርምረው በማወቃቸውና ለቤተ ክርስቲያን ምሪት በመስጠታቸው የሚታወቁ ነበሩ። ይህ ጥቂቶች ብቻ የያዙት ስጦታ ሳይሆን፣ ነገር ግን በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚገኝ ነበር። እንደ አጋቦስ ያሉ ጥቂት ሰዎች በስም ቢጠቀሱም፣ አብዛኞቹ በስማቸው ካለመጠቀሳቸውም በላይ፣ ምን ዓይነት ሚና ይጫወቱ እንደ ነበ ረም አልተገለጸም። ከ1ኛ ተሰሎንቄ 5:20-21 እንደምንመለከተው፣ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች እነዚህን ነቢያት ከመስማትና ከማክበር ይቆጠቡ ነበር። ጳውሎስ እግዚአብሔር በሰዎች በኩል እንደሚናገርና እነዚህን ነቢያት መስማት እንደሚገባ አስረድቷል። ይሁን እንጂ፣ የመልእክታቸውን ፍሬ ሐሳብ ማወቁም አስፈላጊ ነው።

የአዲስ ኪዳን ነቢያት ከተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ጋር እኩል ሥልጣን የነበራቸውን የብሉይ ኪዳን ነቢያት ያህል ሥልጣን እንደ ነበራቸው የሚያመለክት መረጃ የለም። ይህ አመለካከት በአያሌ ምክንያቶች ላይ የተገነባ ነው።

<u>አንደኛ</u>፣ የአዲስ ኪዳን ነቢያት እንደ ብሉይ ኪዳን ነቢያት ቀጥተኛ ማጣቀሻ የሚመስል ንግግር አልተጠቀሙም። «የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል . . . » ብለው አልተናገሩም።

<u>ሁለተኛ</u>፣ የነቢያቱ ቃላት እንደ ብሉይ ኪዳን ነቢያት ቃላት ሥልጣን ያለው ሆኖ የቀረበበት ሁኔታ የለም። የአዲስ ኪዳን ጸሐፊ ዎች የአዲስ ኪዳን ነቢያትን የእምነታቸው መሠረት አድርገው አልጠቀሷቸውም። የጠቀሱት ብሉይ ኪዳንን ብቻ ነበር።

<u>ሦስተኛ</u>፣ አማኞች የትንቢትን ቃል ቸል ሊሉና ከእግዚአብሔር ፍርድ ነፃ ሊሆኑ የሚችሉ ይመስላል። በብሉይ ኪዳን አንድ ነቢይ

በእግዚአብሔር ስም ተናገረ ማለት ልክ እግዚአብሔር እንደ ተናገረ ነበር:: የተነገረውን ነገር ሁሉም ሰው መስማትና መታዘዝ ነበረበት:: በሐዋርያት ሥራ 21:10-14 ግን አማኞች አጋቦስ ስለ ጳውሎስ የተናገረው ትንቢት እንዳይፈጸም ለማድረግ ሲሞክሩ ነበር:: ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ ወደ ኢየሩሳሌም እንድሄድ ነግሮኛል ቢልም፣ አማኞቹ እንዳይሄድ ለመከላከል ሞክረው ነበር::

አራተኛ፣ በሕይወቱ መጨረሻ አካባቢ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በሰጠው ምክር ከራሱ በተቀበላቸው ትምህርቶች ላይ ትኩረት እንዲያደርግ እንጂ፣ አዳዲስ ነቢያትን እንዲጠብቅ አላበረታታውም (2ኛ ጢሞ. 1:13-14፤ 2:2፤ 3:14-16):: ስለሆነም፣ ዛሬ ትኩረት ማድረግ ያለብን አዳዲስ የትንቢት ቃላት ለማግኘት ሳይሆን፣ በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር በተጻፉት ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ያሉትን እውነቶች በመታዘዝ ላይ መሆን አለበት::

ይህ ተገቢው የአዲስ ኪዳን ግንዛቤ ከሆነ፣ እግዚአብሔር እንደ ብሉይ ኪዳን ነቢያት ከተጻፈው ቃል ጋር እኩል ሥልጣን ያለው መልእክት የሚሰጡንን ልዩ መልእክቶች ይልክልናል ብለን መጠበቅ የለብንም:: እንከን የሌለው የእግዚአብሔር ቃል በብሉይ ኪዳን ነቢያትና በአዲስ ኪዳን ሐዋርያት ተጽፎ ተጠናቅቋል:: ስለዚህ፣ ዛሬ የትንቢት ቃል ያላቸው ሰዎች የብሉይ ኪዳን ነቢያትን ቃል ከርጀው «የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል . . . » ማለት የለባቸውም:: በእንዲህ ያለ ሥልጣን እንዲናገሩ ከፈቀድንላቸው፣ የተናገሩት ቃል ዝንፍ ቢል በድንጋይ መወገር እንዳለባቸው፣ ቢያንስ ደግሞ እንደ ሐሰተኛ ነቢያት ተቆጥረው ከቤተ ክርስቲያን መወገድ እንዳለባቸው መረዳት አለባቸው:: (ከአያሌ ዓመታት በፊት ነቢይ ነኝ የሚል አንድ ግለሰብ ለአንድ ወንጌላዊ «እግዚአብሔር በእኔ በኩል የተናገረውን ቃል ስላልሰማህ እግዚአብሔር ከዚህ ቀን በፊት ትሞታለህ ብሏል» ሲል ተነበየ:: ቀኑ ደረሰ:: ወንጌላዊው ግን አልሞተም:: ይህ እንግዲህ ግለሰቡ ሐሰተኛ ነቢይ መሆኑን የሚያሳይ ነው:: በኋላ ይህ ነቢይ ነኝ ባይ ገንዘብ ተሰጥቶት የሌላ ሃይማኖት ቡድን አባል ሆነ:: አሁን የዚያ ሃይማኖት ድርጅት መሪ ሆኖ እየሠራ ነው::) በብሉይ ኪዳን ዘመን ነገሮችን ለራሳቸው



ጥቅም የሚጠመዝዙ ሐሰተኛ ነቢያት ቁጥር ከእውነተኞቹ ነቢያት ይበዛ ነበር:: ዛሬም ይህ ሁኔታ ይቀጥላል:: የትንቢትን ቃል በምንናገርበት ጊዜ የአዲስ ኪዳንን ልምምድ በመከተል «መንፈስ ቅዱስ እንዲህ እያለን ይመስላል» ማለቱ የተሻለ ነው::

ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስ ሊሰጠን የሚፈልገውን የትንቢት ቃል እንዴት ማዳመጥ እንዳለባቸው መረዳት አለባቸው:: ጳውሎስ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አምልኮ መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ልብ ውስጥ ያስቀመጠውን መልእክት እንደሚያካትት ስለ ተናገረ፣ የዚህ ዓይነቱ ነገር በዛሬው ዘመን ቤተ ክርስቲያን አብቅቷል ለማለት የሚያስችል ምክንያት የለንም:: አብቅቷል የምንል ከሆነ፣ ምናልባት ሰዎች መንፈስ ቅዱስን እንዲሰሙ እያስተማርን አይደለንም ወይም እግዚአብሔር የሰጣቸውን መልእክት የሚያካፍሉበትን ዕድል አንሰጣቸውም ማለት ነው:: ይህ ግን በጥንቃቄ ሊከናወን የሚገባው ነገር ነው:: እያንዳንዱን የትንቢት ቃል በጥንቃቄ በመመርመር:- ሀ) ለክርስቶስ አካል ጠቃሚ መሆኑን፣ እና ለ) ከተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ጋር መስማማቱን ማረጋገጥ አለብን::

በአንድ ሁኔታ ውስጥ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ ተረድተው ለሕዝቡ የሚናገሩ የተወሰኑ ሰዎችስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ (በአጥቢያ፣ በክልልም ሆነ በብሔራዊ ደረጃ) ሊኖሩ ይችላሉ:: እነዚህ ሰዎች በአገራቸው ወይም በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ ተረድተው ይህንኑ ለቤተ ክርስቲያን የመናገር ልዩ ችሎታ አላቸው:: እነዚህ ሰዎች የመደበኛው አመራር አካላት ሊሆኑም ላይሆኑም ይችላሉ:: ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር በእነርሱ በኩል የሚያስተላልፍልን መልእክት ሊኖር ስለሚችል፣ ልንሰማቸው ይገባናል:: ይህንን በምናደርግበት ጊዜ ግን እንደ ሁልጊዜው መልእክታቸው ከእግዚአብሔር ቃል ጋር መጣጣሙን ማረጋገጥ ይኖርብናል (የሐዋ. 17:11 እግዚአብሔር ሰዎች በስሙ የሚናገሩት ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ የሚገመግሙትን ወገኖች እንደሚያከብር ያስተምራል::) (ማስታወሻ:- እነዚህ የትንቢት ስጦታ ያላቸው ሰዎች ብዙውን ጊዜ

መልእክታቸውን የሚናገሩት በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተመለከተውን የነቢያት ፈለግ ተከትለው አይደለም። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ስለ ዘመኑ ታላቅ መረዳት ስለ ሰጣቸው፣ አማኞች ለሚጠብቃቸው ነገር ዝግጁዎች ይሆኑ ዘንድ ያስጠነቅቁአቸዋል። ስለዚህ፣ ይህንን ስጦታ መፈለግ ያለብን የትንቢት ስጦታ እስን ከሚሉ ወገኖች ብቻ ሳይሆን፣ ስለ ዘመናችን ታላቅ መረዳት ካላቸው ጭምር መሆን አለበት።)

> 20ኛ ጥያቄ፡- የሐዋ. 21:8፤ 2ኛ ጢሞ. 4:5ን አንብብ። የወንጌላውያን አመራር ምን ምን ያካትታል ብለህ ታስባለህ? ይህ የመሪነት ስፍራ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

ሐ. ወንጌላውያን፡- በኤፌሶን 4:11 የተጠቀሰጡ ሦስተኛው አገልግሎት ወንጌላዊነት ነው። ይህ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በጣም የተለመደ አገልግሎት ነው። ብዙ አብያተ ክርስቲያናት «ወንጌላውያንን» ይቀጥራሉ። የእነዚህ ወንጌላውያን ተግባር ምእመናንን ከማገልገል እስከ ለማኅበረሰቡ አባላት ወንጌልን መስበክ ይደርሳል። እነዚህ «ውስጣዊ ወንጌላውያን» የሚባሉ ናቸው። አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ወንጌሉ እምብዛም ወዳልተ ሰበከባቸው ወይም ቤተ እምነታቸው ባልተስፋፋባቸው የኢትዮጵያ አካባቢዎች ወንጌላውያንን ይልካሉ። እነዚህም «የውጭ ወንጌላውያን» በመባል ይታወቃሉ። በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ይህ የወንጌላዊነት አገልግሎት ከፍተኛ ክብር ስለ ተሰጠው፣ ሰዎች «ወንጌላዊ እገሌ» ተብለው መጠራት ይፈልጋሉ።

ነገር ግን እንደ ነቢይነት አገልግሎት ሁሉ፣ አዲስ ኪዳን ስለ ወንጌላዊነትም ብዙ ማብራሪያ አይሰጥም። ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሦስት ጊዜያት ብቻ ነው የተጠቀሰው። ፊልጶስ ወንጌላዊ ተ ብሎ ተጠርቷል (የሐዋ. 21:8)። ጢሞቴዎስ የወንጌላዊነትን ሥራ እንዲሠራ ተነግሮታል (2ኛ ጢሞ. 4:5)። ጳውሎስም ወንጌላውያን ተብለው የሚጠሩ መሪዎች መኖራቸውን አመልክቶአል (ኤፌ. 4:11)። በአዲስ ኪዳን ውስጥ የወንጌላዊ ሥራ ምን እንደ ነበረ ስላልተገለጸ፣ ፍችውን ከራሱ ከቃሉ መፈለግ



አለብን። ወንጌላዊነትን የሚገልጸው የግሪክ ቃል የመጣው «መልካም ዜና መናገርን» ከሚያመለክት ቃል ነው። ሰዎች በማኅበ ረሰባቸው ውስጥ የሚፈጸሙትን መልካም ዜናዎች ለማመልከት ይህንን ቃል ይጠቀሙ ነበር። (ለምሳሌ፣ ለአንድ የተከበረ ቤተሰብ ልጅ ሲወለድ።) ለአማኞች ወንጌልን ኢየሱስ ሰዎችን ከኃጢአታቸውና ከእግዚአብሔር ቁጣ ለማዳን መሞቱን መናገርን የሚያሳይ ነው። ከቃሉ ትርጉም በመነሣት የአንድ ወንጌላዊ ሥራ ሰዎች በክርስቶስ እንዲያምኑ መናገር እንደ ሆነ እንረዳለን። ምናልባትም ፊልጶስ ወንጌላዊ የተባለው እንደ ሰማርያ ወዳሉት ወንጌል ወዳልተሰበከባቸው ቦታዎች ወንጌሉን ስላደረሰና ለኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የወንጌሉን ምንነት ስላብራራለት ሳይሆን አይቀርም (የሐዋ. 8)።

«የወንጌላዊነት» አገልግሎት እግዚአብሔር አንድ ሰው ለማያምኑ ወገኖች ወንጌሉን በመመስከር ወደ ክርስቶስ የሚመልስበትን ልዩ ስጦታ የሚያሳይ ይመስላል። ሁሉም አማኞች በትጋት ሳልዳኑ ሰዎች መመስከር ቢኖርባቸውም፣ ወንጌላዊነት ልዩ የመመስከር ስጦታ ያላቸውን ሰዎች የሚያመለክት ነው። የዚህ የጥናት መምሪያና ማብራሪያ ጸሐፊ በቀዳሚነት በአማኞች መካከል የማስተማርና የመስበክ አገልግሎት የሚያከናውነውን ሰው «ወንጌላዊ» ማለቱ ብዙ ግራ መጋባቶችን መፍጠር ነው የሚል እምነት አለው። ይህ የመጋቢነት/አስተማሪ ስጦታ ነው። የመጋቢ/አስተማሪን አገልግሎት ለወንጌላዊ በመስጠታችን የቤተ ክርስቲያንን እንደ ትልቅ ኃላፊነት ችል ብለናል። ይህም እግዚአብሔር የማያምኑትን ሰዎች እንደሚወዳቸውና በክርስቶስ በማመን ልጆቹ እንዲሆኑ የሚፈልግ መሆኑን ቤተ ክርስቲያን ለማኅበረሰቡ እንድታስተምር ነው።

> 21ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችሁ ወንጌላውያን አሏት? ከሆነ፣ አገልግሎታቸው ትኩረት የሚያደርገው ባልዳኑት ላይ ነው ወይስ በዳኑት? ለ) ቤተ ክርስቲያናችሁ ያልዳኑትን ሰዎች ወደ ክርስቶስ የመመለስ ኃላፊነት የተሰጠው ሰው ከሌላት ይህ ቤተ ክርስቲያናችሁ የጠፉትን ሰዎች ለመድረስ ስላላት ራእይ ምን ያሳያል?

22ኛ ጥያቄ:- ሀ) መጋቢ የሚለውን ቃል ስትሰማ ወደ አእምሮህ የሚመጣው ቃል ምንድን ነው? የመጋቢ ትልቁ ኃላፊነት ምንድን ነው? ለ) አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት መጋቢ የሚለውን ቃል የሚፈሩትና አገልጋዮቻቸውን በዚህ ማዕረግ ለመጥራት የማይፈልጉት ለምንድን ነው? ሐ) ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት መጋቢ ለቤተ ክርስቲያን የአመራር ችግር መፍትሔ ነው ብለው የሚያስቡት ለምንድን ነው? መ) ለቤተ ክርስቲያን መጋቢን መጠቀም የሚያስከትላቸው አዎንታዊና አሉታዊ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?

መ. <u>መጋቢ/አስተማሪ:-</u> «መጋቢ» የሚለው ቃል በሚጠራበት ጊዜ የተለያዩ አሳቦች ወደ ሰዎች አእምሮ ይመጣሉ:: ለምዕራባውያን የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ አገልግሎት የሚከታተልና በየእሑዱ ቀጣይነት ያለው የማስተማር አገልግሎት የሚሰጥ መጋቢ የሌለባትን ቤተ ክርስቲያን ማሰቡ ከባድ ነው:: ብዙ ሚሊዮናውያን ደከም ያሉ አብያተ ክርስቲያናትን በሚመለከቱበት ጊዜ የመጀመሪያው መፍትሔ ነው ብለው የሚያስቡት ነገር ቢኖር በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ መጋቢዎችን ማስቀመጥ ነው::

ነገር ግን በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ መሪዎች «መጋቢ» የሚለውን ቃል በሚሰሙበት ጊዜ፣ በቤተ ክርስቲያን ላይ መንፈሳዊ አምባገነን የሆነ ሰው ምስል ይታያቸዋል:: ሥልጣን ያለው የእርሱ ቃል ብቻ ነው:: ሰዎች የተለያዩ ነገሮችን እንዲያደርጉ ያዝዛቸዋል:: ማንም በዚህ ጉዳይ ላይ ጥያቄ አያነሣም:: ከእግዚአብሔር ሰምቶ ለሰዎች መልእክት ለማስተላለፍ የሚችለው መጋቢ ብቻ ነው ብለው ያስባሉ:: በአንዳንድ አገሮች ለመጋቢ ከፍተኛ ክብር በመስጠቱ፣ እንደ አገልጋይ መሪ ሳይሆን እንደ አገር መሪ የሚታይበት ሁኔታ አለ:: እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ አብያተ ክርስቲያናት መጋቢ አደገኛ ነገር ነው ብለው እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል:: በሽማግሌዎች መገልገል በስንት ጣእሙ? ሲሉ ያስባሉ:: እንዲሁም ደግሞ በየእሑዱ የአንድን ሰው ስብከት መከታተል ምእመናንን ያሰለቻቸዋል ብለው ያስባሉ:: ስለሆነም፣ አንድ ወጥነት ያለው ትምህርት መስጠት ባይቻልም፣ የተለያዩ አገልጋዮች በየእሑዱ ማገልገላቸው ጥሩ ነገር ነው ብለው ያስባሉ::



እንግዲህ ትክክለኛው ማን ነው? ትክክል ያልሆነውስ? ከዚህ በላይ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ምን ይላል? ለዚህ ጥያቄ የምናገኘው ምላሽ ሊያስገርመን ይችላል? የቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ከምንመለከታቸው አብያተ ክርስቲያናት በተለየ ሁኔታ ነበረ የተደራጀችው? የዛሬዎቹ አብያተ ክርስቲያናት አደረጃጀት ከቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያናት ጋር የሚመሳሰል አይደለም::

በመጀመሪያ፣ ስለ መጋቢዎች/አስተማሪዎች ሦስት አስገራሚ ነጥቦችን እንመልከት::

1) የቤተ ክርስቲያን መሪን ለማመልከት መጋቢ የሚለው ቃል የተጠቀሰው በኤፌሶን 4:11 ላይ ብቻ ነው:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ የቤተ ክርስቲያን መሪ መጋቢ ተብሎ መጠራቱን የሚያሳይ ምሳሌ የለንም:: ስለሆነም፣ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ተብሎ በሚጠራና በከፍተኛ ደረጃ በሚፈራ አንድ ሰው መመራቷን የሚያመለክት የመጽሐፍ ቅዱስ መረጃ ማግኘት አይቻልም:: እግዚአብሔር መጋቢ የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት ማዕከል እንዲሆን ቢፈልግ ኖሮ ስለዚህ የመሪነት አገልግሎት ሰፊ መረጃ በሰጠን ነበር:: ይህንን አለማድረጉ የመጋቢነት አገልግሎት በሌሎች መንገዶች ተግባራዊ እንደሚሆን ያሳያል::

2) ምሁራን ጳውሎስ በኤፌሶን 4:11 ለማመልከት የፈለገው አንድ ዓይነት አገልጋዮችን ነው ወይስ ሁለት ዓይነት? የሚል ጥያቄ ያነሣሉ:: ወይስ የመጋቢነትንም የአስተማሪነትንም አገልግሎት የሚሰጥ አንድ ሰው ማለቱ ነበር? የግሪኩ የዓረፍተ ነገር አወቃቀር መጋቢና መምህር ሆኖ የሚሠራውን አንድ ሰው የሚያመለክት ይመስላል::

3) በዚህ ክፍል ውስጥ ስለ ሽማግሌዎች ያልተገለጸው ለምንድን ነው? እንደምንመለከተው፣ አዲስ ኪዳን የቤተ ክርስቲያን ዋንኛ መሪዎች «ሽማግሌዎች» መሆናቸውን ያስረዳል:: ታዲያ በዚህ የጳውሎስ ዝርዝር ውስጥ ሽማግሌዎች የሚለው ቃል ለምን አልተካተተም? ምናልባት:-

ሀ) የእግዚአብሔር መንጋ (1ኛ ጴጥ. 5:1-3) እረኞች (መጋቢዎች) ናቸው፣ ደግሞም ለ) የእግዚአብሔር ሕዝብ አስተማሪዎች ናቸው (1ኛ ጢሞ. 3:2)። ጳውሎስ፣ አንድን መጋቢ የቤተ ክርስቲያን አባላትን በማስተማር ላይ የሚያተኩር ከሽማግሌዎች አንዱ የሆነ አድርጎ ይመለከተዋል ብለው አንዳንድ ምሁራን ያምናሉ። በ1ኛ ጢሞቴዎስ 5:17-18 ሽማግሌዎች፣ በተለይም ሥራቸው መስበክና ማስተማር የሆነ ሽማግሌዎች፣ የበለጠ ክብር የሚገባቸው መሆኑን ይጠቅሳል። ጳውሎስ፣ የሚሰብክና የሚያስተምር ሰው ለሚሰጠው አገልግሎት በቤተ ክርስቲያን ሊከፈለው የሚገባ መሆኑን ማስረዳቱን ይቀጥላል። ይህ አባባሉ ምንም እንኳ የእግዚአብሔርን ቃል በትርፍ ጊዜያቸው ያስተማሩ ብዙ ሽማግሌዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩ ቢሆንም፣ አንዳንዶቹ ሽማግሌዎች አብዛኛውን ጊዜያቸውን የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር ያሳለፉ ናቸው ማለት ሊሆን አይችልምን? ስለዚህ፣ እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች፣ አስተማሪ ሽማግሌዎች መጋቢ/አስተማሪ በመባል ይጠሩ እንደ ነበሩ ይገምታሉ።

ስለ መጋቢያን/አስተማሪዎች በሚናገርበት ጊዜ፣ ጳውሎስ ሽማግሌዎችን እያመለከተ መሆኑ የዚህ የጥናት መምሪያ ጸሐፊ አመለካከት ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመጨረሻው ዋነኛ መሪ ሽማግሌዎች ናቸው ይላል። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላሉ አማኞች እንክብካቤ ለማድረግ ቀጥተኛ ኃላፊነት የነበረባቸው ሽማግሌዎች ናቸው። ያም እንክብካቤ በሁለት አገልግሎቶች ላይ ያተኩራል። በ<u>መጀመሪያ</u>፣ «እረኛ» የመሆን መሪነት ነበር። ሽማግሌዎች፣ የቤተ ክርስቲያናቸውን እያንዳንዱን አባል፣ የእያንዳንዳቸውን መንፈሳዊ እድገት ደረጃ፣ ማወቅ ይጠበቅባቸዋል፣ እንዲሁም በመንፈሳዊ ረገድ ጤናማ እንዲሆኑ ሊረዱዋቸው ይገባል። <u>ሁለተኛ</u>፣ አስተማሪዎች ሊሆኑ ይገባቸዋል፣ ጥንቃቄም በሞላበት ሁኔታ የእግዚአብሔርን ቃል ማብራራት ያሻቸዋል፣ በዚህም የቤተ ክርስቲያን አባላት እያንዳንዳቸው የእግዚአብሔርን ቃል እውነት ያውቃሉ፣ ከሕይወታቸው ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ይረዳሉ፣ እንዲሁም እርሱን በመታዘዝ የሚኖሩ ይሆናሉ።



ስለዚህ፣ እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አንድ መጋቢ ያስፈልገዋል ማለት ነውን? አንድን ሰው መጋቢ ብሎ መጥራት ወይም አለመጥራት አይደለም ጠቃሚው ነገር። ይልቁንም፣ ይህን ጥያቄ በልዩ ልዩ መንገዶች መጠየቅ እንችላለን።

1) ከሽማግሌዎቹ በላይ የሆነ፣ ደግሞም የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎቶችን አስመልክቶ ውሳኔ የሚያሳልፍ፣ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚከናወኑ ነገሮችን ሁሉ የሚቆጣጠር መጋቢ ተብሎ የሚጠራ መሪ እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ያስፈልገዋልን? መጽሐፍ ቅዱሳዊው መልስ አይደለም የሚል እንደ ሆነ አምናለሁ። አዲስ ኪዳን አንድ ሰው የቤተ ክርስቲያን ራስ ይሁን አይልም። ያ ሥልጣን የኢየሱስ ክርስቶስ የብቻው ሥልጣን ነው። አዲስ ኪዳን ሁልጊዜ ቤተ ክርስቲያንን የመሩ መሪዎች ብዙዎች እንደ ሆኑ፣ በሁሉም ላይ የገዛ አንድ ሰውም እንዳልነበረ ያሳያል።

2) እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ የሆነውን የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት በጥንቃቄ በጥልቀት ለማሰብ በቂ ጊዜ ያለው አንድ ሰው ያስፈልገዋልን? ማኅበረ ምእመኑን በቀጣይነት ማስተማር ይችል ዘንድ በእግዚአብሔር ቃል በበቂ ሁኔታ የሠለጠነ አንድ ሰው መኖር አለበትን? ቤተ ክርስቲያንን ለሚዋጋ የስሕተት ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ መስጠት የሚችል አንድ ሰው መኖር አለበትን? አማኞችን በመጐብኘት ረገድ ከሽማግሌዎች ጋር በመሆን ሁኔታዎችን የሚያመቻች አንድ ሰው መኖር አለበትን? አዎን! ይህ በጣም ጠቃሚ እንደ ሆነ አስባለሁ። ብዙዎቹ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ሌላ የሙሉ ጊዜ ሥራ አላቸው። የቤተ ክርስቲያንን ጉዳዮችና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ሥራዎች ለማሰብ ያላቸው ጊዜ የተወሰነ ነው። አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ በመጠን እያደጉና፣ የበለጠም እየተወሳሰቡ በመሄድ ላይ ናቸው። ስለዚህ፣ አብያተ ክርስቲያናታችን ጠንካራ ሊሆኑ የሚችሉበት ነጥብ ለማኅበረ ምእመኑ ቀጣይነት ያለው ትምህርት ሊያቀርቡ የሚችሉ፣ እንዲሁም ለዚህ ትውልድ አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ መናገር የሚችሉ ተገቢ በሆነ መንገድ

የሠለጠኑ በቂ ሰዎች ካሉን ብቻ እንደ ሆነ አምናለሁ:: ነገር ግን፣ መጋቢው ሥራውን በሚገባ ለመሥራት በቂ ጊዜ ሊኖረው ይገባል::

3) መጋቢው በሽማግሌዎች ቊጥጥር ሥር ያለ የተቀጠረ ሰው መሆን ይገባዋልን? ወይም ከሽማግሌዎች መካከል አንዱ ሆኖ ሳለ ተጠያቂነቱ ለሽማግሌዎች የሆነ ትኩረቱን በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ ያደረገ ሰው መሆን ይኖርበታል? መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ መልኩ እጅግ ትክክለኛው መልስ፣ «መጋቢው» ከሽማግሌዎቹ አንዱ ነው የሚለው እንደ ሆነ አምናለሁ:: መሪ የሆነ ሽማግሌ ሊሆንም ሳይሆንም ይችላል:: ነገር ግን፣ በሁሉም ሽማግሌዎች ቊጥጥርና ምሪት ሥር መሆን አለበት:: እያንዳንዳቸው እኩል ሥልጣን ከሚይዙበት፣ ከብዙ ሽማግሌዎች መካከል አንዱ ነው:: መንጋውን ለመጠበቅና ለመመገብ ሁሉም ሽማግሌዎች ኃላፊነት አለባቸው:: ሁሉም ሽማግሌዎች ሕዝቡን ማስተማር አለባቸው:: ነገር ግን፣ ብኩን በምታደርግ ዓለማችን ውስጥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመጠበቅም ሆነ ለማስተማር የበለጠውን ጊዜያቸውን መስጠት የሚችሉ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች መኖራቸው አስፈላጊ ነው:: ዋናው ጉዳይ የመጋቢው የሥልጣን ደረጃ አይደለም፣ ነገር ግን የእግዚአብሔርን መንጋ በተሻለ ሁኔታ የመጠበቅና የማስተማር ሥራ እንዴት መከናወን ይችላል የሚለው ነው:: ሽማግሌዎች አገልግሎቻቸውን በሚገባ ለማከናወን በቂ ጊዜ የማይኖራቸው ከሆነ፣ እንግዲያስ፣ የእረኝነትና የማስተማር ኃላፊነቶች ተፈጻሚ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ከአባላቶቻቸው መካከል አንዱን አሊያም ተጨማሪ ሰዎችን ሙሉ ጊዜያቸውን እንዲሰጡና እንዲሠሩ መጠየቅ ያስፈልጋቸዋል::

| |
|---|
| 23ኛ ጥያቄ:- የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከቱ:- ሐዋርያት ሥራ 20:17-31፤ 1ኛ ጢሞ. 3:2፤ 5:17፤ ቲቶ 1:5፣ 9፤ ሐዋርያት ሥራ 15:2፣ 6፤ 22-29፤ ያዕቆብ 5:14፤ 1ኛ ጴጥ. 5:1-3:: ሀ) የአዲስ ኪዳን ሽማግሌዎች ያደረጉትን ዘርዝር:: ለ) ይህ በዘመናችን ብዙዎች ከሚያደርጉት የሚለየው እንዴት ነው? |



ሠ. <u>ሽማግሌዎች ወይም ጳጳሳት</u>:- መጋቢ/አስተማሪ የሚለው ስም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በማስተማርና በመስበክ ላይ የሚያተኩሩ አንድ ወይም ተጨማሪ ሽማግሌዎችን ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋለ ሆኖ ሳለ፣ በአዲስ ኪዳን እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የመሩ በርካታ ሽማግሌ ዎች ነበሩት:: እነዚህ ሽማግሌዎች አንዳንድ ጊዜ «ጳጳሳት» በመባል ተጠርተዋል:: (ሐዋርያት ሥራ 20:17ን ከሐዋርያት ሥራ 20:28 ጋር አመሳክር፣ ደግሞም ቲቶ 1:5ን ከቲቶ 1:7 ጋር አመሳክር):: «ሽማግሌ» የሚለው ቃል አንድ ሰው በጥበብ ለመምራት እንዲችል ዕድሜን እና ብስለትን ለማመልከት ጥቅም ላይ የሚውል ሆኖ ሳለ፣ «ጳጳስ» የሚለው ቃል «ተቈጣጣሪ» ማለት ነው:: አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች «ጳጳስ» የሚለው ቃል ዋነኛ የሆነው ሽማግሌ ሌላ መጠሪያ ነው ሲሉ ያምናሉ፣ ነገር ግን ይህ በአዲስ ኪዳን ውስጥ መኖሩን የሚያመለክት ነገር የለም:: እነዚህ ሽማግሌዎች ወይም ጳጳሳት የእያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነበሩ:: የሽማግሌ ዎችን ወይም የጳጳሳትን አገልግሎቶች በተመለከተ አዲስ ኪዳን የሚከተለውን ይገልጣል::

1) ቤተ ክርስቲያንን የሚመሩ ብዙ ሽማግሌዎች ነበሩ፣ አንድ ሽማግሌ ብቻ ከቶ አልነበረም:: የአዲስ ኪዳን የአሠራር ልማድ ሁልጊዜ መንፈሳዊ፣ ጠቢብ፣ እና ተሞክሮ ያላቸው መሪዎች ቤተ ክርስቲያንን እንዲመሩ፣ አንድ ሰው ከቶ እንዳይመራ የሚል ነው:: የምኩራብ አለቃ ከነበራቸው ከአይሁድ ጋር ባልተመሳሰለ መልኩ፣ በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከእነዚህ ሽማግሌዎች በበለጠ ኃይልና ሥልጣን አንዱ መሪ (ገዢ)ሽ በግል የተባለበት ሁኔታን አመልካች ነገር የለም:: በቤተ ክርስቲያን መሪዎችን እረኞች ለመሆን በአንድ ላይ የሚሠሩ ሽማግሌዎች የተባለ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቡድኖች አሉ::

2) የሽማግሌዎች/ጳጳሳት ተቀዳሚ ተግባራት የቤተ ክርስቲያን አባላትን ማስተማር ነው (1ኛ ጢሞ. 3:2፤ 5:17፤ ቲቶ 1:9):: ከመንፈሳዊ ባሕርያት ባሻገር አንድ ሽማግሌ ሊያሟላው የሚገባ

መመዘኛ ማስተማር መቻሉ» ነበር። ይህም የሚያመለክተው አንድ ሽማግሌ የሚመራበት ተቀዳሚ መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅና ማስተማር ነው። እነርሱ ቤተ ክርስቲያንን ከስሕተት ትምህርት የሚጠብቁ የእውነትም ጠባቂዎች ጭምር ናቸው (የሐዋርያት ሥራ 20:25-31)። ለሽማግሌዎች የአስተዳደር ክህሎት አስፈላጊ እንደ ሆነ ከታሰበ፣ እንግዲያስ ለሽማግሌዎች መረጣ በሰጠው መመዘኛዎች ውስጥ ያንን ያካትተው ነበር። ነገር ግን፣ የሽማግሌዎች ተቀዳሚው ኃላፊነታቸው ቤተ ክርስቲያንን ማስተዳደር አይደለም፤ ይልቁንም፣ ወደ መንፈሳዊ ብስለት በሚያደርጉት ጉዞ ይረዱአቸው ዘንድ አባላትን ማስተማርና መጠበቅ ነው።

3) ሁለተኛው የሽማግሌ አገልግሎት ዳኛ እንደሚያደርግ ማድረግ ነው (ሐዋርያት ሥራ 15:2፣ 6፣ 22-29)። በእግዚአብሔር ሕዝቦች መካከል አከራካሪ የሆኑ አስተምህሮአዊ ጉዳዮች ወይም አስቸጋሪ ችግሮች በሚኖሩበት ጊዜ፣ ሽማግሌዎች ከእግዚአብሔር ያገኙትን ጥበብ ችግሮቹን ለመፍታትና ሰላምን ለማውረድ ይጠቀሙበት ነበር።

4) የቤተ ክርስቲያንን ጉዳዮች እንደ መጋቢዎች ሊመሩ ይጠበቅባቸዋል (1ኛ ጢሞ. 5:17)። የአመራሩ ዓይነት በሰዎች ላይ ፍጹም የበላይ ከሆነው ፖለቲካ አገዛዝ ጋር ተመሳሳይ አልነበረም። ይልቁንም፣ «የእረኛ አመራር ነበር (ሐዋርያት ሥራ 20:28፤ 1ኛ ጴጥ. 5:1-3)። ይህም መንፈሳዊና ቍሳዊ ፍላጎታቸው ይሟላላቸው ዘንድ ለቤተ ክርስቲያን አባላት ጥቅም የሚደረግ ነገሮችን መቃኘት ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሽማግሌዎች ቤተ ክርስቲያንን ስለ ማስተዳደራቸውና እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን አባላትንና የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎቶችን ስለ መቆጣጠራቸው የምናገኘው ፍንጭ እጅግ ኢምንት ነው።

24ኛ ጥያቄ፡- ሐዋ. 6:2-4 እና 1ኛ ጢሞ. 3:8-13ን አንብብ። ሀ) የዲያቆናትን መመዘኛዎች ዘርዝሩ። ለ) አገልግሎታቸው ምንድን ነበር? የዲያቆናት አገልግሎት ከሐዋርያትና ከሽማግሌዎች የሚለየው እንዴት ነው። ሐ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ዲያቆናት የሚያደርጉት ምንድን ነው?



ረ. ዲያቆናት፡- ምንም እንኳ ጳውሎስ በኤፌሶን ውስጥ ባይጠቅሰውም፣ በአንዳንድ የአዲስ ኪዳን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ አንድ ሌላ ዓይነት መሪ አለ። ያም መሪ «ዲያቆን» ነበር። ዲያቆን የሚለው ቃል ከግሪክ የመጣ ሲሆን፣ በገበታ ላይ የሚያስተናግድ አገልጋይ ማለት ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይህ ቃል በሁለት የተለያዩ መንገዶች ጥቅም ላይ ውሏል። በመጀመሪያ፣ የሌላውን ፍላጎቶች የሚያገለግል አንድ ሰው የሚለውን ያመለክታል። ተቀጣሪ የሆነ አገልጋይ ወይም ሌላውን ሰው የሚረዳ አንድ ሰውን ያመለክታል (1ኛ ተሰ. 3:2፤ ቈላ. 1:7)። የሰዎችን አካላዊ ፍላጎት ማገልገል የሚል አሳብን ዘወትር ይይዛል (ሮሜ 15:25፤ 2ኛ ቆሮ. 8:4)። ሁሉም ክርስቲያኖች አንዳቸው ሌላውን የሚያገለግሉ «ዲያቆናት» ሊሆኑ ይገባል።

ነገር ግን «ዲያቆን» ለሚለው ቃል የበለጠ የሙያ መጠሪያ የሆነ አጠቃቀም አለ። በአዲስ ኪዳን ዘመን መጀመሪያ ላይ ቤተ ክርስቲያን እጅግ እየሰፋች ስትሄድ፣ ለሽማግሌዎችም አስተዳደራዊና የገንዘብ ጉዳዮችን ለመምራት አስቸጋሪ ስለ ሆነባቸው፣ «ዲቁና» ተብሎ የሚጠራ ሌላ ዓይነት አመራር እየጐለበተ ሄደ። እንዲህ ዓይነቱ መሪ በመጀመሪያ በሐዋርያት ሥራ 6 ተጀመረ። ምንም እንኳ 7ቱ ሰዎች ዲያቆናት ተብለው ባይጠሩም፣ ሐዋርያው እግዚአብሔር የሰጣቸውን አገልግሎት የማዕድ አገልግሎት ብሎታል (ሐዋርያት ሥራ 6:2)። የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን እጅግ እያደገች በሄደችበት ጊዜ፣ እንደ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች እየሠሩ የነበሩት ሐዋርያት፣ ዝርዝር የሆነ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርን እና ዋነኛ የሆነውን የማስተማርና የመጸለይ፣ እንዲሁም ለአማኞች የሚደረግን መንፈሳዊ እንክብካቤ፣ ሁለቱንም፣ ማከናወን እንዳይችሉ ተገነዘቡ። ስለዚህ፣ ዲያቆን የሆኑ መሪዎችን አስነሡ፣ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደራዊ ጉዳዮች፣ በተለይም ለሌሎች የሚደረግን በገንዘብ የሚሆን ርዳታ ተግባር፣ እንዲያከናውኑ ሥልጣንን ሰጡዋቸው። ጳውሎስ የመሠረታቸው ብዙ አብያተ ክርስቲያናትም ጭምር ይህን የአሠራር ሂደት ተከተሉ። አብያተ ክርስቲያናት አዳዲስ በሚሆኑበትና ሊያከናውኑት የሚገባ በዝርዝር የተቀመጠ ነገር

በማይኖርበት ጊዜ፣ በዚያን ጊዜ ሽማግሌዎች ብቻ ይመረጣሉ:: ስለዚህም፣ በቲቶ መጽሐፍ ውስጥ በቀርጤስ የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት ትንሽ በነበሩበት ጊዜ፣ ሽማግለሌዎችን ብቻ እንዲመርጥ ጳውሎስ ቲቶን አዘዘው (ቲቶ 1):: ነገር ግን፣ እጅግ ትልቅ ለሆነችው የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን በተጻፈ ደብዳቤ፣ ሽማግሌዎችንና ዲያቆናትን፣ ሁለቱንም እንዴት መምራት እንዳለበት ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ነገረው (1ኛ ጢሞ. 3:1-13):: በፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያንም ሽማግሌዎችም ሆነ ዲያቆናት ሁለቱም፣ እንደዚህ ተጠቅሰዋል (ፊልጵ. 1:1):: ዲያቆናት የሆኑት እነዚያ ሰዎች ለአገልጋይነት የሚሆን መንፈሳዊ ስጦታ ያላቸው መሆኑ እያጠራጥርም (ሮሜ 12:7፤ 1ኛ ጴጥ. 4:11):: ምንም እንኳ ይህ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እራሳቸውን የሰጡ አንዳንድ ሰ ዎችን ለማመልከት የሚሆን ዲያቆን የሚለው ቃል አጠቃላይ አጠቃቀም ሊሆን ቢችልም፣ ሴቶችም እንደዚሁ በዲቁና አገልግለዋል (ሮሜ 16:1)::

የዲያቆናት መመዘኛ መስፈርቶች ምንድን ነበሩ? ከሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ታሪክ በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸው ተገልጦ እንደሚታየው፣ በጥበባቸውና በመልካም የተመሰከረላቸው ሊሆኑ የሚገባ መሆኑን መመልከት እንችላለን:: በ1ኛ ጢሞቴዎስ 3 ላይ ዲያቆናት ከሽማግሌዎች ጋር አንድ ዓይነት የሆነ መንፈሳዊ የመመዘኛ መስፈርት ይዘው እንደ ነበረ እንመለከታን:: ይሁን እንጂ፣ ሁለት ነገሮችን ልብ ማለት እንችላለን:: በመጀመሪያ፣ ብዙ ገንዘብን የሚመለከት ኃላፊነት ስለ ነበረባቸው፣ ዲያቆናት የገንዘብ ፍቅር ሊያድርባቸው እንደማይገባ፣ እንዲሁም ገንዘብን በተመለከተ የማይነቀፉ መሆን የሚገባ መሆኑ ላይ ጳውሎስ አጽንዖት ይሰጣል:: ሁለተኛ፣ ለሽማግሌዎች ከተሰጠው የመመዘኛ መስፈርት ውስጥ እጅግ ልብ የሚባለው ልዩነት የማስተማር ችሎታ ለዲያቆናት ያልተጠቀሰ፣ ሽማግሌዎች ሁሉ ግን ለማስተማር የሚበቁ መሆናቸው የሚጠበቅ መሆኑ ነው::

አዲስ ኪዳን የሽማግሌዎችን ኃላፊነቶች እንዲሁም የዲያቆናትን ተግባራት በተመለከተ የአሠራር መዋቅርን



ያስቀምጣል:: ሽማግሌዎች በእረኛነትና በማስተማር እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ መንፈሳዊ አገልግሎቶች ላይ እንዲያተኩሩ ይፈለግባቸዋል:: ከሐሰተኛ ትምህርት እነርሱን በመጠበቅ፣ በእምነታቸው እንዲያድጉ በመርዳት እንዲሁም እግዚአብሔርን ለማገልገል እነርሱን በአገልግሎት ውስጥ እንዲሳተ ፉ በማድረግ የቤተ ክርስቲያን አባላት ለሆኑ ነፍሳት ሊደረግ ስለሚገባው እንክብካቤ ትኩረት ሊሰጡ ይገባል:: ዲያቆናት ገንዘብን በተመለከተ፣ ምናልባትም ደግሞ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ አገልግሎቶችን በተመለከተ፣ ኃላፊነት አለባቸው:: መባን ከመሰብሰብ የበለጠ ነገር አከናውነዋል:: የሰዎችን የገንዘብ ፍላጎት ለማሟላት የሚደረገውን የገንዘብ ዕደላ ይቆጣጠራሉ:: የትኞቹም አዲስ ኪዳናዊ የሽምግልና መግለጫዎች በቤተ ክርስቲያን አስተ ዳደራዊ ሥራ ላይ የሚያተኩሩ ባለመሆናቸው፣ ይህ በተቀዳሚነት የዲያቆናት ኃላፊነት የነበረ ይመስላል:: በእርግጥ፣ በጥንት ቤተ ክርስቲያን፣ የሚገነቡዋቸውም ሆነ የሚያስተዳድሩዋቸው ሕንፃዎች አልነበሩም፣ የሚያስተዳድሩት የእሑድ ትምህርት ቤት መርሐ ግብር አልነበረም፣ ደግሞም አመራር ሊሰጠው የሚገባም መዋቅር (ቤተ እምነት) አልነበረም:: ስለዚህ፣ ከዛሬ ጋር ሲወዳደር ዲያቆናት በኃላፊነት የሚያከናውኑዋቸው አስተዳደራዊ ሥራዎች ውሱን የሆኑ ነበሩ::

ዛሬ አብያተ ክርስቲያናታችን ይህን መንፈሳዊ አገልግሎትን እና የገንዘብ አስተዳደር አገልግሎትን መለያየትን በጥንቃቄ መመልከት ያስፈልጋቸዋል:: የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የቤተ ክርስቲያንን ጉዳዮች (ድርጅታዊ ለሆነ አሠራር እንክብካቤ ማድ ረግ፣ ለአገልግሎቶችም አመራር ቁጥጥርን ማድረግ፣ ወዘተ. . .) የቤተ ክርስቲያናቸውን አባላት ለማወቅ፣ እያንዳንዱን አባል በመንፈሳዊ ሕይወቱ ወይም ሕይወቷ ለመምራት፣ ለመጸለይና ለማስተማር እጅግ በሥራ የተጠመዱ ናቸው:: ብዙዎቹ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች በጥንት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሐዋርያቱ እምቢ ያሉትን ዋነኛ ነገር፣ የአስተዳደር ሥራን፣ በማከናወን የተ ወጠሩ ይመስላሉ:: በውጤቱም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለእ ረኛነትና ለመንፈሳዊ አገልግሎት ሽማግሌዎች የሚኖራቸው ጊዜ

ትንሽ ይሆናል፡፡ ምናልባትም የእግዚአብሔር ፍላጎት እያንዳንዱን የመንጋውን አባል ሽማግሌዎች ባላቸው መንፈሳዊ ብስለት እንዲሁም ባላቸው የማስተማር ችሎታ በጸሎትና በእረኝነት አገልግሎት በኩል መንፈሳዊ የሆነ አመራርን እንዲሰጡ ነው፡፡ በእነዚህ የመንፈሳዊ እድገት አገልግሎቶች ላይ ማተኮር ይጠበቅባቸዋል፡፡ ደግሞም ሌሎቹ አስተዳደር-ነክ የሆኑ አገልግሎቶች የዲያቆናት አገልግሎቶች ሲሆኑ ይገባል፡፡ ዲያቆናቶቻችንን መባን እንደ መሰብሰብ፣ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ማጽዳት፣ ወንበርና ጠረጴዛዎችን እንደ ማስተካከል፣ ወይም ሰ ዎችን በእሑድ አምልኮ ላይ የሚቀመጡበትን ስፍራ በማሳየት እንደ ማስተናገድ ባሉ ቀላል ሥራዎች ከመገደብ ይልቅ፣ ዲያቆናት የበለጠ ኃላፊነት ሲሰጣቸው ይገባል፡፡ እግዚአብሔር ለእነርሱ የአስተዳደር ስጦታን ለጥቷቸው ከሆነ፣ የገንዘብ ጉዳይን ሲቆጣጠሩ፣ መንፈሳዊ ባልሆኑ የቤተ ክርስቲያን እና የቤተ እምነት ጉዳዮች ላይ አስተዳደራዊ አገልግሎት ሊያበረክቱ ይገባቸው ይሆናል፡፡

በ1ኛ ቆሮንቶስ 12:28 ጳውሎስ «የአስተዳደር ስጦታም» ጭምር እንዳለ ይናገራል፡፡ አስተዳዳሪ/ሥራ አስኪያጅ ከመሪ የተለየ ነው፡፡ መሪ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ሊወስዳት የሚፈልገው አቅጣጫን በመወሰን ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያንን ግብ ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመፈጸም የሚያስችሉ አገልግሎቶችን በማከናወን ላይ ያተኩራል፡፡ እግዚአብሔር ለአንዳንድ ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን በመንፈሳዊ ብስለት በማሳደግ ረገድ እንዴት መረዳት እንደሚገባቸው የሚገነዘቡበትን ልዩ ችሎታ ለጥቷቸዋል፡፡ ነገር ግን፣ አስተዳዳሪ ማለት ያሉትን አገልግሎቶች የበለጠ ቀልጠፍ ባለ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲሠሩ የሚ ረዳ ሰው ነው፡፡ እግዚአብሔር ለአንዳንድ ሰዎች ነገሮችን የማደራጀት እንዲሁም የድርጅቶችን ዝርዝር አሠራር በተመለከተ እንክብካቤ የሚያደርጉበትን ችሎታ ለጥቷቸዋል፡፡ የአስተዳደር ስጦታ የአመራር ስፍራ ቢሆን ኖሮ፣ ጳውሎስ ክቶ አይናገረውም፡፡ ይህ ስጦታ ለሽማግሌዎች ወይም ለዲያቆናት ተስጥቷቸው ቢሆን ኖሮ፣ አይነግረንም ነበር፡፡ ነገር ግን ዲያቆናት በሚኖራቸው



የአገልግሎት ዓይነት ምክንያት በተለይ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ላላቸው አስፈላጊ የሆነውን ጠቃሚ ከሆኑ ስጦታዎች እንዱ የሆነው ይህ ስጦታ ለዲያቆናት የተሰጠ ይመስላል፡፡ ቤተ ክርስቲያን እያደገች በምትሄድበት ጊዜ፣ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ማስተባበር፣ ብዙ የሀብት ምንጮች፣ እንዲሁም ብዙ መዋቅሮች ያስፈልጉአታል፡፡ በመሆኑም፣ የአስተዳደር ስጦታ ያላቸው ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለን እያንዳንዱን አገልግሎት በቀልጣፋ ሁኔታ ለማሠራት ይችላሉ፡፡ ይህ በአዲስ ኪዳን በዲያቆናት ቁጥጥር ሥር የሚደረግ ይመስላል፡፡

| |
|---|
| 25ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ያለውን የዲያቆናት ሚና በአዲስ ኪዳን ዘመን ከነበረው ጋር አወዳድር፡፡ ለ) ሽማግሌዎች የበለጠ እንደ መንፈሳዊ እረኞች እንዲሁም ዲያቆናት እንደ ሥራ አስኪያጆችና አስተዳዳሪዎች ቢሆኑ በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ምን ዓይነት ለውጦች ይከሰታሉ? ሐ) የሽማግሌዎችንና የዲያቆናትን ሚና የበለጠ አዲስ ኪዳንን እንዲመስል አድርጎ ማስተካከል መልካም እንደሚሆን ታስባለህን? |

2\. የተለያዩ ዓይነት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአንድ ላይ በመሥራት ለቤተ ክርስቲያን ያለውን የእግዚአብሔርን ዓላማ እንዴት ሊፈጽሙት ይችላሉ፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ሁሉም ልዩ ልዩ መሪዎች ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ በአንድ ላይ መሥራታቸው አስፈላጊ መሆኑን ልብ ማለት የሚያስደስት ነው፡፡

ሐዋርያት፣ በዛሬው ዘመን የድርጊት ትግበራ እግዚአብሔር የጠራቸውና ቤተ ክርስቲያንን ምንም በሌለበት ስፍራ አዲስ ቤተ ክርስቲያን እንደ መትከል ያለውን አዳዲስ ቤተ ክርስቲያን መጀመር ይችገራሉ፡፡ ነገር ግን ይህንንም በደንብ ሊያከናውኑ የሚችሉ እንዳንድ ሰዎችን ሰጥቷል፡፡ ሌላ አማኝ የሌለበት ስፍራ ሄደው ቤተ ክርስቲያን ይተክላሉ፡፡ ከእግዚአብሔር ያላቸው ጥሪ እንደ ቤተ ክርስቲያን ለረጅም ጊዜ ለማስተዳደር የሚሆን አይደለም፡፡ ብዙውን ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የሚተክሉ ሰዎች ጠንካራ ስብዕና ያላቸው ስለሆነ፣ በዚህ ላይ በአንድ ስፍራ ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ ከሆነ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊኖር ለሚገባው የአጥቢያ አመራር መጉልበት እንቅፋት ይሆናሉ፡፡ ነገር ግን፣ ቤተ

ክርስቲያንን ለመመሥረት ከእግዚአብሔር ያገኙት ስጦታ አላቸው:: ቤተ ክርስቲያን አንድ ጊዜ ከተመሠረተች፣ ሙሉ የሆነ አገልግሎትን በአጥቢያ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለመስጠት ሌሎች ዓይነት መሪዎች በአንድ ላይ መሥራት ያስፈልጋቸዋል::

ነቢያት፣ ቤተ ክርስቲያን እንድታደርገው እግዚአብሔር የሚፈልገውን ነገር በተመለከተ ወይም ከእግዚአብሔር መንገድ መውጣት በምትጀምርበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ለመገሠጽ የነቁ ናቸው::

ወንጌላውያን፣ ያልዳኑ ሰዎችን ለመድረስ፣ ወንጌልን ለማካፈል፣ እንዲሁም ሰዎችን ከጌታ ኢየሱስ ጋር ለማስተዋወቅ ይተጋሉ::

መጋቢዎች/አስተማሪዎች/ሽማግሌዎች፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላለ ለእያንዳንዱ አማኝ መንፈሳዊ እድገት እንክብካቤ ያደርጋሉ:: እያንዳንዱ አባል ትምህርት እንደ ተሰጠው፣ ወደ ስሕተት ወይም መንፈሳዊ መዝናናት እንዳላመራ፣ ደግሞም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማገልገል እንደ ጀመረ ያረጋግጣል::

እንዲሁም ዲያቆናት፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጋቢ ዎች/አስተማሪዎችና/ሽማግሌዎች በተቀዳሚነት በመንፈሳዊ አገልግሎቶች ላይ ማገልገል እንዲችሉ አስተዳደራዊ/የገንዘብ ጉዳይ ኃላፊነቶችን ይወጣሉ::

ይህ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን እንድትሆን የነደፈው ነገር ይመስላል:: ከእነዚህ ዓይነት መሪዎች የትኞቹም ቢታጡ፣ ቤተ ክርስቲያን የተሟላች አትሆንም፣ ደግሞም እግዚአብሔር እንድታደርግ የሚወድደውን ሁሉ ማድረግ አትችልም::

3. ሁሉም መሪዎች በአንድ ላይ ሊሠሩበት የሚገባው የመጨረሻው ግብ::

26ኛ ጥያቄ:- ኤፌሶን 4:11-16:: እነዚህ መሪዎች ሊያደርጉት ስለሚገባው ነገር ጳውሎስ ምን አለ? በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የአገልግሎቶቻቸው ሁሉ የመጨረሻ ግብ ምንድን ነው?



እነዚህ መሪዎች በበቂ ሁኔታ የነበሩን በመሆኑ ብቻ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እያንዳንዱ ነገር በደንብ ይሠራል እንደሚል አድርገን ጳውሎስን እንጠብቀው ይሆናል:: ነገር ግን፣ ጳውሎስ እነዚህ የእያንዳንዱ ዓይነት መሪዎች በምን ላይ ማተኮር እንዳለባቸው በተመለከተ ጠቃሚ የሆነ ትምህርትን ያቀርባል:: ቤተ ክርስቲያንን በመወከል የየራሳቸውን አገልግሎት ማከናወንን ማጉላት ብቻ አይጠበቅባቸውም:: ይልቁንም፣ ሁሉም አባላት ሥራውን በአንድ ላይ ያከናውኑት ዘንድ፣ የቤተ ክርስቲያንን አባላት ማሠልጠን ይጠበቅባቸዋል:: እነዚህ የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከአነርሱ ጋር እንዲሠሩ የቤተ ክርስቲያንን አባላት ሁሉ በማሠልጠን ብቻ ዓለምን ለክርስቶስ በወንጌል የመድ ረስ ጥሪዋን ማከናወን ትችላለች:: የቤተ ክርስቲያን አባላት ሁሉ በአገልግሎት ውስጥ በሚሳተፉበት ጊዜ፣ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የበለጠ ሙሉ በሙሉ የሚከናወን ይሆናል:: ለምሳሌ ያህል፣ አንድ ወንጌላዊ በሳምንት ለ40 ሰዎች ወንጌልን መመስከር ይችል ይሆናል:: ይሁን እንጂ፣ በሳምንት ለ10 ሰዎች የሚመሰክሩ 100 የቤተ ክርስቲያን አባላት በሳምንት 1000 ሰዎችን መድረስ ይችላሉ:: አንድ ሽማግሌ መንፈሳዊ እድገታቸውን ለማረጋገጥ በሳምንት 20 የቤተ ክርስቲያን አባላትን መጐብኘት ይችላል:: ነገር ግን፣ መንፈሳዊ እድገታቸውን ለመከታተል በሳምንት 5 ሰዎችን የሚከታተሉ 50 የቤተ ክርስቲያን አባላት ለ250 ሰዎች በሳምንት እ ረኛ መሆን ይችላሉ:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ክርስቶስን በማገልገል ተግባር እንዲሳተፉ በማሠልጠኑበት ጊዜ፣ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን አባላት ሁሉም በአገልግሎት ውስጥ በንቃት በሚሳተፉበት ጊዜ፣ አንደ አካል የበለጠ ሙሉ በሙሉ ወደ መንፈሳዊ ብስለት እየጐለበቱ ይሄዳሉ ሲል ጭምር ጳውሎስ ያስተ ምራል:: ወደ ተሳሳተ ትምህርት የማዘንበሉ ሁኔታ ይቀንሳል:: እንዲሁም አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን አባላት በመንፈሳዊ ሁኔታ በሚበስሉበት ጊዜ፣ እያንዳዱ እርስ በርስ እየተረዳዳ የሚያድግበት፣ እውነትን በፍቅር የሚነጋገርበት፣ ወዘተ . . . ታላቅ አንድነት ይኖራል::

የቤተ ክርስቲያን አባላት ሁሉ ከተማሩና በአገልግሎት የተሰማሩ ከሆነ ምን ዓይነት ኃይለኛ ቤተ ክርስቲያን ናት የምትኖረው! ለዚህ ነው የጥንት ቤተ ክርስቲያን እጅግ በፍጥነት ታድግ የነበረችው:: ለዚህ ነው የጥንት ቤተ ክርስቲያን በቁጥር ማደግና በሮማ ግዛት ሁሉ መሰራጨት ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን፣ በማኅበረሰቡ ላይም እንዲሁ ተጽዕኖዋን ማሳለፍ የቻለችው::

| |
|---|
| 27ኛ ጥያቄ:- አንተ 1000 አባላት የሏት ቤተ ክርስቲያን አባል ነህ እንበል:: እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጣትን ልዩ ልዩ ዓይነት መሪዎች በተመለከተ ከላይ የተሰጠውን መረጃ በመያዝ ጳውሎስ የአመራር ግብ፣ ማስተም እያንዳንዱ አባል የበሰለና በአገልግሎት ውስጥ የሚሳተፍባት ቤተ ክርስቲያን መገንባት፣ የሚለውን ለማሳካት ቤተ ክርስቲያናችሁን እንዴት ታዋቅራታለህ? |

4. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች (ሽማግሌዎች፣ ወንጌላውያን፣ ነቢያት፣ መጋቢዎች/አስተማሪዎች፣ ዲያቆናት) የሚሠለጥኑት እንዴት ነው? አዲስ ከዳን ሰዎችን ለአገልግሎትና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላለ አመራር እንዴት ታሠለጥን እንደ ነበረ የሚሰጠን መረጃ ትንሽ ነው:: ምናልባት ይህ የሆነበት ምክንያት ለምእተ ዓመታት አይሁዶች የሚጠቀሙበትን የአመራር ሥልጠና ስለ ቀጠለችበት ይሆናል:: ምናልባት በአመራር ላይ ያለው የቤተ ክርስቲያን መሪ ለአመራር ያበቃቸው ዘንድ ወደ ፊት ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት አቅም ያላቸውን ይዞ ጥንቃቄ በሞላበት ሁኔታ እነርሱን በማሠልጠን ላይ ይሆናል:: የ1ኛ እና 2ኛ ጢሞቴዎስ መጽሐፍ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰዎችን እንዴት ማዘጋጀት ይቻላል ለሚለው እጅግ ግልጽ የሆነ ጥቆማዎችን ያቀርብልናል::

| |
|---|
| 28ኛ ጥያቄ:- 2ኛ ጢሞ. 2:2ን አንብብ:: ሀ) ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የሰጣቸው ትእዛዛት ምንድን ናቸው? ለ) ሰዎቹ መሠልጠን ያለባቸው እንዴት ነው? ሐ) ከሠለጠኑ በኋላ ምን ሊያደርጉ ይጠበቅባቸዋል? |

ሀ. እግዚአብሔርን ለማገልገል በመዘጋጀት ረገድ ይረዳቸው ዘንድ ሁልጊዜ ሰዎችን መፈለግ እንደሚገባው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ነግሮታል:: ጢሞቴዎስ ሊያስተምራቸው የሚችል ታማኝ ሰ



ዎችን መፈለግ ይጠበቅበታል:: እነዚህም በበኩላቸው ሌሎችን ማስተማር ይጠበቅባቸዋል (2ኛ ጢሞ. 2:2)::

ለ. ሰዎችን ለማሠልጠን ተቀዳሚው ለምርጫ የሚሆን የመመዘኛ መስፈርት ባሕርያቸው ነበር:: «ታማኝ» ሊሆኑ ይገባል:: ጳውሎስ ከእግዚአብሔር ጋር የበሰለ ግንኙነት ሊኖራቸው ያስፈልጋል ይላል:: ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡ መሆን ይኖርባቸዋል፤ ደግሞም እግዚአብሔርም ሆነ ሌሎች ሰዎች እንዲያደርጉ የሚጠይቁዋቸውን ለማድረግ የሚታመኑባቸው ሰዎች መሆን ይጠበቅባቸዋል::

ሐ. የሥልጠናው ዓይነት ከእነዚህ ግለሰቦች ጋር አብሮ በመኖር የአስተማሪና የደቀ መዝሙር ግንኙነትን በመመሥረት የሚደረግ ነበር:: የመሪውን ሕይወት በማየት ይማሩ ነበር:: የሥልጠናው ዋነኛ መሣሪያዎች:-

1) ሕይወት:- ጳውሎስ የእርሱን የኑሮ ምሳሌነት እንዲከተል ጢሞቴዎስን ያስታውሰዋል (2ኛ ጢሞ. 3:10-14):: ለሌሎች ምሳሌ እንዲሆን፣ ለአማኞችም በሕይወት፣ በፍቅር፣ በእምነትና በንጽሕና መልካም የሆነ ሕይወትን በመያዝ ምሳሌነት እንዲኖረው ለጢሞቴዎስ ነግሮታል (1ኛ ጢሞ. 4:12)::

2) የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር:- ጳውሎስ እንዴት እርሱን እንዳስተማረው ጢሞቴዎስን ያስታውሰዋል (2ኛ ጢሞ. 1:13-14):: ዕድሉን በሚያገኝበት ጊዜ ሁሉ፣ እንዲሰብክና እንዲያስተምር ጢሞቴዎስን ያበረታታዋል::

3) በአገልግሎት ውስጥ መሳተፍ:- ጳውሎስ በአገልግሎት ውስጥ በመሳተፍ እንዲቆይ ጢሞቴዎስን ያስጠነቅቀዋል:: የወንጌል ለባኪነትን ሥራ ማከናወን ይጠበቅበታል (2ኛ ጢሞ. 4:2፣ 5):: ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ያደረገውን ነገር ለአዳዲስ መሪዎች እርሱ እንዲያደርግ ይጠበቅበታል:: ጢሞቴዎስ ለእነዚህ አዳዲስ መሪዎች ደረጃቸው የጨመረ ኃላፊነቶችን አምኖ እንዲሰጣቸው ይጠበቅበታል::

4) <u>ጊዜ</u>:- ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችንና አገልጋዮችን ለማመልከት (ሽማግሌ) የሚለውን ቃል ይጠቀማል:: ይህ ቃል በዕ ድሜ መብሰልን ያሳያል:: በጥንት ጊዜ፣ ሰዎች ሊመሩ የሚገባቸው ዕድሜ የጠገቡ ሊሆኑ ይገባል ሊሉ ያስባሉ:: ጊዜ ለሦስት ነገሮች አስፈላጊ ነው:: በ<u>መጀመሪያ</u>፣ ሰዎች በጊዜ ብዛት የመምራትን ልምድ ያገኛሉ:: ሰዎችን በመመልከት እንዲሁም ሽማግሌዎችን በመርዳት አንድ ሰው እንዴት አመራር እንደሚሰጥ ይማራል:: ይህ ተግባራዊ ሥልጠና ከመጽሐፍ ሊማሩት የማይችሉትን ጥልቀት ያለው ተሞክሮ ይሰጣል:: <u>ሁለተኛ</u>፣ ጥበብን ማግኘት ጊዜን ይጠይቃል:: በክፍል ውስጥ የሚሰጥ ትምህርት ስለ አንድ ነገር እውነታዎችን የምንማርበትን እውቀትን ሊያስተምር ይችላል:: በቤተ ክርስቲያን የቱ እንደሚሠራና የቱ እንደማይሠራ፣ እንዲሁም አንድ መሪን የሚገጥሙትን ልዩ ልዩ ችግሮችን ለመፍታት ሰዎች የሚማሩት በጊዜ ውስጥ ነው:: <u>ሦስተኛ</u>፣ በመንፈሳዊ ረገድ የበሰሉ ለመሆንና መንፈሳዊ ለመሆን ጊዜ ይጠይቃል:: በአንድ ወይም በሁለት ዓመታት ጊዜ ብቻ የበሰለ የሚሆን ማንም የለም:: ክርስቶስን የሚመስል ለማድረግ፣ መንፈስ ቅዱስ በባሕርይ ዝንባሌዎች እና በሰውየው የልብ አሳብ ላይ እየሠራ ሳለ፣ ጊዜን ይወስዳል:: እነዚህ ነገሮች በግልጽ እስኪታዩ ድረስ፣ አንድ ሰው ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት በቂ አይደለም::

| |
|---|
| 29ኛ ጥያቄ:- ሀ) ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ማሠልጠንን እንዴት ይመለከተው እንደ ነበር፣ እኛም ዛሬ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ማሠልጠንን እንዴት እንደምንመለከት፣ በመካከል ያለውን ልዩነት አብራራ:: ለ) መሪዎችን እና አገልጋዮችን አዲስ ኪዳናዊ በሆነ መንገድ እንዴት ማሠልጠን አለብን የሚለውን በተመለከተ ምን ጠቃሚ ትምህርቶች ልንማር እንችላለን? |

## ሦስተኛ ቀን

**ከእግዚአብሔር ሕዝቦች ታሪክ በቤተ ክርስቲያን አመራርና አስተዳደራዊ መዋቅሮች ላይ የምንማራቸው ትምህርቶች (ክፍል 5** - ከሐዋርያት በኋላ ያለ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ)



በታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ጠንካራ የሆነ ለዓለም የሚሆን ስበታዊ የሆነ መማረክ ነበረባቸው:: በብሉይ ኪዳን ውስጥ አይሁድ እንደ ሌሎች ሕዝቦች ለመሆንና የገዛ ራሳቸውም ንጉሥ እንዲኖራቸው (1ኛ ሳሙ. 8:5) እንዲሁም ልክ በዙሪያቸው እንዳሉ ሕዝቦች ጣዖታትን ማምለክ ፈልገው ነበር (ሕዝ. 23:30):: በተመሳሳይ መልኩ፣ በዘመናችን ዓለምን ለመምሰል የሚሆን ጠንካራ የሆነ መሳብ አማኞችን ይገጥማቸዋል:: ይህ እንዴት እንልበስ፣ እንዲሁም ማንን እናግባና ምን ብናስብ ጠቃሚ ነው በሚሉት ተግባራት ሊታይ ይችላል:: ነገር ግን፣ አመራርንም በምንረዳበት መንገድ እንዲሁ ሊታይ ይችላል:: አመራርን በምንረዳበት እንዲሁም ለአመራር የሚሆን የአስተዳደር መዋቅሮችን እንዴት እናደራጅ በሚሉት በሁለቱም ዓለምን ለመኰረጅ የሚሆን ጠንካራ ዝንባሌ በአማኞች ላይ አለ::

ለሦስት ዓመት ተኩል ጊዜ፣ ኢየሱስ በጥንቃቄ ደቀ መዛሙርቱን አስተማራቸው:: አጉልቶ ይመለከታቸው ከነበሩ ነገሮች መካከል አንዱ አመራርን ይረዱበት የነበረውን መንገድ መለወጥ ነበር:: በእግዚአብሔር ሕዝቦች ላይ የሚደረግ አመራር ብዙዎቻችን በትምህርት ቤት ከተማርነው የተለየ ዝንባሌ አለው:: ሰዎችን ከመግዛት ይልቅ፣ እነርሱን ለማገልገል ከሚሆን ልብ መምጣት አለበት:: በቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል ልዩነት ከማድረግ መቆጠብ እንደሚያስፈልግ ኢየሱስ አስጠንቅቋል:: ደግሞም ዛሬ ብዙ ቤተ እምነቶች ያላቸው የአመራር ሥልጣን ተዋረድን ማጉልበትን በተመለከተ ቤተ ክርስቲያኑ የምትጠባበቀው ምንም ነገር አልተናገረም::

በ33 ዓ.ም ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከተመለሰ ጀምሮ፣ የመጨረሻው ሐዋርያው ዮሐንስ እስከ ሞተበት 100 ዓ.ም ድረስ፣ ቤተ ክርስቲያን ከኢየሩሳሌም በመነሣት በአብዛኛዎቹ የሮማ ግዛቶች ተሰራጭታለች:: በእነዚህ ዓመታት ውስጥ እንደ ጴጥሮስና ጳውሎስ ያሉ ሐዋርያት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ስለሚሆን አመራር ኢየሱስ ያስተማራቸውን ትምህርቶች ተግባራዊ ለማድረግ በጥንቃቄ ሞክረዋል:: ምንም እንኳ ሐዋርያት በኢየሱስ ላይ ያለ እምነት

የሚጠይቀውን ነገር ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት እንደ ተረዱት ለማረጋገጥ የለፉ ቢሆንም፣ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሉ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ርቀው ነበር:: ደግሞም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖችን እርስ በርስ በማያያዝ እያደገች ያለችውን ቤተ ክርስቲያን ወደ «ቤተ እምነት» ለማዋቀር ይጥሩ እንደ ነበር የሚያሳይ ጠቋሚ ነገር የለም:: በዚህ ፈንታ፣ ሐዋርያት በሚሄዱበት ስፍራ ሁሉ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖችን እንዲመሩ «ሽማግሌዎችን» ይመርጡ ነበር::

እነዚህ ሽማግሌዎች በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ ማተኮር እንደሚገባቸው ወይም አማኞችን ለማስተዳደር እንደሚሞክሩ የሚያመለክት ነገር የለም:: ይልቁንም፣ ሽማግሌዎች ሌሎች አማኞችን ለማገልገል ይመረጣሉ:: ከእምነት እንዳይመለሱ ክርስቲያኖች እንክብካቤና ጥበቃ እንዲያደርጉላቸው በእግዚአብሔር የተመረጠ <u>እረኞች</u> ናቸው:: ሰዎች እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ እንዴት መኖር እንደሚቻል ያውቁ ዘንድ የእግዚአብሔርን ቃል በጥንቃቄ የሚገልጡ <u>አስተማሪዎች</u> ነበሩ:: ሽማግሌዎች በእግዚአብሔር ቤተሰቦች መካከል ይህ ግንኙነት ምን ያህል የተቀራረበ መሆኑን ለማመልከት ከሌላኛው 40 ጊዜ በላይ ይጥራሉ:: እያንዳንዱ አማኝ እግዚአብሔር የሰጠውን መንፈሳዊ ስጦታ መጠቀምና እርስ በርስ ማገልገል ይጠበቅበታል:: እነርሱ ቤተሰብ ናቸው፣ ድርጅት አይደሉም፤ ወይም የክርስቶስ አካል ናቸው እንጂ የሥልጣን መዋቅር ያላቸው ቤተ እምነቶች አይደሉም የሚለው እውነታ ቤተ ክርስቲያን እንዴት ነበር ልትመራ የተገባት፣ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን ተግባርዋን ልትፈጽም የተገባት እንዴት ነበር በሚለው ላይ ታላቅ ተጽዕኖን አሳድሮአል:: ይሁን እንጂ፣ የኢየሱስ አርአያነት ያለውን የአገልጋይነት አመራር የተመለከቱት ሐዋርያት በሞቱ ጊዜ፣ ነገሮች ጀመሩ:: ምንም እንኳ የሮማ መንግሥትን ስደት የተጋፈጡ ቢሆንም፣ አዳዲሶቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሌሎች ሃይማኖቶች እንዴት እራሳቸውን እንዳዋቀሩ፣ በተለይም ደግሞ የሮማ መንግሥት እንዴት እንደ ተዋቀረ መመልከት ጀመሩ:: ከዚያም በቤተ ክርስቲያኖቻቸው ውስጥ ታላላቅ አስተዳደራዊ መዋቅሮችን ማነሣሣት ጀመሩ:: በጊዜ



ውስጥም ቤተ ክርስቲያንን ጠንካራ ወደ ሆነ የተወሳሰበ መዋቅር ለማደራጀት የሆነው ይህ መስህብ እያደገ መጣ፣ እንዲሁም በውጤቱ በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ረገድ ለውጦች ተደርገው ነበር::

መነሻው ከተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት የሆኑ ክርስቲያኖች በተለያዩ መንገዶች በመላው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደሮችን ተመልክተዋል:: ደስ የሚለው፣ ለቤተ ክርስቲያናቸው የአስተዳደር ሥልት ፍንጮችን ለማግኘት አዲስ ኪዳንን መመልከታቸው ነው:: ምን ዓይነት ቤተ ክርስቲያን እየገነባን ነው፣ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን ምን ዓይነት የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርን ለመከተል መወሰን አለባት:: ምን ዓይነት የቤተ ክርስቲያን አመራር ምርጥ ነው ብለን እናስባለን:: በዚህ ጥናት መምሪያ ጸሐፊ አመለካከት አዲስ ኪዳን በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ላይ የተቀናጀ መዋቅርን አስመልክቶ የሚያመለክተን ትንሽ ማስረጃዎችን ነው:: የትኛዋም ቤተ ክርስቲያን፣ በመጀመሪያ የተቋቋመችው የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን እንኳ፣ በሌላ አካባቢ ያሉ አብያተ ክርስቲያናትን ለማስተዳደር አልሞከረችም:: ሐዋርያትም ደግሞ የነበራቸውን ተጽዕኖ የቤተ ክርስቲያን ንጹሕ ትምህርቶች ምን እንደ ሆኑ ሰዎች እንዲረዱ ለመርዳት በተቀዳሚነት የተጠቀሙበት ይመስላል፤ በስፍራ ሁሉ የተተከሉ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን ለማስተዳደር አይደለም:: ክርስቲያን ማለት ምን ማለት ስለ መሆኑ ለማስተማር ካልሆነ በቀር ሐዋርያት፣ የገዛ እራሳቸውን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እንዲመሩ ለእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ሙሉ ሥልጣን የሰጡ ይመስላል:: በየትኛውም አውራጃ ኅብረትን የመሠረቱበት፣ ወይም የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ላይ አስተዳደራዊ ሥልጣንን ለመመሥረት የሻተችበት ምንም አመልካች ፍንጭ የለም::

30ኛ ጥያቄ:- ሀ) የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደ ተዋቀረች እንዲሁም እያንዳንዱ የሥልጣን ደረጃን ኃይል ከቤተ ክርስቲያናችሁ አወቃቀር ጋር አመሳክር:: የሚመሳሰሉበትና የሚለያዩት እንዴት ነው? ለ) ከደርግ መንግሥት በፊት በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የቤተ ክርስቲያን መሪ ከነበረ ሰው ጋር ተነጋገር:: በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ

እንዲህ ያለ ሰው ከሌለ፣ በሌላ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካለ የሽመግለ እማኝ ጋር ተነጋገር:: ባለፉት 25-30 ዓመታት ጊዜ ውስጥ የቤተ ክርስቲያን የአመራር መዋቅርና በእያንዳንዱ ደረጃ ያለ የመሪዎች ሥልጣን እንዴት እንደ ተለወጠ ጠይቀው/ጠይቃት:: ሐ) ከመንግሥት የአመራር መዋቅር ጋር ግንኙነት ያለው ነገር ትመለከታለህን? ደግሞስ በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ እየተከሰተ ያለው ምንድን ነው? ይህ ከሆነ፣ የምትመለከታቸውን መመሳሰሎችና ልዩነቶች ዘርዝር:: መ) ቤተ ክርስቲያናችሁ በተዋቀረችበትና ሰዎች መሪዎችን በሚመለከቱበት ረገድ የምታያቸውን ብርቱ ጐኖችና እደጋዎች ዘርዝር::

1. በመላው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ አመራር በሦስት የቤተ ክርስቲያን መዋቅሮች ዙሪያ ብቻ ተዋቅሮአል::

ሀ) በቤተ ክርስቲያን ላይ «መንፈሳዊ ንጉሥ» በሆነው ሊቀ ጳጳስ ወይም ፖፕ ተብሎ በሚጠራው ግለሰብ የሚደረግ የቤተ ክርስቲያን አመራር ነው::

ከሐዋርያት ሞት በፊት፣ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት «ጳጳሳት» ወይም «ኤጲስ ቆጶሳት» ተብለው ጭምር በሚጠሩት በሽማግሌዎች ይተዳደሩ ነበር:: በመጀመሪያ ሁሉም ሽማግሌዎች ጳጳሳት ተብለው ተጠርተዋል:: ደግሞም ጳጳሳት ሽማግሌዎች በመባል ይጠሩ ነበር:: ነገር ግን፣ በመጀመሪያው ምእተ ዓመት መጨረሻ ላይ፣ ነገሮች መለወጥ ጀመሩ:: ሐዋርያቱ ከሞቱ በኋላ፣ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በሽማግሌዎች የሚመሩበት ተቀይሮ ግለሰቦች በቤተ ክርስቲያን ላይ መንፈሳዊ «ንጉሦች» ሆኑ:: ከ100 ዓ.ም እስከ 1517 ዓ.ም ድረስ እየጨመረ በመሄድ በክርስትናው ዓለም በካቶሊኮችና በፕሮቴስታንቶች መካከል መከፋፈል በነበረበት ጊዜ፣ በብዙ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖች ላይ በሚሠለጥን አንድ ግለሰብ ቤተ ክርስቲያን ትመራ ነበር:: ይህ ለውጥ በአራት ደረጃ ዎች የተከናወነ ነበር::

(1) ከሽማግሌዎች አንዱ እንደ መሪ ሽማግሌ ይመረጥ፣ ከዚያም «ጳጳስ» ይባል ነበር:: ከ100 ዓ.ም በኋላ፣ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት በጣም ተሰጥኦ ያለውና በኃይል የሚከበር መሪ የቤተ ክርስቲያን ቋሚ መሪ ይደረግና ጳጳስ የሚል መጠሪያም



ይሰጠው ነበር:: አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ሽማግሌዎቹ በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ ማተኮር ይጀምራሉ:: እንዲሁም ጳጳሱ ቤተ ክርስቲያንን በመምራት፣ የቅዱስ ጥምቀትንና የጌታን ራት አገልግሎት በመስጠት ያገለግላል ሲሉ ያምናሉ::

(2) የተከበሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በማኅበረሰባቸው ውስጥ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን በመንፈሳዊ ረገድ የመቆጣጠር ኃላፊነት ይሰጣቸው ነበር:: በአብያተ ክርስቲያናት ላይ አስተ ዳደራዊ ቍጥጥር የማድረግ ሥልጣን አልነበራቸውም:: ነገር ግን የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ሽማግሌዎች «እረኞች» ነበሩ፣ ለእነርሱ እጅግ በጣም አስቸጋሪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ፣ በተለይም አስተምህሮን በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ፣ ያማክሩዋቸው ነበር:: ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ አምላክ ነው ወይስ አይደለም፣ እንዲሁም ሙሉ በሙሉ ሰው ነው ወይስ አይደለም የሚሉ ጥያቄዎች በሚነሡበት ጊዜና የሐሰት ትምህርቶች በሚሠራጩበት ጊዜ፣ እነዚህ ግለሰቦች ጉዳዩን ለማጥናት ይሰበሰቡና ትክክለኛ የሆነውን ነገር ይወስኑ ነበር:: እነርሱም የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ያስተምራሉ፣ ከዚያም የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ሕዝቡን የቱ እውነት እንደ ሆነ፣ እንዲሁም ለስሕተት ትምህርቶች እንዴት መልስ መስጠት እንዳለባቸው ያስተምሩዋቸው ነበር:: አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ሐዋርያው ዮሐንስ በትንሿ እስያ እንዲህ ያለውን ሚና ይጫወት ነበር ሲሉ ያስባሉ:: በኤፌሶን እየኖ ረ፣ በትንሿ እስያ ያሉ የሌሎች አብያተ ክርስቲያናት መንፈሳዊ አማካሪ ነበር:: ለዚያም ነው በትንሿ እስያ ለነበሩ ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ደብዳቤዎችን እንዲልክ እግዚአብሔር የተጠቀመበት:: ነገር ግን፣ በየትኞቹም የአዲስ ኪዳን ደብዳቤዎች ውስጥ በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ላይ የሚሠለጥን ቋሚ የሆነ መንፈሳዊም ሆነ አስተዳደራዊ መሪ ስለ መኖሩ ጠቋሚ ነገር የለም::

(3) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መልክዓ ምድራዊ አመራር ቋሚ የሆነ ሚና ሆነ:: ስለዚህም ደግሞ በኢየሩሳሌም፣ ሌላው በኤፌሶን፣ እንዲሁም ሌላው በሮም የሚቀመጡ ጳጳሳት ነበሩ:: ቀስ በቀስም የጳጳሱ ሚና መንፈሳዊ አማካሪ ከመሆን ወደ አስተዳዳሪነት ተ

ሰወጡ። ይህ አስተዳዳሪም ከአውራጃ ገዢ አስተዳደር ጋር ተ መሳሳይ የሆነ ነበር።

(4) ከጳጳሳቱ አንዱ በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ላይ መሪ የሆነ ጳጳስ እንዲሆን ይመረጥ ነበር። ያ ጳጳስ በሮማ ግዛት ዋና ከተማ በሮም ይኖር ነበር። ወዲያውም እርሱ «ፖፕ» ወይም ራስ የሆነ ጳጳስ ይባል ነበር። ቤተ ክርስቲያን ይህ ልዩ የሆነ ጳጳስ «የመንግሥቱን ቍልፍ» ለመያዝ የጴጥሮስን ሥልጣን ወርሷል (ማቴ. 16:18-19) በማለት ማስተማር ጀመረች። ስለዚህ፣ በክርስትናው ሁሉ ላይ ፍጹም የሆነ ነገርን መናገር ይቻል ነበር። እርሱን የሚያማክሩት ጳጳሳት ሊኖሩት ይችላሉ፣ ነገር ግን የእርሱ ቃል ሕግ ነው። እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን የእርሱን ትእዛዛት መከተላቸውን ማረጋገጥ የጳጳሳትና የካህናት ሚና ነበር። ልክ በመላዋ የሮም ግዛት ሙሉ ሥልጣን እንዳለው የሮማ ንጉሠ ነገሥት፣ በክርስትናው ላይ የሚገዛ መንፈሳዊ ንጉሥ አለ። በዚያ ዘመን የነበሩ አማኞች ከንጉሥ አገዛዝ ጋር በጣም የሚተዋወቁ ስለ ነበሩ፣ በዚህ የአመራር ዓይነት ደስተኞች እንደ ነበሩ ጥርጥር የለውም።

ይህን የተወሳሰበ የሥልጣን ደረጃ የሚያስተዋውቁ ሰዎች የኢየሱስን ትምህርት ሊያብራሩ የሚስማ አንድ ሰው ይገረማል። (ማር. 10:41-45 እና ማቴ. 23:1-12 ተመልከት።) ኢየሱስ በመምራት ረገድ ሥልጣንን መጠቀምን በመቃወም እንዲሁም የአመራር ማዕረግን ስላለመቀበል በግልጥ አስተምሯል።

በመላው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ አብያተ ክርስቲያናት ይህን ዓይነት የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር መርጠው ነበር። ይሁን እንጂ፣ ለጳጳሳት የተሰጠው ሥልጣን ከአንድ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሌላው ይለያያል። እጅግ ትልቅ ሥልጣን የነበራቸው መሪዎች በሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እና በኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚገኙ ነበሩ። እነዚህ ቤተ እምነቶች እግዚአብሔር ስቤተ ክርስቲያን በመዋቅሩ ውስጥ፣ በመጀመሪያ ለሊቀ ጳጳሱ፣ ከእርሱም ለጳጳሳቱ፣ በመጨረሻም ለካህናቱ ሥልጣንን ሰጥቷል ሊሉ ያስተምራሉ። ሥልጣን በቤተ ክርስቲያን



ውስጥ ማዕከላዊ ከሆነው ግለሰብ፣ ሊቀ ጳጳሱ ወይም ርእሳነ ሊቃነ ጳጳሳቱ ወደ ጳጳሳት ከዚያም ወደ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ካህናት ይፈስሳል። እያንዳንዱ የአመራር ደረጃ ከበላዩ ላለው አመራር ኀላፊነት/ተጠያቂነት አለበት። ስለዚህም ደግሞ፣ ክልላዊ አመራር ላይ ያሉ ጳጳሳት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ካህናትን ይሾሙም ሆነ ያስወግዱ ነበር። ደግሞም ማዕከላዊው መሪ፣ ሊቀ ጳጳሱ ወይም ርእሳነ ሊቃነ ጳጳሳቱ ክልላዊ ጳጳሳትን፣ ወዘተ . . . ይሾማል።

በ1600፣ እንግሊዝ ውስጥ፣ ከሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተ ገንጥሎ የወጣ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተ። እርሱም አንግሊካን ወይም ኤጲስኮፓል ቤተ ክርስቲያን ተብሎ ተጠራ። እርሱም እንደዚሁ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ካህናትን ለመቆጣጠርና ለመጐብኘት የሚያስችል መዋቅር አለው። ይሁን እንጂ፣ ለእነዚህ ጳጳሳት እንዲሁም «ርእሳነ ሊቀ ጳጳሳት» ተብሎ ለሚጠራው ዋና ጳጳስ የተሰጣቸው የሥልጣን መጠን በሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ካሉ መሪዎች ያነሰ ነው፡ ጳጳሳት ለቤተ ክርስቲያን ጥቂት መንፈሳዊ ሥልጣንን ይሰጣሉ፣ የቤተ ክርስቲያን ካህናትንና ጳጳሳትን አመራረጥ ይታዘባሉ። ነገር ግን፣ የገዛ አራሳቸውን ጉዳዮች ለማስተዳደር የአንግሊካን አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የበለጠ ሥልጣን አላቸው።

እንዲህ ያለው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር እንዴት እንደ ተ ጀመረ አራት ትምህርቶችን ልንማር እንችላለን፦

1) ብዙዎቹ መዋቅሮች እና እመለካከቶች ከመልካም ምክንያቶች ይጀምራሉ፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር መንግሥትን ውጤታማ ከመሆን ወደሚገድቡበት ስፍራ ያድጋሉ። ዝቅተኛ ክህሎት ወይም ዝቅተኛ ሥልጠና ላላቸው ሽማግሌዎች አማካሪ የሚሆኑ የእግዚአብሔር ሰዎች መኖራቸው መልካም ነው። ነገር ግን፣ ይህ አቋም አንድ ጊዜ ከተመሠረተ በኋላ፣ በመጨረሻ ጳጳሳቱና ሊቃነ ጳጳሳቱ እንደ ነገሥታት እስኪሆኑ ድረስ፣ ይህ አሠራር በሥልጣን ማደጉን ይጀምራል። በመካከለኛው ዘመን፣ የሕዝቦችን ነገሥታት ከሥልጣን እስከ ማውረድ ድረስ የሊቃነ

ጳጳሳቱ ሥልጣን እጅግ አድጎ ነበር:: «ሥልጣን ፈር ይለቅቃል፣ ፍጹም የሆነ ሥልጣን፣ ፍጹም በሆነ መልኩ ፈር ይለቅቃል::» የሚለው በእንግሊዝኛ የተለመደ አባባል ነው:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድ ግለሰብ የበለጠ ሥልጣን በያዘ መጠን (በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፣ ወይም በክልል፣ ወይም በቤተ እምነት ደረጃ)፣ ብዙዎቹ መሪዎች ሥልጣናቸውን በተሳሳተ መንገድ የበለጠ የሚጠቀሙ ይሆናሉ:: አመራር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ፖለቲካዊ ሆነ ደግሞም በጥንቃቄ የሚጠበቅ ሆነ:: እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን አባላት ክካህኑ ወይም ክጳጳሱ ፈቃድ ውጭ ማከናወን የሚችሉት ኢምንት ነበር:: ስለዚህ፣ ለአንድ ሰው የሚሆን መልካም ሚና ወይም መልካም የሆነ መዋቅር የእግዚአብሔርን መንግሥት ወደሚገድብ ነገር እንዲያድግ ሳለመፍቀድ በጣም ጠንቃቃ መሆን ያስፈልገናል::

2) ብዙዎቹ የቤተ ክርስቲያን መዋቅሮች የተዘረጉት በመንግሥት መዋቅር መልኩ ነው:: በ300 ዓ.ም ገደማ፣ ቤተ ክርስቲያን በገሃድ ተቀባይነት ባገኘችበት ጊዜ፣ የቤተ ክርስቲያን መዋቅር ከሮማ መንግሥት መዋቅር ጋር አንድ ዓይነት ነበር:: ሊቀ ጳጳሱ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር እንዲሁም ጳጳሳቱ ክአገር (ከክልላዊ) መሪዎች ጋር የሚጐዳኙ ነበሩ:: በመጨረሻም፣ የቤተ ክርስቲያን መዋቅር ብቻ አልነበረም ከመንግሥት ጋር ተመሳሳይ የነበረው፣ ነገር ግን አመራርን በተመለከተ የነበረው ዝንባሌም ልክ እንደ መንግሥት ያለ ሆነ:: ልክ በመንግሥት ቊጥጥር ሥር ሊውሉ እንደሚገባቸው ዜጎች፣ እንዲሁ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የቤተ ክርስቲያን አባላቶቻቸውን መቆጣጠር እንደሚያስፈልጋቸው ማሰብ ጀመሩ::

3) አንድ ጊዜ በልምምድ/በተግባር አንድ ዓይነት ክሆንን፣ ምንም እንኳ የእራሳችንን ነጥብ ማስረጃ ለማረጋገጥ እየሞከርንም ቢሆን፣ የእኛን አመለካከት ለመደገፍ የእግዚአብሔርን ቃል ሁልጊዜ እንጠቀማለን:: በአዲስ ኪዳን የጴጥሮስን ሥልጣን እየወረሱ እየተፈራረቁ ይመሩ የነበሩ መሪዎች ስለ መኖራቸው የሚናገር ክፍል የለም:: (ጴጥሮስም እንኳ መላውን ክርስትና 

ለመቆጣጠር የሚሆን ሥልጣን እንደ ነበረው አልተናገረም::) ሆኖም ግን፣ የሮማ ሊቃነ ጳጳሳት በቤተ ክርስቲያን ላይ ሊኖራቸው የሚገባውን የበላይነት ለመጠበቅ፣ ሥልጣናቸውን በማስረጃ ለመደገፍ ስለ ጴጥሮስ የሚናገረውን (ማቴ. 16:18-19) ምንባብ ማጉላት ጀመሩ:: ሁላችንም ይህንኑ ወደ ማድረግ እናዘነብላለን:: ሁላችንም የእኛን ሥነ መለኮታዊ አቋም የሚደግፉ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ወደ መጠቀሙ፣ እንዲሁም እኛ ከምናምነው ጋር የማይገጥሙ ክፍሎችን ቸል ወደ ማለቱ እናዘነብላለን:: (ለምሳሌ፣ አንዳንድ ሰዎች አልኮልን በመጠጣት ረገድ ያላቸው አመለካከት በብሉይ ኪዳን ሰዎች የጠጡበትን ሁኔታ የሚያመለክቱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ብዙ ክፍሎችን በእክብሮት እንዳይዙ ሊያደርጋቸው እንመለከታለን:: ዘፍጥረት 14:18 ላይ አብርሃም ወይን የጠጣበትን፣ ዘዳግም 14:26 እግዚአብሔር ለሕዝቡ ወይን እንዴት እንደሚሰጥ ተመልከት:: ቤተ እምነታችን የአልኮል መጠጦችን እንዳይጠጡ አማኞችን የምታደፋፍር ከሆነ፣ ይህ ሊደረግ የሚገባው መጽሐፍ ቅዱስ የአልኮል መጠጦችን ይከለክላል ክማለት ይልቅ በሌሎች ምክንያቶች መሠረትነት፣ ለምሳሌ ያህል፣ ለሰዎች ማሰናከያ መሆንን ባለመፈለግ፣ የስካር ኃጢአት ውስጥ ለመውደቅ ባለመፈለግ፣ በማያምኑ ሰዎች ዘንድ ጥሩ ምስክርነት እንዲኖራቸው በመፈለግ፣ ወዘተ . . . መሆን አለበት::) ይህንን ስለ ቤተ ክርስቲያን አመራር ባለን መረዳት፣ እኛ ጠንካራ የሆነ የሚቆጣጠረን አካል እንዳለን ለማሳየት መጽሐፍ ቅዱስን በመጠቀም እንዲሁም አገልጋይ መሪዎች ስለ መሆናችን መጽሐፍ ቅዱስ የሚያተኵርበትን ቸል ባለማለት እንዳይሆን ጠንቃቆች መሆን ይኖርብናል::

4) ብዙውን ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያን ሙያተኞችን እንደ ልዩ ሰዎች አድርጋ ልትመለከታቸው ወይም ልትይዛቸው ትጀምራለች፣ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚሰጣቸው የበለጠ ሥልጣን ትሰጣቸዋለች:: የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን እንደ ጳጳሳት እና ካህናት ያሉ አገልጋዮችን ሚና ብቻቸውን እንዲሰብኩ፣ እንዲያስተምሩ፣ እንዲያጠምቁ፣ የጌታን እራት እንዲያድሉ

እንዲሁም ኃጢአትን ይቅር እንዲሉ እስከሚችሉበት ነጥብ ድረስ እንዲያድግ ፈቅዳለች። ወዲያውም ደግሞ ተራ የቤተ ክርስቲያን አባላት ለአምልኮ ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመምጣትና ገንዘብ ከመስጠት በስተቀር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምንም ሚና የሌላቸው መሆናቸውን ማሰብ ጀመሩ። ከዚያም ጀምሮ አንዱ የተሰየ ሌላው ደግሞ ተራ በሚል በቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና በቤተ ክርስቲያን አባላት መካከል ክፍተት እየጐለበተ መጣ። በተመሳሳይ መንገድ፣ ጠንቃቃ ካልሆንን፣ ዛሬ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የሆኑት (ማለትም፣ በሥነ መለኮት የሠለጠኑ ሰዎች) ከተራው የቤተ ክርስቲያን ይልቅ እነርሱ የተለዩና የተሻሉ እንደ ሆኑ አድርገው መመልከት ሊጀምሩ ይችላሉ። የቤተ ክርስቲያን አባላት ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊያገለግሉ የሚገባቸው ካህናት ናቸው የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ገና ተግባራዊ አላደረግነውም።

አመራርና አገልግሎት ልክ እንደ ካህናትና ጳጳሳት ባሉ በቤተ ክርስቲያን ሙያተኞች መሪዎች እጅ ውስጥ በሚከማችበት ጊዜ፣ ተራው የቤተ ክርስቲያን አባል ማገልገል አይችልም፣ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች ላይ ሊናገር የሚችለው ትንሽ ነው። «የምደባ» ሂደት ይጀመራል። ይህም ማለት የእግዚአብሔርን ቃል መደበኛ በሆነ መልኩ ያጠኑት ሰዎች ብቻ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ካህናት እንዲሆኑ ይፈቀድላቸዋል። የጳጳሳት አንዱ ዋነኛው አገልግሎታቸው አንድ ሰው ካህን ለመሆን በቂ መሆኑን ማረጋገጥ፣ ከዚያም በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ላይ እርሱን መሾም ነው። መመዘኛዎቹን ሁሉ ያሰፉ በጳጳሳት የተሾሙትና ሥልጣን የተሰጣቸው ሰዎች ብቻ ናቸው በቤተ ክርስቲያን እንዲያስተምሩ፣ የጌታን እራት አገልግሎት እንዲሰጡ፣ ሰዎችን እንዲያጠምቁ የሚፈቀድላቸው፤ ደግሞም ኃጢአትን ይቅር ለማለት ሥልጣን ያላቸው። የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን እየጐለበተች በሄደች ጊዜ፣ ለእነዚህ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ካህናት አንድ ሰው ይድን ወይም ተኰንነው ወደ ገሃነም ለመሄድ ይወስኑ ዘንድ እንኳ ሥልጣን ሰጠቻቸው። አንዳንድ ካህናት የተበላሹ ሆኑ፣ ደግሞም ሰዎች ትልቅ ስጦታ ከሰጡ፣ በኃጢአት ሕይወታቸው የቀጠሉ



ቢሆንም እንኳ፣ እነዚያ ግለሰቦች ዘላለማዊ ሕይወት አላቸው በማለት ያውጃሉ። ታማኝ ያልሆኑና ቅዱስ ለመሆን ምንም ፍላጎት የሌላቸው አንዳንድ ነጋዴዎች፣ በሕይወታቸው መጨረሻ ላይ የዘላለማዊ ሕይወት ዋስትናን ለማግኘት ትልቅ ስጦታ ይሰጣሉ። ማርቲን ሉተር የተባለው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ካህን፣ የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ለመቃወም የጀመረው፣ ደግሞም የተሐድሶ እንቅስቃሴ የጀመረው፣ በውጤቱም የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት የተመሠረቱበት በዚህ ካህናት ሥልጣናቸውን አላግባብ በሚጠቀሙበት ሁኔታ ነው።

እኛም እንደዚሁ ወደ እነዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የተሳሳተ መረዳት ልንወድቅ እንችላለን። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ሥራዎችን ሁሉ እንዲያከናውኑ ወንጌላውያንና መጋቢያንን መቅጠር ለቤተ ክርስቲያን ቀላል ነው። ወዲያውም፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡት ለአምልኮና ሥራውን ለሚሠሩ ሰዎች ገንዘብ ለመስጠት ነው የሚለው አሳብ እየጐለበተ ይሄዳል። ደግሞም ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማገልገል ብቁ አይደለንም የሚል አሳብ ያገኛቸዋል። ወይም የእሑድ የቤተ ክርስቲያን አባላት እንዲዘምሩና እንዲያገለግሉ ከመፍቀድ በኅብረ መዘምራን ዝማሬ ላይ እና በሥነ መለኮት በሠለጠኑ ጥቂት ሰዎች ስብከት ላይ ማተኮር ይጀምራል።

> 31ኛ ጥያቄ:- ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ እነዚህ አራት የአሠራር ልማዶችን እንዴት እንደ ተመለከተካቸው ዘርዝር። ለ) እንዲህ ያለው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር መዋቅር ኢየሱስ ስለ አመራር ካስተማረው ጋር ወደ ተለየ አመራር አስተሳሰብ እንዴት ሊመራ እንደሚችል ግለጥ።

ሰ. «ሽማግሌዎች» በሚል አካል የሚደረግ አመራር።

የፕሮቴስታንት የተሐድሶ እንቅስቃሴ በ1517 በጀርመን ከመጀመሩ ብዙም ሳይርቅ፣ ከስዊዘርላንድ የሆነ ጆን ካልቪን የተባለ ሰው እግዚአብሔር የመሠረተው የአመራር መዋቅር ቤተ ክርስቲያንን የሽማግሌዎች ቡድን ያስተዳድራት የሚል ነው ሲል ወሰነ። ሥልጣንን ልክ ሊቀ ጳጳሳት ወይም ጳጳስ ለሆነ ለአንድ ሰው ከመስጠት ይልቅ፣ ሥልጣን በቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች በጋራ

ይያዛል። ስለዚህም፣ የቤተ ክርስቲያኑን የአመራር መዋቅር ለወጠው። የተለያዩ ደረጃዎች ያሉዋቸው የሽማግሌዎች ቡድኖች ነበሩ። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንና ያስተዳደሩ ሽማግሌዎች ነበሩ። ነገር ግን፣ በመልክዐ ምድራዊ ክልላቸው ያሉ አብያተ ክርስቲያናትን ያስተዳደሩ ሽማግሌዎች ነበሩ። ደግሞም በዚያ ቤተ እምነት ውስጥ ያሉ አብያተ ክርስቲያናትን ሁሉ የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎችም ጭምር ነበሩ። በኢትዮጵያ ውስጥ ይህ ቤተ ክርስቲያን ቤቴል ሲኖዶስ መካነ ኢየሱስ በመባል ይጠራል፣ ነገር ግን በሌሎች አገሮች ይህ ቤተ እምነት ፕሪስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን በመባል ይጠራል።

ይህ የአመራር ስልት ለዊዘርላንዳዊው አመራርን በተረዳበት መንገድ ተጽዕኖ ያደረበት ነበር። በዚያን ጊዜ የስዊዘርላንድ መንግሥት በከፊል ነፃ በሆኑ መልክዓ ምድራዊ ክልሎች የተከፋፈለ ነበር። እያንዳንዱ መልክዓ ምድራዊ ክልል በክልሉ ያሉ ጉዳዮችን ለማስተዳደር «ሸንጎ» ነበረው። እነዚህ ሸንጎዎች ለብሔራዊው የአስተዳደር አካል ተወካዮችን ይልኩ ነበር። ደግሞም ለሕዝባቸው ለክልላቸው ጥቅም በሚወስዱ ውሳኔዎች ላይ ተጽዕኖዎቻቸውን ያሳርፋሉ። «ሽማግሌዎች» ስልትን የሚከተል የቤተ ክርስቲያን አመራር በዚህ የስዊዘርላንድ አስተዳደራዊ ስልት ላይ የተመረኮዘ ነበር።

በዚህ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ዓይነት መሠረት፣ እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን የእራሱን ሽማግሌዎች የመምረጥ ኃላፊነት አለበት። ይሁን እንጂ፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት ሽማግሌዎችን እየመረጡ እንደ ሆነ አያምኑም። ይልቁንም፣ የእነርሱ ሽማግሌ እንዲሆን እግዚአብሔር የመረጠውን ሰው እንደ ተቀበለ ያስታውቃሉ። ስለዚህ፣ ማን ለሽማግሌነት መንፈሳዊ የሆኑ ማስረጃዎች እንደ ታዩበት፣ እንዲሁም ሽማግሌ ለመሆን የመንፈስ ቅዱስን ጥሪ በሚገልጥ መንገድ ቀድሞውኑ ያገለገለ መሆኑን በሰዎች ሕይወት ውስጥ ልብ ብሎ መመልከት የማኅበረ ምእመኑ ኃላፊነት ነው። ሽማግሌ በሚመረጥበት ጊዜ፣ በቤተ ክርስቲያን ላይ ሽማግሌ እንዲሆን መንፈስ ቅዱስ እንደ ጠራው ያረጋግጣሉ።



የሽማግሌዎች ቡድን ኢየሱስ በግለሰብ ላይ ሳይሆን፣ በቤተ ክርስቲያን ሥልጣን ላይ «የበላይ» እንደ ሆነ ይገነዘባሉ። በመንፈስ እንደ በሰሉ ሰዎች፣ የሽማግሌዎች ኀላፊነት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅና በዚያ ተግባር ላይ የቤተ ክርስቲያን አባላትን መምራት ነው። ሁሉም አማኞች የሚመራቸው መንፈስ ቅዱስ ያላቸው በመሆኑ፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት በአንዳንድ ውሳኔዎች ላይ አስተዋጽኦ ማድረግ ይችላሉ። ነገር ግን፣ ለማኅበረ ምእመኑ አመራር ለመስጠት ሽማግሌዎች በቡድን ኀላፊነት አለባቸው። የራሳቸውን መልክዓ ምድራዊ (ክልላዊ ጉዳዮች የሚያስተዳድሩ የተለያዩ የሽምግልና ደረጃዎችም አሉ።

እንዲህ ያለው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር እየጐለበተ በሄደ ጊዜ፣ በገዛ እራሳቸው ሥራ የተጠመዱ ሽማግሌዎች በቂ በሆነ መልኩ ለማስተማርና የእረኝነት አገልግሎት ለመስጠት በአብዛኛው በቂ ጊዜ እንደ ሌላቸው ቤተ ክርስቲያን ተመለከተች። ስለዚህ፣ «የአስተማሪ ሽማግሌ» ወይም የመጋቢ አገልግሎት መደብ እየጐለበተ ሄደ። መጋቢው ከሽማግሌዎቹ አንዱ ነው። ነገር ግን፣ ሙሉ ጊዜውን በመውሰድ ያስተምርና የእረኝነት ሥራን ማከናወን ይችል ዘንድ፣ ደመወዝ ይሰጠው ነበር። የመጋቢው አገልግሎትም ሆነ ሥልጣን ከሌሎቹ ሽማግሌዎች እኩል ነበር። ይሁንና፣ ሙሉ ጊዜውን በመስጠት የሚያገለግለውን አስተማሪ ሽማግሌ፣ ሁሉም ሽማግሌዎች በማስተማርና በእረኝነት ተግባር ሊረዱት ይገባል።

በኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ ቤተ እምነቶች የዚህን አመራር ስልት ለእራሳቸው እንደሚመች በማድረግ ወስደውታል። በአሁኑ ጊዜ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን በእያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሽማግሌዎች በበላይነት በሚያስተዳድሩበት፣ እንዲሁም ደግሞ ለእያንዳንዱ አስተዳደር የተለያዩ የሽማግሌ ደረጃዎች ያሉትን የፕሪስቢቴሪያን ዓይነት አስተዳደር ይዛለች። ይሁን እንጂ፣ በቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንና በፕሪስቢቴሪያን መዋቅር መካከል ያለው ትልቁ ልዩነት፣ በቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን እንደ ግለሰብ በሙሉ ጊዜ አገልጋይነት ሙሉ ጊዜውን ለማስተማርና ለሕዝቡ እረኛ ለመሆን የተመደበበት «አስተማሪ ሽማግሌ»

የሚል የአገልግሎት ምድብ አለመኖሩ ነው:: በዚህ ፈንታ፣ ለቤተ ክርስቲያን አባላት፣ ሽማግሌዎች ወይም ጉብኚ አስተማሪዎች የማስተማር አገልግሎትን ይሰጣሉ:: ወይም በአንዳንድ ሁኔታዎች የማስተማር እና የመመስከር ተግባርን ለማከናወን ሰዎች (ለምሳሌ ም፣ ወንጌላውያን) ይቀጠራሉ፣ እንዲሁም ሽማግሌዎች የበለጠ አስተዳደራዊ በሆኑ ነገሮች ላይ ያተኩራሉ::

ይህ ሽማግሌ - መር የሆነ ቤተ ክርስቲያን አመራር አዲስ ኪዳን ከሚያስተምረው ጋር የበለጠ አብሮ የሚሄድ ይመስላል:: ነገር ግን፣ ጥንቃቄ በሞላበት ሁኔታ ሲዳሰሱ የሚገባቸው ሦስት አደጋዎች በዚህ የአሠራር ዘዴ ውስጥ አሉ::

በመጀመሪያ፣ ምንም እንኳ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ላይ የሚሠለጥኑ ሽማግሌዎች መኖራቸውን አስመልክቶ ብዙ ማስረጃዎች ቢኖሩም፣ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ቁጥጥር የሚያደርጉ የተሰያዩ የሽማግሌ ቡድኖች ስለ መኖራቸው በአዲስ ኪዳን ምንም ማስረጃ የለም:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ የአውራጃ፣ የዞን እና ብሔራዊ የሽማግሌዎች ቡድን የለም:: ስለዚህ፣ ቤተ ክርስቲያን የሽማግሌዎች ቡድን ደረጃዎችን በምትመሠርትበት ጊዜ፣ አዲስ ኪዳን ከሚፈቅደው በላይ እየተጓዘች ነው፣ ደግሞም ይህ የሆነው ቤተ ክርስቲያን የዓለምን መንግሥት የአሠራር ስልት በመከተሏ ብቻ ነው ሲሉ አንዳንዶች ይከራከራሉ::

ሁለተኛ፣ በእያንዳንዱ ግለሰብ የሆነ ክርስቲያን ላይ አመራርን መስጠት ያለባቸው እነርሱ እንደ ሆኑ ሽማግሌዎች የሚያስቡ ከሆኑ፣ ወዲያውኑ እነርሱን ከማገልገል ይልቅ፣ በቤተ ክርስቲያን ላይ በሥልጣን የመግዛት ውድቀት ውስጥ ይገባሉ ሲሉ የሚፈሩ አንዳንድ ክርስቲያኖች አሉ:: ግለሰብ የሆኑ አማኞችን የመስማት ነገራቸው እየቀነሰ ይሄዳል:: ይልቁንም፣ ጉዳዮችን በሽማግሌዎች መካከል የሚወያዩና በቤተ ክርስቲያንም ምትክ ውሳኔዎችን የሚያሳልፉ ይሆናሉ:: እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን አባላት አስተ ዋጽኦ ትንሽ ይሆናል:: ይህም እያንዳንዱ አማኝ መንፈስ ቅዱስ ያለው መሆኑን፣ እንዲሁም በአማኞች ፈንታ ውሳኔን የሚያስተ



ላልፉትን የሽማግሌዎች ቡድኖች ላይ ከማተኮር ይልቅ ኢየሱስን ለመስማት ኀላፊነት ያለበት የመሆኑን እውነት ቸል ይላል::

ሦስተኛ፣ በእግዚአብሔር ቃል የሠለጠነ የሙሉ ጊዜ አስተማሪ ሽማግሌ በማይኖርበት ጊዜ፣ ደግሞም የእግዚአብሔርን መንጋ በቅርበት የሚጠብቅ ሰው በማይኖርበት ጊዜ፣ ብዙዎቹ የቤተ ክርስቲያን አባላት በመንፈሳዊ ብስለት ደግሞም ጥልቀት ባለው የእግዚአብሔር ቃል እውቀት አያድጉም::

> 32ኛ ጥያቄ:- ሀ) ከዚህ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ስልት ስለ ቤተ ክርስቲያን አመራር ምን ትምህርት ተማርህ? ለ) የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንን የአመራር ዓይነት ከፕሪስቢቴሪያን የቤተ ክርስቲያን አመራር ጋር አወዳድር:: ከአዲስ ኪዳኑ ናሙና ጋር የተቀራረበው የትኛው እንደ ሆነ ታስባለህ? የእያንዳንዳቸውን የአመራር ስልት ደካማና ብርቱ ነጥቦች ግለጥ::

ሐ. ማኅበረ ምእመናዊ አስተዳደር:-

ጆን ካልቪን የፕሪስቢቴሪያን የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ስልትን ከማጉልበቱ ብዙም ሳይቆይ፣ በተለያዩ የሽማግሌዎች ደረጃ የሚደረገው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር አሁንም በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ካሉ አማኞች ውጭ ሥልጣንን ወደ ማድረግ ያዘነብላል ብለው የሚያምኑ ሌሎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ ሦስተኛ ዓይነቱን የቤተ ክርስቲያን አመራር አጐለበቱ:: እነዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አዲስ ኪዳን ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውጭ ምንም ዓይነት የቤተ ክርስቲያን ሥልጣንን አያሳይም አሉ:: ደግሞም መላው የአማኞች ቡድን የቤተ ክርስቲያንን ሁሉንም ጠቃሚ ውሳኔዎች ወስነዋል አሉ:: በአስቆሮቱ ይሁዳ ፈንታ ምትክን የመረጡት የቤተ ክርስቲያን አባላት ነበሩ (ሐዋርያት ሥራ 1:15-26):: በኋላም፣ አማኞች ሁሉ የመጀመሪያዎቹን ዲያቆናት መረጡ (ሐዋርያት ሥራ 6:5):: ኢየሱስም ሆነ ጳውሎስ፣ ሁለቱም፣ መላዋ ቤተ ክርስቲያን አንድን አባል መቅጣት እንዳለባቸው ተናገሩ (ማቴ. 18:15-17፤ 1ኛ ቆሮ. 5):: ስለዚህ፣ ቤተ ክርስቲያንን ልታደርገው ስለሚገባት ነገር፣ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በላይ የሆነ ምንም ዓይነት የሥልጣን ደረጃ ሊኖር

አይገባም:: ምን ማድረግ እንዳለባቸውና ሊያደርጉትም ስለማይገባ ነገር መወሰን ያለባቸው በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ያሉ አባላት ናቸው:: ሽማግሌዎች ቤተ ክርስቲያናቸውን በመወከል ሁሉንም ውሳኔዎች በማስተላለፍ ፈንታ፣ ሁሉንም የቤተ ክርስቲያን ዋነኛ ጉዳዮች በተመለከተ እያንዳንዱ አባል ድምፅ ሊሰጥ ይገባል:: ለምሳሌ ያህል፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት የገዛ እራሳቸውን መጋቢ ይመርጣሉ፣ አዲስ ሠራተኛን ይቀጥራሉ፣ እንዲሁም በዓመታዊ በጀትም ላይ ድምፃቸውን ይሰጣሉ::

ይህ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር መረዳት ዓለም አስተዳደርን በምትረዳበት መንገድ ተጽዕኖ ያርፍበታል:: ይህ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በመጀመሪያ በተጀመረ ጊዜ፣ ዲሞክራሲያዊ መንግሥትን በተመለከተ ይለጥ የነበረው ትምህርት ገና መጀመሩ ነበር:: ዲሞክራሲ ሕዝቡ የሚፈልጉትን ሰው በአመራር ላይ መርጠው የሚስቀምጡበት፣ እንዲሁም ለሕዝባቸው የሚፈልጉትን ሕግ የሚመርጡበት የአስተዳደር ዘይቤ ነው:: ውሳኔዎች የሚተላለፉት በብዙኀኑ ድምፅ በኩል ነው:: በተመሳሳይ መንገድ፣ በምርጫ ሂደት በኩል የቤተ ክርስቲያን አባላት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊያደርጉት የሚፈልጉትን ነገር ይወስናሉ::

የዚህ ዓይነቱ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር መጽሐፍ ቅዱስ እያንዳንዱ አማኝ «ካህን» ነው በማለት የሚያስተምረውን ያጕላል (1ኛ ጴጥ. 2:5፣ 9):: እያንዳንዱ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ወደ እግዚአብሔር መገኘት በቀጥታ መግባት ይችላል (ዕብ. 4:14-16):: ደግሞም ኢየሱስ የእያንዳንዱ አማኝ ራስ ስለሆነ፣ አማኞች ትእዛዛትን ከአንድ ሌላ ሰው ወይም በኩል ሳይሆን፣ በቀጥታ ከእርሱ ይቀበላሉ:: አመራር እንደ ካህን ወይም ጳጳስ ወይም ልክ እንደ ሽማግሌዎች ቡድን ካለ የሰዎች ስብስብ የሚመጣ ከሆነ፣ እንግዲያውስ የቤተ ክርስቲያን አባላት አመራራቸውን ከኢየሱስ በቀጥታ አልተቀበሉም ማለት ነው::

ምንም እንኳ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ልክ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ የሚያገለግሉ ወንጌላውያንን እንደ መሳክ ወይም የሥነ መለኮት ትምህርት ቤቶችን እንደ መክፈት ያሉ የጋራ ተ



ግባራትን በአንድ ላይ ሊያከናውኑ የሚችሉ ቢሆንም፣ እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በገዛ እራሱ ማኅበረ ምእመን ላይ ሙሉ የሆነ አስተዳደር ወይም ሥልጣን አለው:: ምንም እንኳ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ቤተ እምነታዊ ኅብረት ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ ቢሆኑም፣ በቤተ እምነታዊው አስተዳደር ውስጥ በተለያዩ ደረጃዎች ያሉ አመራሮች ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አሳባቸውን ብቻ ማቅረብ ይችላሉ:: በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምትክነት መወሰን አይችሉም:: በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት የሚፈለግ የጋራ ውሳኔ በሚኖርበት ጊዜ፣ ቤተ ክርስቲያን የእራሷን ወኪል በመላክ በስብሰባው ላይ እንዲገኝ ታደርጋለች:: ሁሉም ውሳኔ የሌላውን ቡድን የሚቆጣጠርን የአንድን ቡድን ፍላጎት ከማንጸባረቅ ይልቅ፣ የሰዎችን ፍላጎት ያንጸባርቅ ዘንድ የወኪሎች ቁጥር ከቤተ ክርስቲያንዋ ስፋት ጋር የተመጣጠነ መሆን አለበት:: በእንደዚህ ዓይነቶቹ አብያተ ክርስቲያናት ያለ አመራር በአብዛኛው የሚከናወነው በሕዝብ ድምፅ ነው:: ደግሞም መሪዎቹ ውስን ለሆኑ ዓመታት የሚያገለግሉ ናቸው:: የመሪው ሚና የሰዎቹን ፍላጎት በማከናወን ረገድ እገዛን ለማድረግ ነው፣ የሽማግሌዎን ፍላጎት ለመሙላት አይደለም:: ይህ መደበኛ በሆነ መልኩ እንደ ሳውዘርን ባፕቲስት (አዲስ ኪዳን መጥምቃውያን) እና ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያናት በአያሌው ጥቅም ላይ የሚውል ነው::

የዚህ አመለካከት ችግሩ፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሽማግሌዎች በአንድ የሆነ ደረጃ ያለው ሥልጣን ያላቸው ስለ መሆኑ ጠቋሚ የሆኑ ነገሮችን መያዙ ነው:: የቤተ ክርስቲያን አባሎች በሥልጣን ላይ ባሉ ሰዎች እንዲገዙ እና እንዲታዘዙ ተነግሮአቸዋል (1ኛ ተሰ. 5:12-13፤ ዕብ. 13:17):: ደግሞም መጽሐፍ ቅዱስ አብዛኞቹ ሰዎች ውሳኔዎችን በሚያሳልፉ ጊዜ፣ ምርጫቸው በአብዛኛው እራስ ወዳድ የሆነና መንፈሳዊ ያልሆነ ነው::

> 33ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ይህን የአመራር ስልት አሳይ ካሉት ከሁለቱ የአመራር ዓይነቶች ጋር አመሳክር:: ብርቱና ደካማ ጎኖቹን ዘርዝር:: ለ) ከሦስቱ ዓይነት የቤተ ክርስቲያን አመራር ውስጥ አንተ የበለጠ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ብለህ የምታስበው የቱ ነው?

## የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደራዊ መዋቅር በተመለከተ ማጠቃለያዎች

1. መጽሐፍ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያንን ለማስተዳደር የተመረጠ መንገድ መኖሩን በተመለከተ ግልጥ የሆነ ጥቆማን አይሰጠንም። ለምሳሌ ያህል፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሽማግሌዎች መኖር አለባቸው፣ ቍጥራቸውም ይህን ያህል መሆን አለበት የሚል ትእዛዛት የሉም። ነገር ግን፣ ማኅበረ ምእመናን ደግሞም ብዙ የገዛ ራሳቸውን ውሳኔዎችን ስለ ማሳለፋቸው ማስረጃዎች አሉ። በአንዳንድ ሁኔታዎች ሐዋርያት ወይም የእነርሱ መልእክተ ኞች (ጢሞቴዎስ እና ቲቶ) የበለጠ «የጳጳስና» ዓይነቱን አስተ ዳደር የሚመስል በቀጥታ የተሾሙ ሽማግሌዎች ያሉዋቸው ይመስላል። ነገር ግን፣ በሌሎች ሁኔታዎች ልክ የመጀመሪያዎቹ ዲያቆናት እንደ ተመረጡበት ባለ አኳኋን አባላት ውሳኔዎችን ያስተላልፋሉ። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች በግሪኩ ዓለም ባሉት ቤተ ክርስቲያን መሪው «ተቈጣጣሪ» ይባላል፣ ደግሞም ግሪኮቹ እንደሚጠቀሙበት ያለውን የሥራ አስኪያጅነት ተግባር ያከናውናል ሲሉ ያምናሉ። ነገር ግን በአይሁዶች ዓለም የጥንት ቤተ ክርስቲያን የምኵራቡን «የሽማግሌ» ዓይነት አስተዳደር በመቅዳት ወሰዳዋለች።

ይሁን እንጂ፣ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች በተዘረዘሩት በጥንት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ሽማግሌዎች ነበሩ ሲሉ ይከራከራሉ። ስለዚህም ደግሞ፣ ምንም እንኳ ትእዛዝ ባይሆንም፣ ይህ ተመራጭ የሆነ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ዘዴ መሆኑን እግዚአብሔር በተግባር አሳይቷል።

2. አመራርና የአመራር መዋቅሮችን በተመለከተ ሦስት መሠረታውያን እውነታዎች፡-

ሀ. ከቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር መዋቅር ይልቅ ጠቃሚ የሆነው፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አመራራቸውን በተመለከተ መሪ ዎች ያላቸው ዝንባሌ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር መዋቅር ላይ ብዙ ትኵረት/አጽንኦት የማያደርግ



መሆኑ እውነት ነው። ነገር ግን፣ መጽሐፍ ቅዱስ በመሪው ጠባያት፣ እንዲሁም አመራርን በተመለከተ ሊኖረው ስለሚገባ ዝንባሌ ብዙ አጽንኦትን ሰጥቷል። ኢየሱስ፣ ሰዎችን ለመቈጣጠር የሚጥረውን፣ ወይም መንገዳችንን ለመሄድ ኃይልንና ሥልጣንን የሚጠቀመውን፣ የዓለምን ዝንባሌ አስወግዶታል። ይልቁንም፣ አንድ ሰው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ባለው መልኩ መሪ የሚያደርገው ዝንባሌ፣ ወደ መንፈሳዊ ብስለት ያድጉ ዘንድ ሕይወቱንና ጊዜውን በመስጠት ኃላፊነቱን ሰዎችን ለማገልገል ይጠቀምበታል ወይስ አይጠቀምበትም በሚለው ላይ የሚያርፍ ነው።

ለ) ምንም እንኳ ቤተ ክርስቲያን የትኛውንም አስተዳደራዊ መዋቅር ብትይዝ፣ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኑን መገንባት የሚችል ቢሆንም፣ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መዋቅር ዓይነቶች በመሪዎች ላይ አላስፈላጊ ፈተናዎችን ያመጣሉ። አንዳንድ የአመራር መዋቅሮች የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን የአገልጋይ ዝንባሌን ይዘው ከመምራት ይመልሳቸዋል። የቤተ ክርስቲያን መሪ ዎች፣ አመራርን የሥልጣንና የኃይል ጉዳይ አድርጎ የአስተዳደር መዋቅር የዓለምን የአመራር አመለካከት የሚያጠናክር በሚሆንበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔር መሻት ከሆነው የአገልጋይነት አመራር በተ ቃራኒው እንሄዳለን።

ሁለት ጽንፎች በተለይ አደገኛ ናቸው።

የመጀመሪያው፣ መጋቢው ወይም ካህኑ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድ የተለየ ሰው ተደርጎ የሚወሰድ ከሆነ፣ ይህ አደገኛ ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪ ከሕዝቡ የተለየ የሚለብስ ከሆነ፣ በምስባኩ ላይ ለማገልገል ወይም የጌታን እራት ሥርዓት ለማከናወን እርሱ ብቻ የሚፈቀድለት ከሆነ፣ እርሱ የተለየ እንደ ሆነ፣ ደግሞም ሰዎችን ለማዘዝና ለመቈጣጠር ሥልጣን ያለው እንደ ሆነ በማሰብ ለዚያ አገልጋይ የሚመጣበት ፈተና ታላቅ ነው። እንዲህ ላለው አገልጋይ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በማገልገል ረገድ ትሑት ልብን መያዝ በጣም አስቸጋሪ ነው።

ሁለተኛ፣ በሌሳው ጽንፍም በመራመድ ቤተ ክርስቲያን አባላት የፈለጉትን እንዲያደርጉ መፍቀድም እንዲሁ አደገኛ ነው:: ለራሳቸው እንዲወስኑ ክተተዉ፣ ብዙዎች ሰዎች መንፈሳዊ ውሳኔ ዎችን የሚሳልፉበት ሁኔታ በጣም ብርቅዬ ነው:: ይልቁንም፣ የእግዚአብሔር ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በትምህርት የተ ሰጠበትን ነገር በመታዘዝ ረገድ ለማገዝ መንፈሳዊ አመራር እና ምሪት ሁልጊዜ አስፈላጊ ነው::

ሐ. በአዲስ ኪዳን እጅግ ወጥ የሆነው የቤተ ክርስቲያናት አመራር በሽማግሌዎች የሚደረግ ምሪት ሰጪነት ነው:: በአዲስ ኪዳን እንድ ጊዜ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወት የበሰሉ አባላትን የያዘችበት ደረጃ ላይ ከደረሰች፣ አባላቱ ሁልጊዜም የሽማግሌ ቡድኖች በሆኑት ይመራሉ:: እነዚህ ሽማግሌዎች:-

1) የእግዚአብሔርን ሕዝብ መሥዋዕትነት ባለበት መንገድ ለማገልገል በእግዚአብሔር መጠራታቸው ይሰማቸዋል (1ኛ ጢሞ. 3:1)::

2) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተዘረዘሩትን መመዘኛ መስፈርቶች ያሟላሉ::

3) የእነርሱ እረኞች እንደ ሆኑ አድርጎ ሕዝቡ ተቀብሏቸዋል::

4) በተቀዳሚነት መንፈሳዊ አካሄድን ናሙና በማድረግ፣ ቤተ ክርስቲያንን ከሐሰት ትምህርቶች በመጠበቅ፣ እንዲሁም መንፈሳዊ በሆነ መንገድ እንዴት መኖር እንዳለባቸው ሰዎችን በማስተማር የሚመሩ ናቸው::

እነዚህ ሽማግሌዎች በተቀዳሚነት ቤተ ክርስቲያን የምትተ ዳደርበት ቦርድ አባላት አይደሉም:: አሊያም እንደ መጋቢ ባለ ጠንካራ መሪ ሥር ያሉም አይደሉም:: ይልቁንም፣ ሽማግሌዎች ለቤተ ክርስቲያን አባላት ምሪትንና እንክብካቤን እያበረከቱ በጥልቀት፣ በአገልግሎት ውስጥ የሚሳተፉ ናቸው::

> 34ኛ ጥያቄ:- እነዚህን ሦስት እውነቶች ከልሳቸው:: ሀ) እነዚህ ሦስት እውነቶች አስፈላጊ የሆኑት ስምንድን ነው? ለ) በእነዚህ ሦስት እውነቶች



> እንዲሁም በእናንተ ቤተ ክርስቲያን እና በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ በአብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያናት የተለመደ በሆነው መካከል ያሉ አንዳንድ ልዩነቶች ምንድን ናቸው?

3. የቤተ ክርስቲያን የአመራር መዋቅርን ለመዘርጋት መሪ የሆኑ መርሖዎች:- በአንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ስልቶች ላይ ችክ ያለ አቋም መያዝ የማንችል ቢሆንም፣ አብያተ ክርስቲያናት ምን ዓይነት የአመራር መዋቅረን መምረጥ ይገባቸዋል፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መምራት የሚጠበቅባቸው እንዴት ነው የሚለውን በተ መለከተ ምሪት ሊሰጡ የሚገባቸው ጥቂት በጣም ጠቃሚ የሆኑ መሠረታውያን ነጥቦች ከአዲስ ኪዳን እንደሚገኙ እምናስሁ::

ሀ) የመሪዎች ዝንባሌ የሁሉም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሚና ማኅበረ ምእመኑን ማገልገል ነው፣ ማኅበሩን መግዛት አይደለም፣ የሚለውን የኢየሱስን ግልጽ ትምህርት ማንጸባረቅ ይርበታል:: እኔ መሪ ነኝ የሚለው ዝንባሌ፣ እኔ የምለውን ማድ ረግ አለብህ የሚለው በአዲስ ኪዳን የቤተ ክርስቲያን አመራር ግንዛቤ ውስጥ ስፍራ የለውም::

ለ) 1) አማኞች ሁሉ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ክፍል ስለሆኑና ወንድምና እኅት ስለሆኑ፣ 2) እያንዳንዳችን በውስጣችን የሚኖር መንፈስ ቅዱስ ያለን በመሆኑ፣ 3) ኢየሱስ የሁሉም አማኞች ራስ ስለሆነ፣ እንዲሁም 4) ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አባላት ካህናት በመሆናቸው ምክንያት፣ በየትኛውም የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ደረጃዎች ላይ ያሉ መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች ላይ እንዲሳተፉ የቤተ ክርስቲያን አባላት ሊፈቅዱላቸው ይገባል:: እንዲሁም የእግዚአብሔር ቃል የሚፈቅደው እስከ ሆነ ድረስ፣ እግዚአብሔር እንዲያደርጉት የሚፈልገውን ነገር እንዲያደምጡና እንዲታዘዙ ተራ አባላትን ማደፋፈር ይኖርባቸዋል:: አብዛኛውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እጅግ ቁጥጥር የሚያበዙና ወደ ፈላጭ ቆራጭነትም የሚሰወጡ፣ ሰዎችንም ምንም ነገር እንደማያውቁና ብልሃት ያለበት ውሳኔ መወሰን እንደማይችሉ

አድርገው የሚመለከቱት፣ መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ሕይወት ውስጥ እንደሚሠራ በማናምንበት ጊዜ ነው::

ሐ. በቤተ ክርስቲያን መሪዎችና በተራው የቤተ ክርስቲያን አባላት መካከል ጠንካራ ልዩነት እንዲኖር የሚያበረታታ የትኛውም የቤተ ክርስቲያን መዋቅር አደገኛ ነው:: በቤተ ክርስቲያን ሁሉም አባላት እኩል ጠቀሜታ የሚሰጡባት፣ ደግሞም ሁሉም አማኞች በውስጥዋ የሚያገለግሉባት አካል ናት ሲል አዲስ ኪዳን ከሚያስተ ምራቸው ብዙ ትምህርቶች ጋር ይቃረናል:: ቤተ ክርስቲያን በየትኛውም ጊዜ ልክ እንደ ወንጌላውያን ወይም መጋቢያን ያሉ ጥቂት ሰዎች ብቻ ሥራውን ሊሠሩ ይችላሉ፣ ደግሞም ቀሪዎቹ አባላት ተመልካቾች ናቸው ብላ በምታስብበት ጊዜ፣ ሁሉም አባላት የአካሉ አስፈላጊ ብልቶች ናቸው:: ደግሞም ሁሉም አባላት እንዳቸው ሌላውን በማገልገል የሚተጉ መሆን አለባቸው:: የሚለውን የአዲስ ኪዳን አሳብ መጣልዋ ነው (1ኛ ቆሮ. 12):: እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ከአገልጋይነት ይልቅ እንደ ገዢዎች እንደ ሆኑ እንዲያስቡ የሚያበረታታ የቤተ ክርስቲያን መዋቅር፣ ኢየሱስ ስለ መሪነት ካስተማራቸው ትምህርቶች ጋር የሚቃረን ነው፣ ደግሞም ለቤተ ክርስቲያን መሪውም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን አደገኛ ነው::

መ. በአዲስ ኪዳን ውስጥ ዋጋ የሚያስከፍል ብዙ ደረጃዎች ያሉት በጣም በከፍተኛ ደረጃ የተደራጀ የቤተ ክርስቲያን መዋቅር ስለ መኖሩ የምናገኘው ፍንጭ ኢምንት ነው:: የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የቤተ ክርስቲያን መዋቅር የበለጠ እየተወሳሰበ በሄደ መጠን፣ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እጅግ ዋጋ የሚያስከፍል፣ እንዲሁም በገዛ አራሳቸው ጉዳይ ላይ የሚወስኑ ሰዎች እያነሡ ይሄዳሉ ሲል ያስተምረናል:: ወዲያውም ይህ በቤተ ክርስቲያን አባላት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖን ያሳድራል:: በንግዱ ዓለም እንኳ ዛሬ፣ ሰዎች በሚኖሩበትና በሚሠሩበት ስፍራ ለማይኖሩና ቅርርብ የሌላቸውን መሪዎች በተመለከተ፣ በአመራር ወይም አስተዳደራዊ ውሳኔዎች በሚሰጡት ስፍራ እጅግ ብዙ ለዎችን ማለባለብ ለንግድ ሥራ ወሳኝ የሆነ ጉዳይ እንደ ሆነ መሪዎች መገንዘብ ጀምረዋል:: የቤተ



ክርስቲያን ቤተ እምነቶች በአስተዳደር ስፍራ ላይ ብዙ ሰዎችን በማስቀመጥ እና አገልግሎቶች በማዕከል ቊጥጥር ሥር እንዲውሉ የማድረግ አስቸጋሪ ቊንጮ የመሆንን ዝንባሌ ሊቋቋሙት ይገባል:: ውሳኔዎች የበለጠ በማዕከላዊ መልኩ በሚተ ላለፉበት ጊዜ፣ በአጥቢያቸው የሚገኙ ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ ጠቃሚ ናቸው ብለው በሚመለከቱዋቸው ጉዳዮች ላይ የባለቤትነት ስሜት ሲያጡ፣ የቤተ ክርስቲያን ቤተ እምነት ወዲያውኑ ትግል ውስጥ ይገባሉ::

| |
|---|
| 35ኛ ጥያቄ:- ሀ) ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ላለች ቤተ ክርስቲያን እነዚህ አራት ነጥቦች አስፈላጊ የሆነ ማስጠንቀቂያዎች ናቸው ብለህ ለምን ታስባለህ? ለ) ከሦስቱ ዋና ዋና የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ናሙናዎች መካከል ቤተ ክርስቲያናችሁ የምትከተለው የትኛውን ነው? ሐ) የአዲስ ኪዳን ትምህርቶችን ከግምት አስገብተህ ስትመለከት፣ ከሦስቱ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር አመለካከቶች አዲስ ኪዳን ስለ አመራርና ስለ ክርስቲያን ከሚናገረው ጋር የበለጠ የሚጐዳኘው የትኛው ነው? |

## አራተኛ ቀን:- ለሳምንታዊ ውይይት ለመዘጋጀት የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስ::

## ሳምንታዊ ስብሰባ

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአመራር ግንዛቤአቸው ለዱቃውያንን ሊመስሉ የሚችሉት እንዴት ነው? ለ) ፈሪ ሳውያንንስ? ሐ) የሥነ-መለኮት ሥልጠና ያገኙ መሪዎች አገልግሎትን እንደ ጸሐፍት ሊመለከቱ የሚችሉት እንዴት ነው?

2. ሀ) የኢየሱስ አመራር በቤተ ክርስቲያን አብዛኞቹ መሪዎች ከሚያከናውኑት አመራር የሚለየው እንዴት ነው? ለ) ኢየሱስ ለሰ ዎች ያለው አመለካከት ብዙውን ጊዜ መሪዎች ሰዎችን ከሚመለከቱበት የሚለየው እንዴት ነው? ሐ) የቤተ ክርስቲያን

መሪዎች የኢየሱስን ምሳሌነት እየተከተሉ ለመምራት ቢፈልጉ እንዴት የሚለወጡ ይመስልሃል?

3. ሀ) በብሉይ ኪዳንና በኢየሱስ ባሕርይ የተገለጹትን የመሪ ዎች ማዘጋጃ ትምህርቶች ዘርዝር:: ለ) ይህ ዛሬ መሪዎችን ስለ ማዘጋጀት ከምናስብበት መንገድ የሚለየው እንዴት ነው? ሐ) በብሉይ ኪዳንና በኢየሱስ ዘመን ይስጥ የነበረውን የመሪዎች ማሠልጠኛ ዘዴ ብንከተል፣ በአመራር ሥልጠና ላይ ምን ዓይነት ለውጥ ይኖራል? መ) ዛሬ ለቤተ ክርስቲያናችን የበለጠ ጠቃሚ የሚሆነው የመሪነት ሥልጠና የትኛው ነው? ለምን?

4. ሀ) በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሱትን የተለያዩ ዓይነት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዘርዝር:: ለ) እያንዳንዱ የመሪነት ዓይነት በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ዓይነት ሚና እንደ ነበረው ግለጽ:: ሐ) እነዚህ መሪዎች ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለ መኖራቸው አብራራ:: የአዲስ ኪዳን መሪዎች ካገለገሉበት ሁኔታ የዛሬዎቹ የሚለዩትና የሚመሳሰሉት እንዴት ነው? መ) ከዛሬው ዘመን ጋር ሲነጻጸር፣ በአዲስ ኪዳን ዘመን መሪ ዎች እንዴት ይሠለጥኑ እንደ ነበረ አብራራ:: በአዲስ ኪዳን ዘመን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከሠለጠኑበት መንገድ ምን እንማራለን? ሠ) ባለፉት 100 ዓመታት ውስጥ በአመራር ሥልጠና ላይ የታዩት ለውጦች ምን ምንድን ናቸው? እነዚህ ለውጦች በዛሬው የመሪዎች ሥልጠና ላይ ያስከተሏቸው አዎንታዊና አሉታዊ ገጽታዎች ምን ምንድን ናቸው? የአመራር ሥልጠናን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ ምን ማድረግ እንችላለን?

5. ሀ) ሦስቱን ዐበይት የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ዓይነቶች ዘርዝር:: ለ) ከእነዚህ መካከል የአዲስ ኪዳንን ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ይመስላል የምትለው የትኛው ነው? መልስህን አብራራ:: ሐ) የእያንዳንዱ አስተዳደር ደካማና ጠንካራ ነጥቦች ምን ምንድን ናቸው? መ) ቤተ ክርስቲያናችሁ የምትከተለው የትኛውን ዓይነት አስተዳደር ነው? ሠ) በቤተ ክርስቲያናችሁ አደረጃጀት ላይ ምን ዓይነት ለውጦች ቢደረጉ ይበጃል ትላለህ? ለምን?



6. ሀ) ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር አደገኛ ሁኔታዎች ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ ምን እንማራለን? ለ) እነዚህ ዝንባሌዎች ዛሬ በኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚታዩት እንዴት ነው? ሐ) ቤተ እምነታችሁን ገምግም:: ከአዲስ ኪዳን መርሖዎች ለማፈንገጥ የሚጥሩ አንዳንድ ዝንባሌዎች ምን ምንድን ናቸው? ቤተ ክርስቲያን በአስተዳደራዊ መዋቅሯም ሆነ በመሪዎቹ አመሰካከት ጤናማ መሆኗን የሚያሳዩ ምን ምን ምልክቶች አሉ?

7. ሀ) ኢየሱስም ሆነ ሐዋርያት ቤተ እምነትን ስመመሥረት ጥረት ያላደረጉት ለምን ይመስልሃል? ለ) ቤተ እምነትን የሚመሠርቱ አብያተ ክርስቲያናት ምን ዓይነት አዎንታዊ ነገሮችን ሊያመጡ ይችላሉ? ሐ) አብያተ ክርስቲያናት ቤተ እምነቶችን በመመሥረታቸው ምክንያት የተከሰቱት አሉታዊ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? መ) ቢሮክራሲያዊ ቤተ እምነትን ሳሰመገንባት አብያተ ክርስቲያናት እንዴት ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይችላሉ?

# ትምህርት ሃያ አንድ

## አንደኛ ቀን:-

አብዛኞቻችን ረዥም የተደራጁ የቤተ ክርስቲያን አደረጃጀት ዘዴዎች ያሏቸው አብያተ ክርስቲያናት አባላት ነን:: ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያናችንን አስተዳደራዊ መዋቅር ስመለወጥ የሚደ ረገው ጥረት አምብዛም ጠቃሚ ላይሆን ይችላል:: የቤተ ክርስቲያናችን መዋቅር በጣም መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም ብለን በማሰባችን ምክንያት ለመለወጥ በመነሣሣት ክፍፍል እንድንፈጥር የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም:: ይሁን እንጂ፣ የቤተ ክርስቲያናችን መዋቅር እግዚአብሔር የሚፈልገው ብቸኛው ዓይነት መዋቅር እንዳልሆነም ማወቅ ይኖርብናል:: እንዲህም ደግሞ በምእመናን ላይ ከፍተኛ ጫና በማድረግ ሰዎች ስለ ቤተ ክርስቲያንና የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ

ግንዛቤ እንዲይዙ የሚያደርጉ የአስተዳደራዊ መዋቅር ክፍሎች ካሉ፣ እነዚህን ነገሮች ማስተካከል ይኖርብናል። መዋቅሩ የበለጠ ተቆጣጣሪና ቢሮክራሲያዊ በመሆን የእግዚአብሔር መንፈስ ተግባሩን እንዳያከናውን የሚከላከል ከሆነ፣ ምናልባትም እግዚአብሔር ሽማግሌዎች ይህንን ችግር እንዲመለከቱ እንድታግዝ ሊጠቀምብህ ይችላል። ከሁሉም በላይ፣ እንደ ክርስቶስ አገልጋይ መሪዎች መሆናችንን ለማረጋገጥ ልባችንን መመርመር አለብን።

1ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ባለፈው ሳምንት ካካሄድነው የታሪክ ዳሰሳ ስለ አስተ ዳደራዊ መዋቅሮችና የቤተ ክርስቲያን አመራር የተማርካቸውን ነገሮች ዘርዝር። ለ) የቤተ ክርስቲያናችሁ መሪዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ አመራር ለመስጠት በሚያደርጉት ጥረት ሊያውቋቸው የሚገቧቸው የቤተ ክርስቲያን አመራርና መዋቅር እውነታዎች ምን ምንድን ናቸው?

## እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ራእይ ለማሳካት የሚያስችል ውጤታማ ድርጅት ለመመሥረት የሚያግዙ ቁልፍ እውነቶች

1. ድርጅትና አስተዳደራዊ መዋቅር የሚፈጠርበት ምክንያት ሰዎች ውጤታማ በሆነ መንገድ ተቀናጅተው የቤተ ክርስቲያኒቱን ራእይ እንዲፈጽሙ ለማስቻል ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ሊኖራቸው ይገባል የሚለው አንድ ዓይነት መዋቅር መኖሩን አያሳየንም። አዲስ ኪዳን የቀድሞዎቹ አብያተ ክርስቲያናት እርስ በርሳቸው የሚገናኙባቸው የአሠራር መንገዶች እንደ ነበሯቸው ቢናገርም፣ ያካሄዱት መደበኛ የሆነ ስምምነት አልነበረም። በእያንዳንዷ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልግሎቶችን የሚቆጣጠሩና ሕዝቡን በእረኝነት የሚያገለግሉ ሽማግሌዎች ነበሩ። በአብያተ ክርስቲያናት መካከል የነበረው ግንኙነት መደበኛ ያልሆነና አንዱ ሌላውን የማይቆጣጠርበት ነው። የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን በቆሮንቶስ ላሉት አብያተ ክርስቲያናት አስተ ዳደራዊ ሥልጣን እንደ ነበራቸው የሚያሳይ መረጃ የለም። በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ላይ መንፈሳዊና አስተምህሯዊ ሥልጣን የነበራቸው ሐዋርያት ብቻ ነበሩ፣ ይህም ሥልጣን



እነርሱ ሲሞቱና አዲስ ኪዳን ሲጻፍ አብቅቷል። አማኞች የትም ቢኖሩ የአንድ ቤተሰብ አባል መሆናቸውን ስለ ተረዱ፣ አንዱ ለሌላው ይጸልይና ይረዳዳ ነበር። አንዱ ቤተ ክርስቲያን ችግር ሲገጥመው ሌሎች ይረዱት ነበር። (ለምሳሌ፣ በመቄዶንያ የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት በኢየሩሳሌም ለነበሩት ድሆች ገንዘብ ልከው ነበር። 2ኛ ቆሮ. 8።) ይህ የተደረገው ግን በክርስቲያናዊ ፍቅር እንጂ የቤተ ክርስቲያን መዋቅር ይህንን ድርጊት ስላበረታታው አልነበረም።

በታሪክ ሁሉ፣ ቤተ ክርስቲያን የተለያዩ አስተዳደራዊ መዋቅሮችን አዘጋጅታለች። ይህንንም ያደረገችው የአገራቸውን የመንግሥት አስተዳደር በመኮረጅ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን እንዴት መተዳደር እንዳለባት የሚናገር ነገር የለም። ስለሆነም፣ እያንዳንዷ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንና ቤተ እምነት ወንጌሉን ለማሰራጨት ከሁሉም በላይ ጠቃሚ ነው የሚሉትን ዓይነት አደረጃጀት መከተል ይችላሉ። ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የዓለምን የአስተዳደር መዋቅር ላለመከተል መጠንቀቅ አለባቸው። አንድ ቤተ እምነት የቤተ ክርስቲያኑን ፍላጎት የሚያሟላ ዓይነት አስተዳደራዊ መዋቅር ቢከተል መልካም ነው። ይሁን እንጂ፣ መዋቅራቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አገልጋዮች መሆን እንዳለባቸውና አማኞች ስጦታቸውን በመጠቀም እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ ካህናት መሆናቸውን የሚገልጹትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሖዎች እንዳይጥስ መጠንቀቅ አለባቸው።

በቤተ ክርስቲያን ወይም በቤተ እምነት ውስጥ የተለያዩ ደረጃ ዎች ያሏቸውን መሪዎች የምንጠቀመው ሰዎችን ለመቆጣጠር ሳይሆን፣ አብረው የሚሠሩበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ነው። አብዛኞቹ ድርጅቶች መዋቅሮችን የሚጠቀሙት ሕዝቦቻቸውን ለመቆጣጠርና የአገሪቱን ሕጎች መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ ነው። ነገር ግን የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ሥልጣንን በዚህ መንገድ መገልገል የለባትም። ይልቁንም፣ **መዋቅርን መጠቀም ያለብን የእግዚአብሔር ሕዝብ ለመንግሥቱ በይበልጥ ተባብረው እንዲሠሩ ለማገዝ መሆን አለበት።** ዓላማው

ቡድኑ የመሠረተውን ዓላማ ማሳካት ሊሆን ይገባል:: የትኛውም ድርጅታዊ መዋቅር ጠቃሚ የሚሆነው ሰዎች በተሻለ ሁኔታ እንዲሠሩ ለማድረግ ሲችል ነው:: አስተዳደር አስፈላጊ የሚሆነው ሰዎች ለብቻቸው ከሚሠሩት በላይ በጋራ በመሥራት ዘለቄታዊ የሆነ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ለማገዝ ነው::

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሦስት መስፍርቶችን ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ በተደጋጋሚ ቤተ እምነታዊ መዋቅሮቻ ቸውን መገምገም አለባቸው:-

ሀ. መዋቅሩ ቤተ ክርስቲያን ራእይዋን እንድትፈጽም እየረዳት ነው? መዋቅሩ የራእዩ አገልጋይ መሆን አለበት:: መዋቅሩ ሰዎች ለብቻቸው ከሚያከናውኑት በላይ እግዚአብሔር የሚፈልጋቸውን ተግባራት እንዲያከናውኑ ካላስቻለ፣ የእድገት መሣሪያ ሳይሆን መሰናክል መሆኑ እሙን ነው::

ለ. አስተዳደራዊ መዋቅሩ ሰዎች በአንድነት ውጤታማ ተግባር እንዲያከናውኑ እየረዳቸው ነው ወይስ በአንድነት በመልካም ሁኔታ የሚሠሩበትን ሁኔታ እየቀነሰ ነው? አንድ መዋቅር የሚያስፈልገው ቤተ ክርስቲያን በአንድ ደረጃ ጥሩ ተግባር ማከናወን ሳትችል ስትቀርና ይበልጥ ውጤታማ ለመሆን የሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ትብብር ሲያስፈልጋት ነው:: ለምሳሌ፣ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መዋቅር ሳያስፈልጋት ለአካባቢዋ ሕዝብ ወንጌልን ልትመሰክር ትችላለች:: ነገር ግን ወንጌላውያንን ወደ ሩቅ ቦታዎች በምትልክበት ጊዜ አስተዳደራዊ መዋቅር ሊያስፈልጋት ይችላል:: ይህ መዋቅር አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መረጃ እንድታገኝ፣ ለወንጌላውያን የሚሰጥ ገንዘብ እንዲሰበሰብ፣ ልዩ ሥልጠና እንዲሰጥ፣ የወንጌላውያኑ ልጆች የትምህርት ጉዳይ እልባት እንዲያገኝ፣ ወዘተ. . . የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል:: ወይም ደግሞ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ቁልፍ አገልጋዮቻቸውን የማሠልጠን አቅም ላይኖራቸው ይችላል:: ነገር ግን አብረው የሚሠሩ አብያተ ክርስቲያናት በቡድን ሆነው መሪዎቻቸውን ሊያሠለጥኑ ይችላሉ:: ስለሆነም፣ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በላይ የሆነ መዋቅር የሚያስፈልገው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በራሷ



አገልግሎቷን ማከናወን በማትችልበት ጊዜ ነው:: አብያተ ክርስቲያናት እግዚአብሔር ከእነርሱ የሚፈልጋቸውን ነገሮች ለማሟላት ብዙ ነገሮችን ማሟላት ካለባቸው፣ ይህ ከእግዚአብሔር ፍላጎት እንዲወጡ ሊያደርጋቸው ይችላል:: ለምሳሌ ያህል፣ አንድ መዋቅር አብያተ ክርስቲያናት ከሩቅ አስተዳደር ድጋፍ ለማግኘት የሚያደርጉት ጥረት እግዚአብሔር እንዲያከናውኑ የሚፈልጋቸውን ነገሮች እንዳያከናውኑ የሚያደርግ ከሆነ፣ ይህ መዋቅር የእግዚአብሔርን ሥራ ከማሳካት ይልቅ እያደናቀፈ ነው ማለት ነው::

ሐ. ሰዎች የመዋቅሩን ዓላማ አውቀው ድጋፋቸውን ይሰጣሉ? ሰዎች መዋቅሩን ወይም የመዋቅሩን ምክንያት ካልተገነዘቡ፣ ያ መዋቅር መሰናክል ይሆንባቸዋል፤ ወይም ደግሞ ከመዋቅሩ ዓላማ ጋር ካልተስማሙ፣ መዋቅሩን ሊደግፉ አይችሉም:: ሰዎች ገንዘባቸውን የሚሰጡት ጠቃሚ ነው ብለው ለሚያስቡት ነገር ነው:: ምእመናን መዋቅሩን የማይደግፉ ከሆነ፣ ብዙውን ጊዜ ይህ የሚሆነው የመዋቅሩን ጥቅም ባለመረዳታቸው ነው:: ስለዚህ መዋቅሩን መለወጥ ወይም ደግሞ የመዋቅሩን ጥቅም ለምእመናን በሚገባ ለማብራራት ተጨማሪ ጥረቶችን ማድረግ የመሪዎች ኃላፊነት ይሆናል ማለት ነው::

| |
|---|
| 2ኛ ጥያቄ:- ከላይ የተመለከቱትን ሦስት መስፈርቶች በመጠቀም የቤተ እምነታችሁን መዋቅር ገምግም:: ሀ) ወንጌሉን በውጤታማነት በማስፋፋት ላይ ያለው የመዋቅሩ ክፍል የትኛው ነው? ለ) ውጤታማ ያልሆነውና የእግዚአብሔርን ሥራ የሚያደናቅፈው የትኛው ክፍል ነው? ሐ) ይህ የመዋቅር ክፍል የእግዚአብሔርን ሥራ ከማጠናከር ይልቅ የሚገድበው ለምንድን ነው? መ) ቤተ ክርስቲያናችሁ አስተዳደራዊ መዋቅሯን ለመደገፍ የሚያስችል ገንዘብ ለማግኘት እየተቸገረች ነው? ከሆነ፣ ምክንያቱ ምን ይመስልሃል? |

አንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ወይም ቤተ እምነት ምንም ዓይነት መዋቅር ቢያዘጋጅ፣ መዋቅሩ ግልጽ ዓላማ ያለውና የቤተ ክርስቲያኒቱን ራእይ እውን ለማድረግ የሚያግዝ መሆን አለበት:: ምእመናን የመዋቅሩን ዓላማ መረዳት አለባቸው:: የመዋቅሩን ጥቅምና እግዚአብሔር የሰጣቸውን ራእይ እንዴት እውን

እንደሚያደርግ መረዳት አለባቸው። አንድ የቤተ እምነት የመዋቅር ክፍል የተዘጋጀበት ግልጽ ምክንያት ከሌለው፣ ይህ መዋቅር ሕዝቡን የሚያስጨንቅና የእግዚአብሔርን ሥራ የሚገድብ ቢሮክራሲያዊ ማነቆ መሆኑ የማይቀር ነው።

ችግሩ፣ እድሜያቸው እየገፋ ሲሄድ፣ የቤተ እምነት መዋቅሮች እየተወሳሰቡ ይሄዱና ሕዝቡ የተጨመሩትን ክፍሎች ዓላማ ይዘነጋል። ቢሮክራሲ እንደ አረም ይስፋፋና ሰዎች መንፈስ ቅዱስን ሰምተው እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሥራ የሚያከናውኑበትን መንገድ ይዘጋል። ብዙውን ጊዜ መዋቅሮች አብያተ ክርስቲያናት የራሳቸውን ኃላፊነት እንዳይወጡ ወይም ባላቸው ሀብት ተ ጠቅመው ተግባራቸውን እንዳያከናውኑ ይከለክሏቸዋል። በመዋቅሩ ላይ የበላይ አካላት የሆኑት መሪዎች ውሳኔዎችን እንዲሰጡና የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች እንዲያሟሉላቸው ይጠብቃሉ። በአጠቃላይ መዋቅሩ እየተስፋፋ በሚሄድበት ጊዜ፣ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት በጋራ የሚሠሩበትን ሁኔታ ከማመቻቸት ይልቅ ቤተ ክርስቲያንና መሪዎችን ያዳክማል።

| |
|---|
| 3ኛ ጥያቄ፡- የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ችግሮቻቸውን መፍታት ሲገባቸው የበላይ መሪዎችን ሲጠብቁ የተመለከትክበት ሁኔታ ካለ ግለጽ። |

የአጥቢያና የቤተ እምነት መሪዎች በየጊዜው መዋቅራቸውን በመመርመር የእግዚአብሔርን ሥራ የማያደናቅፉ መሆናቸውን ማ ረጋገጥ አለባቸው። የትኛውም የመዋቅሩ ክፍል የእግዚአብሔር ሕዝብ ለየብቻቸው ከሚያከናውኑት የበለጠ ተግባር እንዲያከናውኑ የማያስችል ከሆነ፣ መለወጥ አለበት። ጠቃሚ መስሎ ቢታየንም ባይታየንም፣ ቀደም ሲል ለተዘጋጀው የአስተዳደር መዋቅር ራሳችንን በግድ ከማስገዛት ይልቅ፣ ግቦቻችንን ለማሳካት እንደሚያግዝ አድርገን ልናስተካክለው ይገባል።

ዛሬ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እስከ ዋናው ጽሕፈት ቤት ድረስ አምስት አስተዳደራዊ ደረጃዎች አሏቸው። ለእነዚህ ሁሉ ደረጃዎች ገንዘቡ የሚመጣው ከአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ነው። ምእመናን እነዚህ የመዋቅር ደረጃዎች ለምን እንደሚያስፈልጉ ስለማይረዱ፣ ብዙውን ጊዜ ገንዘብ



ለመስጠት ፈቃደኞች ሳይሆኑ ይቀራሉ። «የክፍለ ማኅበር ወይም የክፍለ ማኅበራት ኅብረት ጥቅም ምንድን ነው? ቀጣናው ወይም ዋናው ጽ/ቤት የሚረዳን እንዴት ነው? የሴቶች ወይም የወጣቶች ማኅበር አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን የሚረዳት እንዴት ነው?» ሲሉ ያጉረመርማሉ። ምእመናን ለአንድ የመዋቅር ክፍል ድጋፍ መስጠታቸውን የሚገልጹት የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ነው። ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውጭ ያሉት የአመራር ክፍሎች ለአገልጋዮቻቸው የሚከፍሉትን ገንዘብ አጥተው የሚቸገሩት፡- ሀ) የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባላት ያ የአመራር ደረጃ ለምን እንዳስፈለገ ስለማይረዱ፣ ወይም ለ) ለዚያ መዋቅር ድጋፍ ስለ-ማይሰጡና በገንዘባቸው ለመደገፍ ፈቃደኞች ባለመሆናቸው ነው። እስተዋይ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጊዜ ወስደው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን መዋቅሮቹንና አስፈላጊነታቸውን መ ረዳታቸውንና ድጋፍ ለመስጠትም ፈቃደኞች መሆናቸውን ለማ ረጋገጥ ይሞክራሉ። የቤተ እምነት መሪዎች የእግዚአብሔርን ሥራ በውጤታማነት ለማከናወን የሚያስችሉትን የመዋቅር ክፍሎች ብቻ በመጠቀም ላይ ቢያተኩሩ መልካም ነው። መዋቅሩንና ዓላማውንም ለምእመናን ማብራራት አለባቸው። ይህ ሁሉ ጥረት ተደርጎ አሁንም ምእመናኑ የማይደግፉት ከሆነ፣ ሕዝቡ ጠቀሜታውን እስኪረዳ ድረስ አገልግሎት ከመስጠት እንዲርቅ ማድረጉ መልካም ይሆናል።

| |
|---|
| 4ኛ ጥያቄ፡- ብሔራዊ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አብያተ ክርስቲያናት በበለጠ ተቀራርበው እንዲሠሩና የጋራ ራእያቸውን እንዲያሳኩ ለማገዝ ምን ቢያደርጉ ይበጃል ትላለህ? |

2. አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የአጠቃላይ ቤተ እምነት መሠረታዊ ደ ረጃ ስለ ሆነች፣ እጅግ ግልጽና ጠንካራ መዋቅርና በሚገባ የሠለጠኑ መሪዎች ሊኖሯት ይገባል።

አንድ ቤተ እምነት ጠንካራ የሚሆነው የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን ጥንካሬ ያህል ነው። አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ጠንካራ ከሆኑ፣ ቤተ እምነቱ ጠንካራ ይሆናል። አጥቢያ እብያተ ክርስቲያናት ደካማ ከሆኑ ደግሞ፣ ቤተ እምነቱ ደካማ ይሆናል።

የቤተ እምነቱ መዋቅሮች ሁሉ የሚመሠረቱት በእጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ላይ ነው። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አስተ ዳደራዊ መዋቅር የሁሉንም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት መንፈሳዊ አድገት የማያፋጥንና እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጠውን ራእይ ለመፈጸም የማያግዝ ከሆነ፣ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ያለው መዋቅር ቤተ ክርስቲያኒቱ እንድታድግ አያስችልም። ስለሆነም፣ አንድ ቤተ እምነት ጠንካራ ለመሆን ከፈለገ፣ ምእመናንን እግዚአብሔር ወደሚፈልገው አቅጣጫ የሚያደርሱ መንፈሳዊ ብስለት ያላቸው የእጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት መሪ ዎች እንዲኖሩት ሊያደርግ ይገባል። ቤተ እምነቱ በከፍተኛ የአመራር ደረጃ ላይ ብቻ ከፍተኛ ብቃት ያላቸውን መሪዎች ከማስቀመጥ ይልቅ፣ በእጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አመራር ላይ ምርጥ መሪዎችን ማስቀመጥ ይኖርበታል።

> 5ኛ ጥያቄ:- የቤተ እምነት ጥንካሬ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን መሪ ዎች ጥራት ያህል የሚሆነው ለምንድን ነው?

3. ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መዋቅር ውጭ ያሉት መዋቅሮች መመሥረት ያለባቸው ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንና ለወንጌል ስርጭት በሚሰጡት ጥቅም ሊሆን ይገባል።

አንድ የቤተ ክርስቲያን መዋቅር ወይም በቤተ እምነት ውስጥ የሚገኝ ድርጅት የተመሠረተበት ግልጽ የሆነ ምክንያት ከሌለው፣ መዋቅሩ መቀየር አለበት። አስተዳደራዊ መዋቅሮች ተስማጭ መሆን አለባቸው። በታሪክ የተወሰኑ ጊዜያት ውስጥ ለመሥራት በሚፈልጉ ሰዎች ፍላጎት አንጻር ሊሰፋ ወይም ሊጠብ የሚችል መሆን አለበት።

ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውጭ የትኛውም ድርጅታዊ መዋቅር ቋሚ ሊሆን አይገባም። አንድ መዋቅር ለጊዜው አስፈላጊ ከሆነ (ለምሳሌ፣ በአንድ ከተማ ጆማ ስብከተ ወንጌል ማዘጋጀት) ጊዜያዊ እስተዳደራዊ መዋቅር ሊቋቋምና የተፈለገው ዓላማ ከተ ከናወነ በኋላ ሊነሣ ያሻል። መዋቅሩ ለገጠሩ ሕዝብ የሚጠቅም ከሆነ፣ የከተማው ሕዝብም እንዲከተሉት የግድ ማለቱ አስፈላጊ አይሆንም። ወይም ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው አስተ



ዳደራዊ ሁኔታ ከተለወጠ፣ መዋቅሩም መለወጥ ለአበት። መዋቅሩ ለረዥም ጊዜ አገልግሎት (ለምሳሌ፣ በብዙ ትምህርት ቤቶች ትብብር የሚካሄድ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት) የሚያስፈልግ ከሆነ፣ ረዥም እድሜ እንዲኖረው ይደረጋል ማለት ነው። ያሁን እንጂ፣ መዋቅሩ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በሚርቅበት ጊዜ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የመዋቅሩን ዓላማና አስፈላጊነት ለምእመናን ግልጽ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ምእመናን የመዋቅሩ አስፈላጊነት ግልጽ ካልሆነላቸው፣ አገልግሎቶችንና ከእጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውጭ ያሉትን ሥራዎች ለማገዝ አይፈልጉም። የምእመናን ድጋፍ ከተለየው ደግሞ፣ መዋቅሩ ሸክም ስለሚሆን መወገድ አለበት። ይህ ካልሆነ፣ ስለ አስፈላጊነቱ ለምእመናን ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠቱ አስፈላጊ ይሆናል።

> 6ኛ ጥያቄ:- ሀ) አብያተ ክርስቲያናት ከብቻቸው ይልቅ በኅብረት የበለጠ ጥሩ አድርገው ሊያከናውኑ የሚችሏቸውን ነገሮች ዘርዝር። ለ) እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን ራእይ ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑት እስተ ዳደራዊ መዋቅሮች ምን ምንድን ናቸው ብለህ ታስባለህ? ሐ) እብሮ መሥራቱ ለቤተ ክርስቲያን ሸክም ሳይሆን ተግባራዊ እንዲሆን በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ መስተካከል ያለባቸው መዋቅሮች የትኞቹ ናቸው?

ያለነው አስተዳደራዊ መዋቅሮች እያደጉ ባሉበት ዘመን ላይ ነው። ከዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ኅብረት (ኢቫሱ) ወይም ከታላቁ ተ ልዕኮ ጋር አብረው የሚሠሩ ብዙ ድርጅቶች አሉ። እነዚህ ድርጅቶች ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያላቸው ግንኙነት ምንድን ነው? የወንጌላውያን እብያተ ክርስቲያናት ኅብረትም አለ። ይህ ድርጅት ለቤተ ክርስቲያን እድገት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ምንድን ነው? ይህ ድርጅት ቋሚ መሆን አለበት ወይስ ጊዜያዊ በመሆን እብያተ ክርስቲያናት እንደ ጆማ ስብከተ ወንጌል ዓይነት የተወሰኑ ተግባራት በጋራ እንዲያከናውኑ ማገዝ አለበት? ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውጭ እንድ ድርጅት በምንመሠርትበት ጊዜ እጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የምታከናውናቸውን ተግባር የመድገሙን ችግር ልንፈጥር እንችላለን። ወይም ደግሞ በበለጠ ስልታዊ ጠቀሜታ ባለው መንገድ ሊያገለግል የሚችለውን ገንዘብ ለድርጅቱ ማቋቋሚያ እንጠቀማለን። የእግዚአብሔር ገንዘብ ባለ አደራዎች

አንደ መሆናችን መጠን፣ የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ መጠቀም ያስብን የእግዚአብሔርን ራእይ በሚያስፋፋና የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ራአይ እውን በሚያደርግ መንገድ መሆን አስበት።

4. በቤተ ክርስቲያን ቤተ እምነታዊ መዋቅር ውስጥ የመሪዎች ሚና

ሀ. እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ስያዙት የመሪነት ደረጃ በተጠያቂነት ይይዛቸዋል። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ስሁሉም ምእመናን እንክብካቤ የማድረግ ኃላፊነት አስባቸው። የአውራጃ መሪዎች ስአውራጃው ምእመናን፣ የቀጣናው መሪዎች ደግሞ ስቀጣናው ምእመናን ኃላፊነት እስባቸው። የዋናው ጽ/ቤት መሪዎች ደግሞ በአገሪቱ ውስጥ ላሉት ምእመኖቻቸው ሁሉ ኃላፊነት አስባቸው። በመሪነት ስማገልገል በምንስማማበት ጊዜ በተሾምንበት ክልል ውስጥ ያሉትን ኃላፊነቶች ስመወጣት መስማማታችን መሆኑን መዘንጋት የስብንም። እግዚአብሔር እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪ (የአጥቢያ፣ የአውራጃ፣ የዋናው ጽ/ቤት መሪ) ባለን ሥልጣን ላይ እንድናተኩር አይፈልግም። ነገር ግን አናገለግላስን ላልናቸው ሰዎች ሕይወት ኃላፊነት እንዳስብን እንድንገነዘብ ይፈልጋል።

ስ. በክፍተኛ አመራር ላይ ያሉት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ኃላፊነታቸውን የሚወጡት ከሥልጣናቸው ሥር ላሉት መሪዎች የአረኝነትን አገልግሎት በመስጠት ነው። በከፍተኛ አመራር ላይ ያሉት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከኃላፊነታቸው ሥር ያሉትን ምእመናን ሁሉ በእረኝነት ሊያገለግሉ የሚችሉት እንዴት ነው? የበላይ አመራር አካላት እያንዳንዱን ምእመን ሊያውቁና በቀጥታ ሊያገለግሉ እንደማይችሉ ግልጽ ነው። መሪዎች በክፍተኛ የአመራር ደረጃ ላይ በሚሆኑበት ጊዜ፣ ስምእመናን ቀጥተኛ አገልግሎት የሚሰጡበት ሁኔታ ይቀንሳል። እንዲህ ዓይነቱን አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉት **በተዘዋዋሪ መንገድ** የበታች መሪ ዎች ውጤታማ አገልግሎት እንዲያበረክቱ የሚያስችል ሥልጠና በመስጠት ነው። አነዚህ ሰዎች ራሳቸውን ከሥልጣናቸው ሥር ያሉት ሰዎች አስተዳዳሪዎች አድርገው በመመልከት ፈንታ፣



የበታች መሪዎች አረኞች አድርገው መመልከት እስባቸው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸውና በአመራር ብቃታቸው እንዲያድጉ በማገዝ በታችኛው መዋቅር ያሉት ምእመናን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ይረዷቸዋል። ይህም እግዚአብሔር በኃላፊነት የሾሟቸውን ሰዎች ሁሉ የሚያገለግሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

ስስሆነም የብሔራዊ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቀዳሚ ኃላፊነት ስቀጣና ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነው ማስት ነው። ይህም ማስት ብሔራዊ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስቀጣና ቤተ ክርስቲያን መሪዎች የግል እንክብካቤ ማድረግ አስባቸው ማስት ነው። በመንፈሳዊ ብስለትና በአመራር ብቃት እንዲያድጉ ይ ረዷቸዋል። የቀጣና ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከእነርሱ የገዘፉትን ችግሮች እንዲፈቱ በማገዝ ይረዷቸዋል። የቀጣና ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ደግሞ ስአውራጃ መሪዎች፣ የአውራጃ መሪዎች ስአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተመሳሳይ እንክብካቤ ማድረግ እስባቸው።

> 7ኛ ጥያቄ:- ይህ የመዋቅር አስተሳሰብ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንንና ቤተ እምነትን ሊያጠናክር ወይም ሊያዳክም የሚችለው እንዴት እንደ ሆነ አብራራ። ለ) ከላይ የተገለጸውን መዋቅራዊ አሠራር ተግባራዊ ሰማድረግ በአስተዳደራዊ ግንዛቤ ውስጥ ሊኖር የሚገባው ለውጥ ምንድን ነው? ሐ) ከሥርህ ሌሎች መሪዎችን የምታገለግል መሪ ብትሆን፣ በመንፈሳዊ ሕይወታቸውና በአመራር ችሎታቸው እንዲያድጉ ለማገዝ ምን ምን ነገሮችን እንደምታደርግ ዘርዝር።

ሐ. የቤተ ክርስቲያን የበላይ መዋቅር አመራር አካላት ውሳኔ መስጠት ያስባቸው ከደረጃቸው ጋር ግንኙነት ላላቸው ነገሮች መሆን አስበት። በሌላ አባባል፣ አንድን አገልግሎት ማጽደቅ የሚያስፈልገው ከመዋቅሩ ጋር ግንኙነት በሚኖርበት ጊዜ ነው። ስለሆነም፣ አገልግሎቱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ብቻ የሚያሳትፍ ከሆነ፣ አገልግሎቱን በተመለከተ ውሳኔ መስጠት ያስባቸው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ብቻ መሆን ይኖርባቸዋል። ነገር ግን አገልግሎቱ የሌሎች አብያተ ክርስቲያናትን ተሳትፎ

የሚጠይቅ ከሆነ፣ የእነዚያ እብያተ ክርስቲያናት ሽማግሌዎችም በአገልግሎቱ ላይ ውይይት አድርገው ውሳኔ መስጠት ይኖርባቸዋል:: የቤተ እምነት መሪዎች ለእነርሱ ሪፖርት ለሚያደርጉት መሪዎች የእረኝነት አገልግሎት በሚሰጡበት ጊዜ ሊያስታውሷቸው የሚገቡ አራት እውነቶች አሉ:-

1) የበላይ መዋቅር አመራር መሪዎች የበታች መዋቅር አመራር መሪዎች በሰጡት ውሳኔ ላይ ጣልቃ መግባት የለባቸውም:: ይህንን ማድረግ ያለባቸው ውሳኔው የበላይ አስተ ዳደራዊ ደረጃን የሚነካ ወይም ውሳኔው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሐ ዎችን የሚጥስ ነው የሚል እምነት ካደረባቸው ብቻ ነው:: (ማስታወሻ:- መሪዎች ባለማቋረጥ የመጽሐፍ ቅዱስን የፍትሐዊነት መርሖዎች የሚጥሱ ከሆነ፣ ምናልባትም መፍትሔው ውሳኔያቸውን መሻር ሳይሆን፣ መንፈሳዊ ብቃት የሌላቸውን መሪዎች በሌሎች መተካት ሊሆን ይችላል::) ይህንን በሚያደርጉበት ጊዜ፣ መሪው ስሕተት ሠርቷል እያሉ ማውራቱ ጥቅም የለውም:: የቤተ ክርስቲያን የበላይ መዋቅር መሪዎች የበታች መዋቅር መሪዎች በሚሰጡት ውሳኔ ካልተስማሙ፣ የተ ለያዩ ጥያቄዎችን በማንሣት የበታች መዋቅር መሪዎች ውሳኔያቸውን እንደገና እንዲመረምሩ ማገዝ ይኖርባቸዋል:: የበላይ መዋቅር አመራሩ የበታች መዋቅር አመራሩን ውሳኔዎች የሚቀይር ከሆነ፣ ይህ በሁለቱ የአመራር አካላት መካከል ያለውን ግንኙነት ከማሻከሩም በላይ፣ ሰዎች በበታች መዋቅር አመራር አባላት ላይ እምነታቸውን እንዳይጥሉ የሚያደርግ ነው:: ይህ ደግሞ የበታች መዋቅር አመራር መሪዎች የመሪነት ተግባራቸውን እንዳያካሂዱ ያደርጋል:: ይህ በሚሆንበት ጊዜ የበላይ መዋቅር አመራሮች ሁሉንም አመራር ለመስጠት ይገደዳሉ:: ይህ ደግሞ የአስተዳደራዊ መዋቅሩን አመራር በሙሉ የሚያበላሽ ነው::

2) የበላይ መዋቅር አመራሮች ጉዳዮችን መመርመር ያለባቸው የበታች መዋቅር መሪዎች ችግሩን ለመፍታት የሚችሉትን ጥረት ካደረጉ በኋላ ብቻ ሊሆን ይገባል:: የበታች መዋቅር መሪዎች ከባባድ ጉዳዮችን ለበላይ መዋቅር መሪዎች እንዲያስተላልፉ



ማደፋፈር ማለት የበታች መዋቅር መሪዎች በመሪነት ችሎታቸው እንዳያድጉ ማድረግ ነው:: ምእመናንም የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችን አልፈው ወደ ላይኛው መዋቅር አመራሮች እንዲሄዱ ያበረታታቸዋል:: ይህ ደግሞ ሁሉም ሰው ወደ ላይኛው መዋቅር አመራር እንዲሄድ የሚገፋፋና አመራሩን የበለጠ እስቸጋሪ የሚያደርግ መሆኑ ግልጽ ነው:: ውሳኔውም ቢሆን ብዙውን ጊዜ ያን ያህል ጥሩ ሊሆን አይችልም:: የቤተ ክርስቲያን የበታች መዋቅር መሪዎች ስለ ሁኔታውና ስለ ሰዎች ተሳትፎ ግልጽ የሆነ ግንዛቤ አላቸው:: ጉዳዩ በአመራር መዋቅር ወደ ላይ በሄደ ቁጥር እውነተኛውን ጉዳይ ለማወቅ ስለሚያስቸግር፣ መሪዎች ውሸትን ሊያምኑና የማይረቡ ውሳኔዎችን ሊሰጡ ይችላሉ::

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድ ችግር በሚኖርበት ጊዜ፣ ወደ ሽማግሌዎች ከመድረሱ በፊት መጀመሪያ በበታች መዋቅር አመራሮች መፍትሔ መፈለግ አለበት:: ችግሩ የተፈጠረው በአንድ አነስተኛ ቡድን ውስጥ ከሆነ፣ የቡድኑ መሪ ችግሩን ለመፍታት መጣር አለበት:: ችግሩ ወደ ቀጣዩ የአመራር ደረጃ (ወደ መጋቢ ወይም ሽማግሌዎች) መተላለፍ ያለበት ከመሪው ችሎታ በላይ በሚሆንበት ጊዜ ነው::

3) የበላይ መዋቅር አመራሮች ትኩረት ማድረግ ያለባቸው ከእነርሱ በታች የሚሠሩትን መሪዎች ብቃት በማሳደጉ ተግባር ላይ መሆን አለበት:: (ለምሳሌ፣ ዮቶር የሙሴ ዋንኛ ተግባር ሰ ዎችን በተለይም መሪዎችን ማስተማር መሆን እንዳለበት ሲናገር፣ ይህንን ማለቱ ነበር::) የበላይ መዋቅር አመራሮች በጠቅላላው መዋቅር ላይ ተጽዕኖ ሊያመጡ የሚችሉት የበታች መዋቅር አመራሮች በሚገባ ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ ሊያግዙ ነው:: ስለሆነም፣ እብዛኛውን ጊዜያቸውን ከሥራቸው ያሉትን መሪዎች በማበረታታት ላይ ሊያውሉት ይገባል:: የበላይ መዋቅር መሪዎች እንዴት በጥሩ ሁኔታ እንደሚመሩ፣ እንዴት እግዚአብሔርን እንደሚለሙና ፈቃዱን እንደሚያውቁ፣ ሰዎችን እንዴት እንደሚወክሉና ሌሎች ሥራውን እንዲያከናውኑ እንዴት ማሠልጠን እንዳለባቸው፣ ወዘተ. . . ማስተማር አለባቸው:: እነዚህ

የበታች መዋቅር አመራሮች የዓለምን መንገድ እንዳይከተሉና መንፈሳዊ በሆኑ መንገዶች እንዲያስቡ ማበረታታት አለባቸው:: የበላይ መዋቅር አመራሮች የበታች መዋቅር አመራሮች የተሻሉ ውሳኔዎችን ለመስጠት ይችሉ ዘንድ ጉዳዮችን በተሻለ መንገድ እንዲገነዘቡ ሊያግዟቸው ይገባል:: በቀጥታ በውሳኔያቸው ውስጥ ጣልቃ ከመግባት ይልቅ የበታች መዋቅር መሪዎች የተሻሉ ውሳኔ ዎችን እንዲሰጡ ሊያግዟቸው ይገባል::

4) አንድ መዋቅር የሚዘጋጅበት ዓላማ ሰዎች አገልግሎታቸውን ለማካሄድ ከሁሉም ደረጃዎች ፈቃድ ማግኘት እንዳለባቸው ለማረጋገጥ መሆን የለበትም:: ዓላማው እግዚአብሔር ለዓለም አቀፋዊት ቤተ ክርስቲያኑ ያለውን ፍላጎት ለማሟላት ሰ ዎች በተሻለ ሁኔታ አብረው የሚሠሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት መሆን አለበት:: ፈቃድ መስጠት ያለበት አገልግሎቱ የሚዳስሰው የሥልጣን ደረጃ ብቻ መሆን አለበት::

ለምሳሌ ያህል፣ አንድ የቤተ ክርስቲያን አባል የሆነ ራእይ ቢኖ ረው፣ ስዚህ ጉዳይ ውሳኔ መስጠት ያለባቸው የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ብቻ መሆን አለባቸው:: ሌሎች የቤተ ክርስቲያኒቱ ክፍሎች ግን ራእዩ እውን እንዲሆን የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድ ረግ ይጠበቅባቸዋል:: ስለዚህ፣ እግዚአብሔር አንድ አማኝ በአካባቢው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እንዲጀምር ራእይ ቢሰጠው፣ ራእዩ የሌሎችን ድጋፍ የሚፈልግበት ሁኔታ በግልጽ እስካልታየ ድ ረስ፣ ሽማግሌዎቹ በዚህ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ መግባት አያስፈልጋቸውም:: የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የግለሰቦችን ራእዮች መገደብ የለባቸውም:: ሽማግሌዎች በአገልግሎቱ ውስጥ መሳተፍ ያለባቸው በግለሰቡና በአገልግሎቱ አካባቢ ችግሮች ካሉ (ለምሳሌ፣ የሐሰት ትምህርት ካለ) ብቻ መሆን አለበት:: ሽማግሌ ዎች የዓለምን ምሳሌነት በመከተል ሰዎች ለሚያደርጉት ነገር ሁሉ ፈቃድ ከእኛ መጠየቅ አለባቸው ማለት የለባቸውም:: ከዚህ ይልቅ፣ አንድ አማኝ እግዚአብሔር በልቡ ውስጥ ያኖረውን ነገር ተግባራዊ ለማድረግ በሚፍጨረጨርበት ጊዜ ድጋፍ መስጠት ይጠበቅባቸዋል::



የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ምእመናን የበለጠ ውጤታማ አገልግሎት እንዲሰጡም የማገዝ ኃላፊነት አለባቸው:: ስለዚህ፣ እግዚአብሔር እያንዳንዱን አማኝ እንዴት እየመራው እንደ ሆነ የማወቅ ኃላፊነት አለባቸው:: አንድ ግለሰብ ብቻ ራእዩን እውን ለማድረግ የሚታገል ከሆነ፣ ራእዩ ሊያድግ የሚችለው በግለሰቡ ችሎታ ደረጃ ብቻ ነው:: የራእዩን እድገት ለማፋጠን የሌሎች ሰ ዎች መንፈሳዊ ስጦታዎች ከጥቅም ላይ ሳይውሉ ይቀራሉ:: ግለሰቡ አገልግሎቱን ቢተወው ደግሞ፣ ይቀራል ማለት ነው:: ስለ-ሆነም፣ ሽማግሌዎች የአንድ ግለሰብ አገልግሎት የቤተ ክርስቲያኒቱን ራእይ የሚያግዙ መሆናቸውን በሚረዱበት ጊዜ፣ ሌ ሎችም ሰዎች የሚሳተፉበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለባቸው:: ራእዩ የእግዚአብሔርን አሳብ እውን ያደርግ ዘንድ ይህንኑ የሚያፋጥን ቀለል ያለ አስተዳደራዊ መዋቅር ሊዘጋጅና የመሪነትና የክትትል ሥራዎች ሊሠሩ ይገባል:: ይህ ማለት ግን መልካም ምሪት ለመስጠት የሚያስችል በቂ ጊዜ የሌላቸው ሽማግሌዎች በአገልግሎቶቹ ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ ሊኖራቸው ይገባል ማለት አይደለም:: ከዚህ ይልቅ፣ የውክልናን ሂደት በመጠቀም አገልግሎቱ እንዲያድግ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ቢያደርጉ የተሻለ ይሆናል::

በተመሳሳይ ሁኔታ፣ የበታች መዋቅር አመራሮች ከበላይ መዋቅር አመራሮች ፈቃድ ማግኘት ያለባቸው አገልግሎታቸው ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውጭ ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ከሆነ ብቻ ነው:: የበታች መዋቅር አመራሮች በእነርሱ ደረጃ ያለችውን ቤተ ክርስቲያን ለሚነኩ ጉዳዮች የበላይ መዋቅር አመራሮችን ፈቃድ ማግኘት ካለባቸው፣ ሰ ዎች እግዚአብሔርን እንዲያገለግሉ ነፃ የሚያደርጋቸውን ሳይሆን፣ አገልግሎቱን የሚያደናቅፍ መዋቅር እየገነባን ነው ማለት ነው:: ነገር ግን ውሳኔው አብረው በሚሠሩ እያሌ አብያተ ክርስቲያናት ላይ ወይም በጠቅላላው ቤተ እምነት ላይ ተጽዕኖ የሚያመጣ ከሆነ፣ የቀጣና ወይም የቤተ እምነት መሪዎችም በውሳኔው ላይ መሳተፍ አለባቸው:: አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በሌሎች አብያተ ክርስቲያናትም ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩትን ውሳኔዎች ለብቻቸው

ማስተላለፍ የለባቸውም። መዋቅሩ የተዘጋጀው አብያተ ክርስቲያናት በተሻለ ሁኔታ አብረው እንዲሠሩ ለማገዝ ስለሆነ፣ በውሳኔው ውስጥ መሳተፍ ያለባቸው አብረው የሚሠሩ አብያተ ክርስቲያናት ብቻ መሆን አለባቸው። (ለምሳሌ፣ አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የራሷን የደቀ መዝሙርነት ፕሮግራም ለመጀመር ከፈለገች፣ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ሽማግሌዎች ውጭ የሌላ ሰው ፈቃድ ማግኘት አያስፈልጋትም። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከእነርሱ በላይ ካሉት አመራሮች ምክር ወይም የቁሳቁስ ድጋፍ ሊጠይቁ ይችላሉ። ውሳኔ ማድረጉ ግን የራሳቸው ተግባር ነው የሚሆነው። ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአካባቢያቸው ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ውስጥ የደቀ መዝሙርነት ፕሮግራም ለመጀመር ከፈለጉ፣ የተሳታፊ አብያተ ክርስቲያናት ተሳትፎ ወሳኝ ይሆናል።)

> 8ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያን የመሪዎችን ፈቃድ የማይጠይቁ የግለሰብ አማኝ አገልግሎቶችን በምሳሌነት ጥቀስ። ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአገልግሎት ላይ በመሳተፍ ክትትል ማድረግ ያለባቸውን ሁኔታዎች በምሳሌነት ጥቀስ። ሐ) ከመጠን ያለፈ ቁጥጥር የግለሰቦችን ራእይ ሊገድብ የሚችለው እንዴት ነው? መ) አብሮ አለመሥራት የአንዳንድ አገልግሎቶችን እድገት የሚያደናቅፈው እንዴት ነው? ምሳሌ ስጥ።

5. ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መዋቅር ሊጠቀም የሚችል አሳብ:-

እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን ለእያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል መንፈሳዊ ሕይወት በኃላፊነት ይጠይቃቸዋል። እያንዳንዱ አባል ለእግዚአብሔር አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔር ለአንደኛው በግ እጅግ በማሰቡ ምክንያት 99ኙን ሜዳ ላይ ጥሎ ፍለጋ የሚሄድ ከሆነ (ሉቃስ 15:4-7)፣ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላለው ለእያንዳንዱ አማኝም ያስባል ማለት ነው። አንድ አባል መንፈሳዊ ምሪት ባለማግኘቱ ምክንያት ችግር ቢገጥመው፣ ዋንኛው ኃላፊነት የሚወድቀው በሽማግሌዎች ላይ ነው። ነገር ግን ጥቂት ሽማግሌዎች (በአንዳንድ ቤተ እምነቶች 7 ወይም 9 ሰዎች) በመቶዎችና አንዳንዴም በሺዎች ለሚቆጠሩ



ምእመናን የግል ምሪት ሊሰጡ የሚችሉት እንዴት ነው? አይችሉም። ስለዚህ እያንዳንዱ አባል የግል እንክብካቤ የሚያገኝበትን መንገድ ማዘጋጀት አለባቸው።

ይህንን ለማሳካት ቤተ ክርስቲያን በሚከተለው መንገድ ብትደራጅስ?

ሀ. የቤተ ክርስቲያን አባላትን በሙሉ ከ10 እስከ 20 ሰዎች ባሉባቸው ቡድኖች ማደራጀት። እያንዳንዱ አነስተኛ ቡድን የየራሱ መሪ ይኖረዋል። እነዚህ መሪዎች መንፈሳዊ ብስለት ያላቸው ሆነው የቡድናቸውን አባላት በግል ደረጃ የሚያውቁና አስፈላጊውን መንፈሳዊ ሥልጠናና ምሪት የሚሰጡ መሆን አለባቸው። የአንድ ቡድን መሪ ደግሞ ተጠሪነቱ ለአንድ ሽማግሌ ይሆናል። ስለዚህ አንድ ሰው በክርስቶስ አምኖ ከቤተ ክርስቲያን ጋር በሚቀላቀልበት ጊዜ፣ ሽማግሌዎች ወደ አንድ ቡድን እንዲገባ በማድረግ የቡድን መሪው ለአዲሱ አማኝ እንክብካቤ እንዲሰጠውና የቡድኑ አካል እንዲያደርገው ኃላፊነት ይሰጡታል።

የቡድኑ አባላት ቁጥር እየበዛ በሚሄድበት ጊዜ፣ ይከፋፈሉና አዳዲስ ቡድኖች ይፈጠራሉ። በዚህ ዓይነት እያንዳንዱ አዲስ አማኝ ማበረታቻ ሊሰጡትና በእምነቱ እንዲያድግ በሚያግዙት ሰዎች መሐል የመሆን ዕድል ይኖረዋል። ብዙውን ጊዜ ሰዎች በክርስቶስ ቢያምኑም፣ በመንፈሳዊ እድገታቸው እንዲያድጉ ኃላፊነት የሚወስድላቸው አይገኝም። በቂ እንክብካቤ ያልተደረገለት ሕጻን በፍጥነት እንደሚሞት ሁሉ፣ እነዚህም አማኞች ቤተ ክርስቲያንን ጥለው በመሄድ በክርስቶስ ላይ ያላቸውን እምነት ይተዋሉ።

ለ. ቤተ ክርስቲያን ሃምሳ አባላት ባሏቸው ትላልቅ ቡድኖች ትከፈላለች። (ሦስት ወይም አራት አነስተኛ ቡድኖችን አንድ ላይ ማድረግ።) እያንዳንዱ ሽማግሌ ለእያንዳንዱ አባል አመራርና ክትትል እንዲያደርግ ኃላፊነት ይሰጠዋል። ብዙ ሽማግሌዎች የቤተ ክርስቲያን አባላትን ሁሉ በስም ለማወቅና ያሉበትን ሁኔታ ለመረዳት ይቸገራሉ። ነገር ግን አንድ ሽማግሌ 50 ሰዎችን በሚገባ

ሊያውቃቸው ይችላል፡፡ ይህ ሽማግሌ እያንዳንዱን አባል፣ የቤተ ሰቡን ሁኔታ፣ መንፈሳዊ እድገቱን፣ መንፈሳዊ ስጦታውን፣ ወዘተ. . . በማወቅ ክትትል የማድረጉን ኃላፊነት ይወጣል፡፡ የዚህን የ50 ሰዎች ቡድን አካል የሆኑትን አነስተኛ ቡድኖች የመከታተልም ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡ የምእመናን ቁጥር እጅግ በመብዛቱ ምክንያት ሽማግሌዎች ክትትል ለማድረግ ከተቸገሩ፣ እያንዳንዱ ሽማግሌ ከሥሩ ሆኖ የሚረዳው ሰው ሊመርጥ ይችላል፡፡ የእረኞች ቀዳሚ ኃላፊነት ለእግዚአብሔር መንጋ የእረኝነት አገልግሎት መስጠት ነው፡፡ መልካም እረኛ ለመሆን ደግሞ ከሁሉም ምእመናን ጋር የግል ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህንን አገልግሎት በቀጥታ ለመስጠት ካልቻሉ፣ ሌሎችን መወከል አለባቸው፡፡ ዓላማው ለቤተ ክርስቲያን አስተዳደር መዋቅሩን ማስፋት ሳይሆን፣ የመሪዎችን የእ ረኝነት ችሎታዎች ማሳደግ ነው፡፡ ስለሆነም የቤተ ክርስቲያኒቱ ምእመናን ቁጥር እያደገ በሚሄድበት ጊዜ፣ ተጨማሪ አነስተኛና የ50 አባላት ቡድኖች ያስፈልጋሉ፡፡

ቤተ ክርስቲያን እያደገች በምትሄድበት ጊዜ፣ ሽማግሌዎች ለአማኞች የእረኝነት አገልግሎት የሚሰጡት በሌሎች መሪዎች አማካኝነት ይሆናል፡፡ እረኞቹ ትልልቆቹን ቡድኖች በእረኝነት ሊያገለግሉ፣ የትልልቅ ቡድኖች መሪዎች በበኩላቸው የአነስተኛ ቡድኖችን መሪዎች በእረኝነት ያገለግላሉ፡፡ በእያንዳንዱ የአመራር ደረጃ ላይ የሚገኙ መሪዎች ያላቸውን ኃላፊነትና ውሳኔ የመስጠት ሥልጣናቸውን ልክ ያውቃሉ፡፡ ዮቶር ለሙሴ እንደ ተናገረው፣ ወደ ሽማግሌዎች መሄድ ያለባቸው ትላልቅ ጉዳዮች ብቻ ናቸው፡፡

> 9ኛ ጥያቄ:- ሀ) ይህንን የቤተ ክርስቲያን ምእመናን በእረኝነት ለማገልገል የቀረበውን መዋቅር በመጠቀም፣ ሀ) የቤተ ክርስቲያናችሁን አባላት ስም በሙሉ ዘርዝር፡፡ 2) እያንዳንዱን አባል በአነስተኛ፣ በ50ዎችና ካስፈለገም ከዚህ ተለቅ ባሉ ቡድኖች ከፋፍል፡፡ 3) አንድ ሽማግሌ ለቡድኑ እንክብካቤ እንዲያደርግ መድብ፡፡ ለ) የዚህ ዓይነት መዋቅር በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ መኖሩ ምን ያህል ጠቀሜታ ይኖረዋል? ሐ) እንዲህ ዓይነት መዋቅር ለመገንባት እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? መ) ዕድሉን ካገኘህ፣ ስለዚህ መዋቅር ምን እንደሚያስብ ከቤተ ክርስቲያናችሁ ሽማግሌ ጋር ተነጋገር፡፡



## የትውፊትን ገጽታዎች መረዳትና ድርጅታዊ ተሐድሶ ማካሄድ

ብዙዎቻችን በግል ሕይወታችንና በቤተ ክርስቲያናችን ተ ሐድሶን እንናፍቃለን፡፡ አንዳንድ ጊዜ በስሜት መዘመር ወይም በልሳናት እንደ መናገርና እንደ ፈውስ ያሉት መንፈሳዊ ስጦታዎች እግዚአብሔር ተሐድሶ ማምጣቱን የሚያሳዩ ናቸው ብለን እናስባለን፡፡ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ አማኞች በማኅበረሰባቸው ውስጥ የሚኖሩበትን ሁኔታና ባሕርያቸውን ካልለወጠ፣ መንፈሳዊ ተሐድሶ መኖሩ አጠያያቂ ጉዳይ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ምእመናን ብቻ ሳይሆኑ፣ አገልግሎቶችና ቤተ እምነቶችም መለወጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ምሑራን በደርጅቶችና አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚከተሉት እውነታዎች የሚከሰቱ መሆናቸውን ያስረዳሉ፡

1. አብያተ ክርስቲያናትና ድርጅቶች በሚጀመሩበት ጊዜ ነገሮች ሁሉ በጣም አስደሳች ገጽታ ይኖራቸዋል፡፡ የቤተ ክርስቲያን መዋቅሮች ተለማጮች ሲሆኑ፣ መሪዎች የመንፈስ ቅዱስን እንቅስቃሴና ነገሮችን በአዳዲስ መንገዶች የማከናወን አማራጮች ለመቀበል ፈቃደኞች ይሆናሉ፡፡ ቤተ ክርስቲያን እድሜ እየቆጠረች ስትሄድ ግን፣ ተለማጭነቷና የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ የማዳመጥ አቅሟ ይቀንሳል፡፡ መሪዎች ልምምዶችንና ደንቦችን በማደራጀት ላይ ያተኩራሉ፣ እነዚህም በአብዛኛው የማያስፈልጉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ትውፊቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይጀመራሉ፣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን የተጀመረበትን ምክንያት የሚያስታውስ ሰው አይኖርም፡፡ ለምሳሌ፣ ብዙውን ጊዜ በፕሮግራም ፍጻሜ ላይ «አባታችን ሆይ» ጸሎት እንጸልያለን፡፡ ነገር ግን ይህን ጸሎት በፕሮግራሙ ፍጻሜ ላይ ለምን እንደምንጸልይ አለማወቃችን ብቻ ሳይሆን፣ የጸሎቱን ቃላት አምብዛም እናስበውም፡፡ ወይም ደግሞ ስለ ትርጉሙ ሳንጨነቅ «በኢየሱስ ስም» እያልን እንጸልያለን፡፡ ይህ ደግሞ «የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ አትጥራ» የሚለውን (ዘጸአት 20:7) ትእዛዝ እንድንጥስ ያደርገናል፡፡ በአመዛኙ ስናጨበጭብ ወይም እልል ስንል፣ እግዚአብሔርን እያመለክን ነው ብለን እናስባለን፡፡ ነገር ግን እውነተኛውን አምልኮ አመለክን ማለት

የምንችለው ልባችን ተነክቶ ስናጨበጭብ ወይም እልል ስንል ብቻ ነው። ሰይጣን መጀመሪያ ትርጉማቸውን በመረዳት የምናደርጋቸውን ነገሮች ትርጉም ወደሌላቸው ተግባራት በመቀየር አምልኮአችንን ሊያበላሽ እንደሚችል መረዳቱ ጠቃሚ ነው።

> 10ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ሰዎች ዓላማውን ሳይረዱና ምንም ሳያስቡ የሚያከናውኗቸው ትውፊቶች (ወይም ልማዶች) ምን ምንድን ናቸው? ለ) ይህ ለቤተ ክርስቲያን አደገኛ የሚሆነው ለምንድን ነው?

እያንዳንዱ ድርጅት ተሐድሶን ለማምጣት፣ ቤተ ክርስቲያን እንደገና መንፈስ ቅዱስን እንድታዳምጥና ነገሮችን ግትር ባልሆነ መንገድ እንድታከናውን ለማገዝ በየጊዜው የእግዚአብሔርን ፊት መሻት አለበት። ለብዙ ዓመታት የተገነቡት ልማዶች ተመዝነው በዓላማ ተግባራዊ ሊሆኑ ወይም ሊወገዱና በምትካቸው ሌሎች ነገሮች ሊከናወኑ ይገባል። ግትር በሆነ መንገድ መቀጠል ማለት የደረቀ ዛፍ እንደ መሆን ነው። እንዲህ ዓይነቱ ዛፍ ቆሞ ሊታይ ቢችልም፣ አንድ ቀን መውደቁ የማይቀር ነው።

2. ቤተ ክርስቲያን፣ እንደ ድርጅት፣ አገልግሎቶቿን የሚመሩትንና የተለያዩ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት ከመሪዎች ጋር ግንኙነት እንደሚያደርጉ የሚያሳዩትን የአመራር መዋቅሮች ታዘጋጃለች። እያንዳንዱ ቤተ እምነት የሽማግሌዎችን ብዛት፣ የመጋቢን አስፈላጊነት ወይም አለማስፈለግ፣ የወጣቶች የአገልግሎት ዘርፍ፣ የሴቶች የአገልግሎት ዘርፍ፣ ወዘተ. . . ይወስናል። በተጨማሪም ቤተ ክርስቲያን የተወሰኑ ነገሮችን ለማከናወን አገልግሎቶችን ትመሠርታለች። ለምሳሌ ያህል፣ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት የመዘምራን ቡድን፣ የልጆች የሰንበት ትምህርት ቤቶች፣ የልማት ፕሮግራሞች፣ ወዘተ. . . አሏቸው። እነዚህ አገልግሎቶች የሚጀመሩት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድን ጠቃሚ አገልግሎት ለማካሄድ በሚያስችል ስልታዊ ፍላጎት መሠረት ነው። እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተ ግባራት የሚካሄዱባቸውን መንገዶች የሚወስኑ ደንቦችም ይወጣሉ። ለምሳሌ፣ በዕለተ ሰንበት ምን ዓይነት አምልኮ



እንደሚያደርጉ ይወስናሉ። በየሳምንቱ ቅዳሜ ማታ የሽማግሌዎች ስብሰባ ይካሄዳል የሚል ደንብም ሊያወጡ ይችላሉ።

እነዚህ ሁሉ መዋቅሮች፣ አገልግሎቶችና ደንቦች የሚጀመሩት ግልጽ ዓላማ ኖሯቸው ነው። ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ እነዚህ ነገሮች ልማድ ይሆኑና ቤተ ክርስቲያን ከጊዜው ጋር እየተለወጠ የሚሄደውን የምእመናን ፍላጎት ለማሟላት ሳትችል ትቀራለች። ቤተ ክርስቲያን የአመራር መዋቅሯን በመመርመር አዳዲስ ተ ግዳሮቶችን ለማሟላት መቻሉን አትፈትሽም። ለምሳሌ፣ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ለሙሉ ጊዜ መጋቢዎች ደመወዝ መክፈል አይፈልጉም። ምክንያቱም ከዚህ በፊት አድርገውት ስለማያውቁ ነው። ሽማግሌዎቹ የሚያስቡት፣ «ልክ እንደ እነርሱ እያረሱ በትርፍ ጊዜያቸው ማገልገል እንዳለባቸው ነው።» ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን ምእመናን ቁጥር በመብዛቱ ምክንያት፣ አገልግሎቱ በትርፍ ጊዜ ሊከናወን የማይችል ከሆነስ? ከዚህ በፊት እንደ ነበ ረው መጋቢው ገበሬ ባይሆንስ? አብያተ ክርስቲያናት በቤተ ክርስቲያንና በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚታዩትን ለውጦች (የኑሮ ውድነት፣ የትምህርት ቤት ክፍያ፣ ወዘተ. . .) የማይገነዘቡ ከሆነ፣ መጋቢው በአግባቡ እያገለገለ እንዲኖር የሚያስችል ተመጣጣኝ ደመወዝ ሊከፍሉት አይችሉም። ይህ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን ለችግር ያጋልጣታል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለረዥም ዓመታት የኖሩ ሰዎች «ሁልጊዜም እንዲህ ስናደርግ ነበር» ለማለት ይሽቀዳደማሉ። ወይም ደግሞ ሽማግሌዎች በየሳምንቱ አርብ ማታ ለጸምና ጸሎት ለመሰባሰብ ይወስናሉ። ብዙም ሳይቆይ፣ ሽማግሌ ዎች ለምን መጸምና መጸለይ እንዳለባቸው ሳያውቁ ሥርዓቱን መከተላቸውን ይቀጥላሉ። ወይም ደግሞ ቤተ ክርስቲያን በማኅበ ረሰቡ ውስጥ ያሉትን ወጣቶች በወንጌል ለመድረስ በማሰብ የስፖርት ፕሮግራም ትጀምራለች። ከጊዜ በኋላ ያልዳኑ ወጣቶች ባይሳተፉበትም እንኳን፣ ፕሮግራሙ ይቀጥላል። ይህ ቀጣይነት ያለው ፕሮግራም በመሆኑ፣ ሽማግሌዎች ምን ያህል ውጤታማ እንደ ሆነ፣ መቆም ወይም እንዴት መሻሻል እንዳለበት አያስቡም።

እንድ መዋቅር፣ አገልግሎት ወይም ደንብ እየቆየ በሚሄድበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ እምብዛም መንፈስ ቅዱስን አያዳምጡም:: ቤተ ክርስቲያን በእድሜ እየገፋች በምትሄድበት ጊዜ፣ ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ለማስገባት ትቸገራለች:: ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነገሮችን ስለ መለወጥ አያስቡም:: እስተዋይ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መዋቅሮቻቸውን፣ እገልግሎቶቻቸውንና ደንቦቻቸውን በየጊዜው በመመርመር እግዚአብሔር እንዴት እንዲያድሱ እንደሚፈልግ ይገነዘባሉ::

3. ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚእብሔር በሚመሠርተው ዘላቂ ነገርና እኛ የእግዚአብሔርን ሥራ ለማከናወን በምንመሠርታቸው ጊዜያዊ ዘዴዎች መካከል ያለውን ልዩነት አይገነዘቡም:: ለምሳሌ፣ እግዚአብሔር ሁልጊዜም ልጆቹ እንዲያመልኩት ይፈልጋል:: ስለዚህ እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርን ማምለክ አለባት:: ነገር ግን አምልኮአችንን የምንገልጽበት መንገድ ከቦታ ቦታ ወይም ከወቅት ወቅት ሊለያይ ይችላል:: እንዳንዶች እጆቻቸውን ወደ ላይ በማንሣት፣ በማጨብጨብ፣ በአምልኮ መሪዎች በመጠቀም፣ መዘምራን ከፕሮግራሙ መጀመሪያና መጨረሻ ላይ እንዲዘምሩ በማድረግ፣ ወዘተ. . . ሲያመልኩ ይችላሉ:: እነዚህ ለአምልክ ልንጠቀም የምንችላቸው ጊዜያዊና ሰው-ሠራሽ ዘዴዎች ናቸው:: ችግር የሚፈጠረው ማጨብጨብ ቋሚ የአምልኮ መንገድ ነው ስንል፣ ወይም ማጨብጨብ ላናስብ የምናደርገው ልማድ ሲሆን ነው:: ወይም ደግሞ ማምለክ የሚቻለው መዘምራን ሲኖሩ ብቻ ነው ካልን፣ ችግር ውስጥ ነን ማለት ነው:: በአምልኮ ውስጥ ሁልጊዜም አክብሮትና ሥርዓት መኖር አለበት:: (1ኛ ቆሮ. 14:40ን እንብብ::) አንዳንድ ጊዜ ግን የምንጠቀምበት የእምልኮ ቅደም-ተከተል አስፈላጊ ነው ብለን እናስባለን:: ይህም ቅደም ተከተል ከሕዝብ ዝማሬ ወደ መዘምራን ዝማሬ፣ ከዚያም ወደ መባ መሰብሰብ፣ ወደ ስብከት፣ ሰዎች በክርስቶስ እንዲያምኑ ጥሪ የማድረግ፣ እንደገና ወደ መዘምራን፣ ወደ መጨረሻ መዝሙርና የአባታችን ጸሎት የሚመራን ነው:: አንድ ድርጅት ወይም ቤተ ክርስቲያን ማደግ የምታቆመው እነዚህ ጊዜያዊ ነገሮች ቋሚ ናቸው ብለን ስናስብ



ነው:: ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ ተለዋዋጭ ለሆኑት ሁኔታዎችና ለሰዎች ፍላጎቶች በሚስማማ መንገድ እገልግሎትን ማቅረቡ ይቀርና ግትርነት ይለፍናል::

**11ኛ ጥያቄ:-** ሀ) የቤተ ክርስቲያናችሁን ልማዳዊ የአምልኮ ቅደም-ተከተል ግለጽ:: ለ) ሰዎች ይህንን የአምልኮ ቅደም-ተከተል የተከተሉት ለምን ያህል ጊዜ ነው? ሐ) ባለፉት አምስት ዓመታት በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ምን ዓይነት ለውጦችን ታዝበሃል? እነዚህን ለውጦች ያመጣቸው ምንድን ነው? ለውጡ የመጣው በዕቅድ ነው ወይስ በአጋጣሚ? ሠ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ነገሮች ወደ ልማድነት በመቀየራቸው ምክንያት ሰዎች ሳያስቡ ዝም ብለው የሚያደርጓቸው እንዴት ነው? ይህ አደገኛ የሚሆነው ለምንድን ነው?

4. እንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መዋቅሮች ቤተ ክርስቲያንን የማያገለግሉና እንዲያውም መሪዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ አመራር እንዲሰጡ የሚያስገድዱ አደገኛ ነገሮች ናቸው:: አንድ ቤተ እምነት አብያተ ክርስቲያናቱ ሁሉ አንድ ዓይነት ሥርዓት እንዲከተሉ በመፈለግ ወይም ባህላዊ የአመራር ዘዴ በመከተሉ ምክንያት፣ የሽማግሌዎች ሰብሳቢ ውሳኔዎችን ሁሉ እንዲሰጥ የሚያደርግ ከሆነ፣ ይህ ደንብ መሪው ለሰዎች የእረኝነት አገልግሎት የሚሰጥ እገልጋይ መሪ ሳይሆን፣ አለቃ እንዲሆን ይገፋፋዋል:: ሰዎች እርሱ የሚናገረውን ብቻ ስለሚሰሙ፣ ኢየሱስን የመስማት ዕድል አይኖራቸውም:: እንዲሁም ደግሞ የቤተ ክርስቲያን እስተዳደር የእገልግሎት መሪዎች (ለምሳሌ፣ ወንጌላውያን፣ የሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪዎች) ለሚያከናውኗቸው ነገሮች ሁሉ ፈቃድ እንዲጠይቁ የሚያደርግ ከሆነ፣ እገልጋዮች መንፈስ ቅዱስን ከመስማት ይልቅ አለቆቻቸው የሚነግሯቸውን ብቻ ለማከናወን ይገደዳሉ:: የትኛውም የቤተ ክርስቲያን መዋቅር የእግዚእብሔርን ሥራ ለማከናወን የሚያግዝ መሣሪያ ብቻ ነው:: መዋቅሩ በቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ምእመናን መካከል ክፍተት በሚፈጥርበት ጊዜ፣ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን ከማዳመጥ ይልቅ ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ፈቃድ እንዲጠይቁ ሲያደርግ፣ ወይም ምእመናን ቁጭ ብለው አገልጋዮች ሲሠሩ እንዲመለከቱ ሲያደርግ፣ ይህ መዋቅር የእግዚአብሔርን

ሥራ የሚያደናቅፍ መሣሪያ ሆኗል ማለት ነው:: የትኛውም የቤተ ክርስቲያን መዋቅር እግዚአብሔር ለዘላለም እንዲኖር የፈጠረው አይደለም:: ስለሆነም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሁልጊዜም መዋቅራቸውን በመገምገም በማኅበረሰባቸው ውስጥ የእግዚአብሔርን ሥራ ለማከናወን ምርጥ መሣሪያ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው::

5. አብያተ ክርስቲያናት በሚገባ በመደራጀታቸው ምክንያት የተፈጠሩትን ነገሮች ለመዳሰስ የሚያስችል የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ምሳሌ:-

ሀ. ኢየሱስ በአይሁዶች ላይ ተሐድሶ ለማምጣት በፈለገ ጊዜ፣ ሰዎች ሰው-ሠራሽ ደንቦችን እንዲከተሉ የሚጠይቀው ግትር ሃይማኖታዊ ሥርዓት ገጠመው:: ኢየሱስ ትውፊቶችን ለመከተል ባለመፈለጉ፣ የሃይማኖት መሪዎች እንደ ጠላት ቆጠሩት፣ በመጨረሻም ገደሉት:: የቤተ ክርስቲያን ትውፊት በጣም ግትር በመሆኑ ምክንያት፣ እግዚአብሔርን ለመስማት በማይችልበት ጊዜ ምን ዓይነት ችግር እንደሚከሰት ለማሳየት ይህ ጥሩ ምሳሌ ነው::

ኢየሱስ አዲስ የእግዚአብሔር ሕዝብ (ቤተ ክርስቲያን) መሥርቷል:: ቤተ ክርስቲያንን የመሠረተው ሰዎች በልባቸው ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት ላይ እንዲያተኩሩና መንፈስ ቅዱስን እንዲያዳምጡ ለማገዝ ነው:: ሰዎች በውጫዊ ድርጊቶች ላይ ትኩረት እንዳይሰጡ አስተምሯቸዋል:: መሪዎች የሕዝቡ እረኞችና አገልጋዮች እንጂ፣ «አለቆች» አለመሆናቸውን ገልጾአል::

ለ. በሐዋርያት ዘመን፣ ቤተ ክርስቲያን አሠራሯ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል መዋቅር አላዘጋጀችም:: ቤተ እምነት ለመፍጠር አልሞከሩም:: ሐዋርያት የፈለጉት የኢየሱስ ተከታዮች የፍቅር ማኅበረሰብ እንዲሆኑ በማድረጉ ተግባር ላይ ነበር:: ምእመናን የእግዚአብሔርን ቃል በማወቅና መንፈስ ቅዱስን በማዳመጥ እንዲያድጉ ጥረት አድርገዋል:: ሐዋርያት እያንዳንዱ አማኝ በእኩል የሚታይበትንና ሁሉም ማኅበረሰቡ በመንፈሳዊ ብስለትና በቁጥር የሚያድግበትን የፍቅር ማኅበ



ረሰብ ለመገንባት ተግተው ሠርተዋል:: መሪዎች ከአገልግሎታቸው ክብር ወይም ሀብት ለማግኘት ሳይሞክሩ፣ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው አገልግለዋል:: ከአስተዳዳሪዎች ይልቅ እንደ አፍቃሪ አባቶች ነበር የሠሩት:: ብዙውን ጊዜ ምእመናንን «ወዳጆች» (ቈላ. 3:12)፣ እንዲሁም «ልጆች» (1ኛ ዮሐ. 4:4) ብለው ይጠሩ ነበር::

ሐ. ከ100-300 ዓ.ም፣ ቤተ ክርስቲያን መለወጥ ጀመረች:: ክርስቶስን በመከተልና ከእግዚአብሔር ጋር መልካም ግንኙነት ከመመሥረት ይልቅ፣ በጥሩ ሁኔታ የሚንቀሳቀስ ሃይማኖት በመመሥረቱ ላይ ትኩረት ይደረግ ይጀመር:: መሪዎች የአይሁድ ምኩራቦችን ወይም የሮም መንግሥታትን መዋቅሮች የሚመስሉ አደረጃጀቶችን መከተል ጀመሩ:: የሐሰት ትምህርት ሲገጥማቸው በጠበቀ ሁኔታ ሰዎችን የሚቆጣጠሩበትን መንገድ መፈለጉ ጀመሩ:: ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እስከ ጳጳሱ ድረስ በተዋረድ መሪዎች ሥልጣን ላይ እንዲቀመጡ አደረጉ:: ለቤተ ክርስቲያን ሕጎችንና ደንቦችን ማውጣት ጀመሩ:: ሰዎችን እነዚህን ደንቦች በሚጥሱበት ጊዜ ቅዱስ ቁርባን እንዳይወስዱ በመከላከል ይቀጧቸው ጀመር:: ይህም የመሪዎችን ኃይል እያጠናከረው ሄደ:: በመሆኑም፣ መሪዎች ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲከተሉና መንፈስ ቅዱስን እንዲያዳምጡ ከማድረግ ይልቅ፣ ለማስገደድ ያወጧቸውን ሕግጋት መጠቀም ጀመሩ::

መ. ከ300-1500 ዓ.ም፣ የቤተ ክርስቲያን በዚህ መንገድ መደራጀት ቤተ ክርስቲያን ለመሪዎች ትልቅ ሥልጣን በመስጠቱ፣ ምእመናን እግዚአብሔርን በማዳመጥ እርሱ የሚፈልገውን ነገር የሚያከናውኑበት ሁኔታ እየቀነሰ እንዲመጣ አደረገ:: በዚህ ጊዜ በሰዎች ላይ ሙሉ ቁጥጥር ለማድረግ የሚፈልጉ ቀሳውስት፣ ጳጳሳትና ሊቀ ጳጳሳት ተነሥተው ነበር:: ሰዎች ኢየሱስን ሳይሆን፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ለመከተል መጣር ጀመሩ:: ሊቀ ጳጳሱ የቤተ ክርስቲያን ራስ በመሆን ኢየሱስን ተክቶ ተገኘ:: ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ የክርስቶስ አካል መሆኗ ቀርቶ፣ የንግድ ወይም የፖለቲካ ድርጅት መሰለች:: ምእመናን በተግባራቸውና በአስተሳሰባቸው ከዓለም ለመለየት ሳይችሉ ቀሩ:: የተወሰኑ

ደንቦችን እስከ ጠበቁ ድረስ (ለምሳሌ፣ ረቡዕ እና አርብ ሥጋ እስካልበሉ)፣ እግዚአብሔር በእነርሱ ደስ የተሰኘ መሰላቸው:: ብዙውን ጊዜ እንደ ሰው ኢየሱስን በትክክል መከተል አለመከተሉን መረዳቱ አስቸጋሪ ነው:: ሰዎች ኢየሱስን ባይከተሉና ትምህርቱን ባይከተሉም፣ «ክርስቲያኖች» መባላቸው ብቻ በቂ ነው ብለው ያስቡ ነበር::

ሠ. በ1517 ዓ.ም:- የፕሮቴስታንት ተሐድሶ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በአደረጃጀት ሂደት ያበላሸቻቸውን ብዙ ነገሮች ለማስተካከል ሞከረ:: ሉተርና ሌሎችም የተሐድሶ መሪዎች ሰዎች መሪዎችን ጣልቃ ሳያስገቡ እግዚአብሔርን በቀጥታ እንዲያዳምጡ አበረታቷቸው:: ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ አንብበው ፈቃዱን እንዲረዱ ለማስቻል መጽሐፍ ቅዱስን ወደሚታወቁ የሕዝብ ቋንቋዎች የተረጎሙ ሰዎች ካቶሊኮች ባስነሡት ስደት ተገደሉ:: የተሐድሶ መሪዎች ጥቂት ካህናትን ከመጠበቅ ይልቅ አማኞች ሁሉ የእግዚአብሔር ካህናት እንደ መሆናቸው፣ እግዚአብሔርን ማገልገል አለባቸው የሚል አቋም ያዙ::

ረ. ከ1517 እስከ አሁን ድረስ:- የተሐድሶ፣ ቤተ እምነታዊ አደረጃጀት፣ ግትር መሆንና ኢየሱስን አለማዳመጥ፣ ከዚያም ሌላ የተሐድሶ እንቅስቃሴ ማካሄድ ቀጥሎ ይገኛል:: ከ500 ዓመታት በፊት እንደ ሉተርና ካልቪን ያሉ የተሐድሶ መሪዎች የመሠረቷቸው ነገሮች አሁን የለውጥ ምልክት ባለማሳየት ሰዎች ኢየሱስን ከመከተል ይልቅ ለቤተ እምነታቸው ታማኞች እንዲሆኑ በማበረታታት ላይ ይገኛሉ:: የጴንጠቆስጤና የካሪዝማቲክ (እንደ ሙሉ ወንጌል ያሉ) ንቅናቄ እየደረቁ በሄዱት የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ላይ ተሐድሶ ለማምጣት የተደረገ ጥረት ነበር::

ከላይ እንደ ተመለከትነው፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በቤተ ክርስቲያን እድገት ውስጥ የተወሰነ ሂደት መኖሩን ያሳየናል:: ሰዎች መንፈስ ቅዱስን ያዳምጣሉ፣ እግዚአብሔር የሚላቸውን ነገሮች ይሰማሉ፣ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ያከብራቸውና ያድጋሉ:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መሥዋዕትነት በመክፈል ምእመናን እንዲያድጉ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ:: ሁሉም ለቤተ



ክርስቲያን እድገት ስለሚሠራ፣ ፍቅርና አንድነት ይኖራል:: ቤተ ክርስቲያን እየበለጸች ስትሄድ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይመረጣሉ፣ መዋቅሮችና አገልግሎቶች ይመሠረታሉ፣ ደንቦች ይወጡና ቤተ ክርስቲያኒቱ ወደ ተቋማዊነት ታድጋለች:: በዚህ ጊዜ ምእመናን ከመንፈስ ቅዱስና ከእግዚአብሔር ይልቅ መሪዎቻቸውንና ደንባቸውን ይከተላሉ:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በኃይልና ሥልጣን እያደጉ ሲሄዱ፣ ምእመናን አብዛኛውን ሥራ እነርሱ እንዲያከናውኑ ይጠብቃሉ:: የቤተ ክርስቲያን መሪነት ዝንባሌ ያላቸው ሰዎች የመሪነትን ሥልጣን ለመጨበጥ ይሟሟታሉ:: ሥልጣኑን ከያዙ በኋላም፣ ላለመውረድ የሚችሉትን ጥረት ሁሉ ያደርጋሉ:: ጊዜው እየገፋ ሲሄድ፣ ተጨማሪ ደንቦችና ሕጎች ይወጡና ምእመናን እግዚአብሔርን ከመታዘዝና ፈቃዱን ከመፈጸም ይልቅ፣ ትውፊታቸውን በመጠበቅ ላይ እንዲያተኩሩ ይደረጋል:: በመጨረሻም፣ እግዚአብሔር የተሐድሶ ተግባር ማከናወን ይጀምራል:: ብዙውን ጊዜ ግን በኢየሱስ ዘመን እንደ ነበሩት አይሁዶች ወይም በማርቲን ሉተር ዘመን እንደ ነበሩት ካቶሊኮች በአገልግሎት ላይ የቆዩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለውጥ እንዲመጣ አይፈልጉም:: በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር አንድን ሰው አስነሥቶ ሙሉ በሙሉ አዲስ ሥራ በመሥራት ሰዎች ለለውጥ እንዲነሣሡና መንፈስ ቅዱስን እንዲያዳምጡ ያደርጋል::

> 12ኛ ጥያቄ:- ሀ) ቤተ ክርስቲያን ከላይ በተጠቀሰው መንገድ ከፍቅር ማኅበረሰብነት ወደ ተቋማዊነትና ክርስቶስን ከመከተል ይልቅ በትውፊቶች ላይ የምታተኩር የምትሆንበትን ሁኔታ እንዴት እንደ ታዘበክ ግለጽ:: ለ) ይህ የተለመደ ዓይነት ሁኔታ በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ እንዳይፈጸም ምን ልታደርግ ትችላለህ?

በእድሜ የገፋና በትውፊቶች የታጠረ ቤተ ክርስቲያን ወይም ቤተ እምነት ውስጥ ብንሆን ምን ማድረግ ይኖርብናል?

ሀ. አብያተ ክርስቲያናት የሚያልፉበትን የተፈጥሮ ሂደት ማወቅ አለብን:: አብያተ ክርስቲያናት ለውጥን እንዳይቀበሉ የሚያደርጓቸውን ነገሮች ልንቀርፍ የምንችለው ይህንን ሁኔታ ስናውቅ ብቻ ነው::

ለ. ሰዎች በትውፊትና የቤተ ክርስቲያን አባልነት ላይ እንዲያተኩሩ የሚያደርገውን ተቋማዊነት መከላከል አለብን:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሁልጊዜም ምእመናን ሰሰውጥ የተዘጋጁና መንፈስ ቅዱስን የሚያዳምጡ እንዲሆኑ ማበረታታት አለባቸው:: የቤተ ክርስቲያናችን ትውፊቶች ወይም ደንቦች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እኩል ናቸው በምንልበት ጊዜ ለውጥን መቃወማችን ነው::

ሐ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምእመናን የፈጠራ ጥበባቸውን በመጠቀም እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ መፍቀድ አለባቸው:: መሪዎች በነገሮች ክንውን ውስጥ የተለያዩ የአሠራር መንገዶች እንዲኖሩ መፍቀድ አለባቸው:: በመሆኑም፣ የአምልኮ መሪዎች ቀደም ሲል ይካሄድ ከነበረው በተለየ መንገድ ነገሮችን እንዲያከናውኑ ቢፈቅዱ መልካም ነው:: ወይም ደግሞ «አባታችን ሆይ» የሚለውን ጸሎት መጸለይ ሊያቆሙና ሰዎች የጸሎቱን ትርጉም እንዲረዱ ሊያብራሩላቸው ይችላሉ፡

መ. በየጊዜው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የምእመናንን ልምምዶች በማጤን ሰዎች ሳያስቡ የሚያደርጓቸውና ወደ ልማዳዊነት የተለወጡ ነገሮች ካሉ መመልከት አለባቸው:: ጸሎታችን ወደ ልማድ በመቀየሩ፣ በልባችን ያለውን ሳይሆን የተለመደውን ጸሎት እየጸለይን ነው? እንዲህ ዓይነት ነገር ካለ፣ ችግሩን ለማስወገድ የሚቻልባቸውን እርምጃዎች እንወስዳለን:: ይህም አዳዲስ የአሠራር መንገዶችን መፍጠርን ወይም ሰዎች ምክንያቱን እንዲያውቁና በልማድ ሳያስቡ እርምጃ ከመውሰድ እንዲቆጠቡ ማድረግን ሊያካትት ይችላል:: በመሆኑም፣ መዘምራን ከስብከት በፊትና በኋላ ሁለት ሁለት መዝሙሮችን እንዲዘምሩ ከማድረግ ይልቅ፣ አንዳንድ ቀን ምእመናኑ ብቻ እንዲዘምሩ ማድረግ ይቻላል:: የቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅሮችንም በመመርመር ማሻሻያዎችን ማድረግ ይቻላል:: የቤተ ክርስቲያንን መዋቅሮችና ልምምዶች በመመርመር የምእመናንንና ተለዋዋጭ የሆኑትን የማኅበረሰብ ፍላጎቶች እንዲያሟሉ አድርገው ሊያስተካክሉ ይችላሉ::



ሠ. መሪዎች እግዚአብሔር በመካከላቸው አዲስን ነገር እንዲያደርግ ሳያቋርጡ መጸለይ ይገባቸዋል:: የእግዚአብሔር መንፈስ አምልኮውና የሕዝቡ ተግባራት ባሉበት እንዲረጉ አይፈልግም::

ረ. ሰዎች የቤተ ክርስቲያን አባላት ብቻ ሳይሆኑ፣ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርትም እንዲሆኑ ማስተማር አስፈላጊ ነው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መንፈሳዊነትን ያሳያል የሚሏቸውን ሕግጋት (ለምሳሌ፣ ወደ ሲኒማ ቤት እንዳትሄዱ ማለት) ከመደንገግ መቆጠብ አለባቸው:: ከዚህ ይልቅ፣ ምእመናን በሙሉ ልባቸው እግዚአብሔርን እንዲወድዱና ሌሎች ሰዎችን ልክ እንደ ራሳቸው አድርገው እንዲወድዱ ማስተማር ይኖርባቸዋል:: በዚህ ጊዜ ሰዎች ለኢየሱስ ያላቸውን ፍቅር የማያንጸባርቁትን ወይም ሌሎች ሰዎችን የሚጎዱትን ተግባራት ከመፈጸም ይቆጠባሉ::

ሰ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሁለተኛና ሦስተኛ ትውልድ ክርስቲያኖች ሕይወታቸውን ለክርስቶስ ሳይሰጡ «ክርስቲያኖች» ወይም «አማኞች» ነን በሚል ብቻ ረክተው እንዳይቀመጡ ማበረታታት ይኖርባቸዋል:: ብዙውን ጊዜ ከኢየሱስ ጋር ግላዊና እያደገ የሚሄድ ግንኙነት ሳይፈጥሩ እምነትን ወደ ልማድ የሚቀይሩት እነዚህ ሁለተኛና ሦስተኛ ትውልዶች ናቸው::

13ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያናችሁን አገልግሎቶች፣ መዋቅሮችና የተለመዱትን ልምምዶች መርምር:: የምትመለከታቸውን የግትርነትና ለመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ክፍት ያለመሆን ምልክቶችን ዘርዝር:: ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህንን ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ ለማስወገድ ሊያደርጉ የሚችሏቸውን ነገሮች ዘርዝር:: ሐ) ቤተ ክርስቲያናችሁ ለመንፈስ ቅዱስ አሠራር ክፍት እንድትሆን ጸልይ::

## የመሪነት ሥልጠና በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ

በመደበኛ ትምህርት ላይ ከፍተኛ ትኩረት ለሚያደርጉ የዘመናችን ሰዎች፣ እግዚአብሔር በታሪክ ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ለማሠልጠን ትምህርት ቤቶችን አለመምረጡን ለመገንዘብ ሊቸገሩ ይችላሉ:: በአብዛኛው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሥልጠና የሚያገኙት ልምድ ካላቸው ቀደምት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነበር።

1. የመሪነት ሥልጠና እስከ 16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን፡-

ሀ. ከ100-500 ዓ.ም፡- የተለመደው የመሪነት ሥልጠና እግዚአብሔር ለአገልግሎት የጠራቸው ሰዎች፣ ልምድ ባላቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሥር ሥልጠና የሚያገኙበት ነበር። ልክ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ እንዳደረገው፣ በማስተማር ወይም በክህነት ለማገልገል የሚፈልጉ ሰዎች በሌላ የቤተ ክርስቲያን መሪ ሥር ያገለግላሉ። ልምድ ያለው መሪ የአዲሱን አገልጋይ የእግዚአብሔር ቃል አጠናን ሁኔታ ይከታተላል። ልምድ ያለው መሪ መንፈሳዊ መሪ ማለት ምን እንደ ሆነ ያሳየዋል። የእግዚአብሔርን ቃል ጥናት፣ የጸሎት፣ የጾም፣ የምስክርነት፣ ወዘተ. . . መንገዶችንም ያሳየዋል። እንዴት ማገልገል እንዳለበት ካሳየው በኋላ፣ ኃላፊነት ይሰጠዋል። ተማሪው በእግዚአብሔር ቃል መረዳት፣ በመንፈሳዊ ባሕርይና በአገልግሎት ክህሎት ብቁ ሆኖ ሲገኝ፣ በአነስተኛ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የማገልገል ዕድል ይሰጠዋል። የመሪነት እድገቱ የሚመጣው የበለጠ ኃላፊነት ለመቀበል እንደሚችል በሥራው ሲያስመሰክር ነው።

ለ. ከ500-1600 ዓ.ም፡- የሰሜን አውሮፓ (ጀርመን) ጎሳዎች ግዛቱን በመውረር፣ ባሮችን በመውሰድ፣ አብያተ ክርስቲያናትን በማውደም፣ ወዘተ. . . በሮም ግዛት ላይ ጥቃት በመሰንዘራቸው፣ ግዛቱ እየተዳከመ መጣ። መረጋጋት እየጠፋ በመሄዱ፣ ቤተ ክርስቲያን የወደፊት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናት ለአገልግሎት የሚዘጋጁበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ስትል ትናንሽ ማኅበረሰቦችን (ገዳማትን) አቋቋመች። በእነዚህ ገዳማት ውስጥ አዳዲስ ካህናት ልምድ ካላቸው አባቶች የእግዚአብሔርን ቃል ይማሩ ነበር። አገልግሎትንም የሚማሩት በሥራ ላይ ሥልጠና አማካኝነት ነበር። እነዚህ ገዳማት ለትምህርት ቤቶች መጀመር ፈር-ቀዳጆች ነበሩ ማለት ይቻላል። መደበኛ የአመራር ሥልጠና ለመስጠት የማኅበረሰቡ አለመረጋጋት እንከን በፈጠረበት ወቅት፣ እግዚአብሔር የመሪዎችን የአገልግሎት



ዝግጅት ለመቀጠልና ቅዱሳት መጻሕፍትን ጠብቆ ለማቆየት እነዚህን ገዳማት ተጠቅሟል። የኋላ ኋላ እነዚህ ስፍራዎች መደበኛ የመሪነት ሥልጠና መስጫዎች ሆኑ። ምንም እንኳን አንዳንድ ሥልጠናዎች በገዳማት ውስጥ ቢካሄዱም፣ አብዛኞቹ ሥልጠናዎች በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ይካሄዱ ጀመር። አዳዲስ ካህናት የአገልግሎት ኃላፊነት ከመቀበላቸው በፊት ልምድ ካላቸው ካህናት ሥር ይሠሩ ነበር። ማንኛውም ካህን ከገዳም መጥቶ ዋና ካህን እንዲሆን አይደረግም ነበር። መጀመሪያ ከአሠልጣኙ መማርና ችሎታውን ማሳየት ይጠበቅበት ነበር። ችሎታው እያደገ ሲሄድ ነበር ኃላፊነቱ ከትንሽ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይነት ወደ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይነት እየጨመረ የሚሄደው። በአገልግሎቱ እያደገ የሚሄደው የአገልግሎት ክህሎቶቹና የአመራር ችሎታው እያደገ ሲሄድ ነበር። ይህ የረዥም ጊዜ አገልግሎት ሽልማት ተደርጎ የሚሰጥ ነገር አልነበረም። በዚህ ጊዜ ካህናት እንዲያገቡ አይፈቀድላቸውም ነበር። ይህ ደግሞ እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ሙሉ ትኩረታቸውን ለአገልግሎታቸው እንዲሰጡ ያስችላቸው ነበር።

2. የመሪነት ሥልጠና ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ 19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን።

ሀ. የዩኒቨርስቲ ሥልጠናዎች፡- የፕሮቴስታንት ተሐድሶን ተከትሎ በአውሮፓ ሁሉ ለትምህርት ከፍተኛ ትኩረት ይሰጥ ጀመር። ፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት እግዚአብሔር የሁሉም እውነት ምንጭ መሆኑን ስለሚያምኑ፣ እርሱ የፈጠረውን ዓለም ማጥናቱ እግዚአብሔርን ያስከብረዋል የሚል እምነት አላቸው። የሳይንስ ዘመን ተወለደ። ከሁሉም በላይ ግን ፕሮቴስታንት አገሮች ትምህርት ለቤተ ክርስቲያን ጤንነት ወሳኝ ነው የሚል እምነት ነበራቸው። አማኞች ሁሉ ካህናት ናቸው የሚለውን ትምህርት ተከትሎ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ አማኞች የእግዚአብሔርን ቃል በራሳቸው ቋንቋ አንብበው የእግዚአብሔርን ቃል እንዲያውቁ ማበረታቻ ተሰጣቸው። መጽሐፍ ቅዱስን በተራው ሕዝብ ቋንቋ ለማሳተም ከፍተኛ ጥረት ይደረግ ነበር። በመሆኑም፣ ማርቲን

ሉተር መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ጀርመንኛ ሲተረጉም፣ ዊክሊፍ ደግሞ ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ተረጎመው::

የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት አገልግሎቶች እውነትን በመረዳት ሊጠቀሙ ይገባል የሚል አቋም ነበራቸው:: በዚህም መሠረት ዩኒቨርስቲዎች ተከፈቱ:: በአሜሪካና በአውሮፓ ካሉት ዩኒቨርስቲዎች ብዙዎቹ የተጀመሩት አገልጋዮች ማኅበረ ምእመናንን በተሻለ ሁኔታ እንዲመሩ ለማስቻል ነበር:: በዚያን ጊዜ የሥነ-መለኮት ጥናት ትልቁ ትምህርት ተደርጎ ሲታይ፣ ሥነ-መለኮት «የሳይንስ ንጉሥ» ይባል ነበር::

ይህ የዩኒቨርስቲዎች መጀመር በመሪነት ሥልጠና ላይ አዲስ ለውጥ አምጥቷል:: አገልጋዮች እንደ ፍልስፍና ባሉት ንድፈ-አሳባዊ እውቀቶች ላይ ትኩረት ማድረግ ጀመሩ:: ይህ ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ትኩረት እንዳያደርጉ ወይም ደግሞ ልምድ ካላቸው አገልጋዮች የመንፈሳዊ አመራርን ክህሎቶችና ባሕርያት እንዳይማሩ አደረጋቸው:: በሥነ-መለኮት ከፍተኛ ዲግሪዎችን የሚያገኙ ሰዎች በአመዛኙ የፍልስፍና ዲግሪዎችን ያገኛሉ:: ይህንን ከሕክምና ትምህርት ጋር ልናነጻጽረው እንችላለን:: አንድ ሐኪም ንድፈ-አሳባዊ ነገሮችን ይማራል:: በተጨማሪም፣ በሆስፒታል ውስጥ ልምድ ባለው ሐኪም ሥር በመሥራትም ልምድ ያገኛል::

ሰ. ልምድ ካላቸው አገልጋዮች ሥልጠና ማግኘት:- አንዳንድ አገልጋዮች በዩኒቨርስቲዎች ውስጥ በመማር በትላልቅ የከተማ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ለመሆን ቢችሉም፣ አብዛኞቹ የገጠር አገልጋዮች ሥልጠና የሚያገኙት ልምድ ካካበቱ አገልጋዮች ነበር:: እንደ ቀደመው ታሪክ ሁሉ፣ አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የእግዚአብሔርን ቃል የሚማሩት ልምድ ካላቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነበር:: እነዚህ መሪዎች ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አስፈላጊ የሆነውን ባሕርይና ክህሎት ጭምር ያስተምሩ ነበር:: ትምህርቱን ያገኙ አዳዲስ አገልጋዮች ወደ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ሄደው በመጋቢነት ያገለግሉ ነበር::



3. የቤተ ክርስቲያን አመራር ሥልጠና ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ አሁን:-

አብዛኞቻችን ዛሬ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች፣ ኮሌጆችና ሴሚናሪዎች የምናገኘው ዓይነት ሥልጠና ከድሮ ጀምሮ ሲሰጥ እንደ ነበረ እናስባለን:: እንዲያውም፣ ከመደበኛ ትምህርት ቤት ከፍተኛ የአገልግሎት ክህሎት የምናገኝ ነው የሚመስለን:: በኢትዮጵያም ሆነ በዓለም ዙሪያ ካሉት ሰዎች በሺዎች የሚቆጠሩት፣ «መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብቼ መሠልጠን አለብኝ» ይላሉ:: ነገር ግን ከቤተ ክርስቲያን መሪነት ሥልጠና አሰሳችን እንደ ተመለከትነው፣ እግዚአብሔር በዓለም ሁሉ ያለ መደበኛ ትምህርት ቤት መሪዎችን አሠልጥኗል:: ሰዎች ልምድ ባላቸው ሰዎች እንዲሠለጥኑና የአገልግሎት ክህሎቶችን እያገኙ በመሄድ ከፍተኛ ኃላፊነቶችን እንዲይዙ ሲያደርግ ቆይቷል::

20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሲጀመር፣ በአውሮፓና በአሜሪካም በተወሰነ ደረጃ የእግዚአብሔር ቃል በስሕተቶችና በተረቶች የተሞላ የሰው ቃል ነው የሚለው አስተሳሰብ በአንድ ወቅት መጋቢዎችን ለማሠልጠን በተከፈቱት ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ይሰማ ጀመር:: ከእነዚህ ትምህርት ቤቶች የሚወጡ ምሩቃን በብዙ የተደራጁ (እንደ ሉተራን፣ ፕረስቢተሪያን፣ ሜቶዲስት፣ ወዘተ. . . ባሉ) አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ያገለግሉ ጀመር:: በእነርሱ አገልግሎት አማካኝነት በትላልቅ ቤተ እምነቶች ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን ከዘላለማዊ አምላክ ጋር እንደሚገናኙባት ስፍራ ሳትሆን፣ እንደ ማኅበራዊ ስብስብ ይመለከቷት ጀመር:: እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁ የሚያደርጉ መንፈሳዊ ትምህርቶችን ከመስጠት ይልቅ፣ ሥጋዊ አገልግሎቶችን በመስጠቱ ላይ ትኩረት አደረጉ::

በአሜሪካ እና በመጠኑ በአውሮፓም፣ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው የሚል እምነት ያላቸው ክርስቲያኖች ይህንን አስተሳሰብ በከፍተኛ ደረጃ ይቃወማሉ:: ሰዎች ከታሪካዊ ክርስትና እንዳይንሸራተቱ ለማገዝ እንደ ጉባኤ እግዚአብሔር፣ «ኢንዲፐንዴንት ባይብል ቸርችስ» ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ተ

ጀመሩ:: የእነዚህን አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት አገልጋዮች ለማሠልጠን ሦስት ዓይነት ትምህርት ቤቶች ተከፈቱ::

በመጀመሪያ፣ ዓለማዊ ትምህርትን ከመጽሐፍ ቅዱስ ወይም ከክርስቲያናዊ አመለካከት አንጻር ለመስጠት ክርስቲያናዊ ኮሌጆች ተከፈቱ:: እነዚህ ትምህርት ቤቶች ወጣቶች እግዚአብሔርን ከማያውቁና ከማያከብሩ መምህራን ዓለማዊ ትምህርት ከሚቀበሉ ይልቅ፣ ተመሳሳይ ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከት አዳብረው ያቀርባሉ:: ብዙውን ጊዜ እነዚህ ክርስቲያናዊ ኮሌጆች የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ለማሠልጠን የሚያግዙ የአገልግሎት ዘርፎች ይኖሯቸዋል::

<u>ሁለተኛ</u>፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ተከፈቱ:: እንደ ሙዲ የመጽሐፍ ቅዱስ ተቋም ዓይነቶቹ ትምህርት ቤቶች የተከፈቱት ምእመናን እንዴት እግዚአብሔርን ውጤታማ በሆነ መንገድ ሊያገለግሉ እንደሚችሉ ለማስተማር ነበር:: የአነስተኛ አብያተ ክርስቲያናት መጋቢዎች፣ በዓለም ዙሪያ ወንጌልን የሚሰብኩ ሚሲዮናውያን፣ የሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪዎች፣ ወዘተ. . . ለመሆን ይችሉ ዘንድ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ወደ እነዚህ ትምህርት ቤቶች ገቡ:: መጀመሪያው አካባቢ ትምህርት ቤቶቹ ትኩረት የሚያደርጉት ለበሳል ሰዎች የአገልግሎት ክህሎቶችን በማስጨበጥ ላይ ነበር:: በኋላ ግን እነርሱም ለወጣቶች ንድፈ-አሳባዊ እውቀት በማስጨበጡ ላይ ትኩረት ያደርጉ ጀመር:: በኢትዮጵያም ተመሳሳይ ሁኔታ መኖሩን መረዳት ይቻላል:: የኤስ ኣይ ኤም ሚሲዮናውያን ወንጌሉን ወደ ኢትዮጵያ ባመጡ ጊዜ አብያተ ክርስቲያናት ተመሠረቱ:: በዚህ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ለማሠልጠን የሚያስችሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ተከፍተው ነበር:: ከቀድሞዎቹ ተማሪዎች አብዛኞቹ በእድሜ የገፉ በሳል ሰዎች ነበሩ:: በኋላ ግን ክህሎቶችን ከመስጠት ይልቅ በሰፊው እንብበው አጠቃላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ሊያስጨብጡ በሚችሉ ወጣቶች ላይ ትኩረት ይደረግ ጀመር:: ምንም እንኳን አብዛኞቹ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ወንጌላውያን በእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ



ትምህርት ቤቶች ውስጥ ቢማሩም፣ በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ ለማገልገል የሚያስችል ክህሎት የሚያገኙ ምሩቃን ግን ጥቂቶች ናቸው::

ሦስተኛ፣ ለመጋቢዎች፣ በተለይም ለከተማ አብያተ ክርስቲያናት መጋቢዎች የጠለቀ ትምህርት ለመስጠት የሚያስችሉ ሰሚናሪዎች ተከፈቱ:: ምንም እንኳን እነዚህ ሰሚናሪዎች ንድፈ-አሳባዊ እውቀትን ከአገልግሎት ክህሎቶች ጋር ለማዛመድ ጥረት ቢያደርጉም፣ ከፍተኛ ትኩረት የሚደረገው በንድፈ-አሳባዊ እውቀት ላይ ነው:: ጥቂት ሰሚናሪዎች ተማሪዎቻቸው ከመመረቃቸው በፊት ልምድ ባላቸው መጋቢዎች ሥር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲያገለግሉ የግድ ይላሉ::

በቅርብ ጊዜ በአሜሪካ ውስጥ ከተካሄደው ጥናት ለመረዳት እንደ ተቻለው፣ አብዛኞቹ መጋቢዎች የሰሚናሪ ትምህርቱ ለመጋቢነት አገልግሎታቸው እንዳላዘጋጃቸው ተናግረዋል:: ስለ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ወሳኝ የሆኑትን ነገሮች የተማሩት ከሰሚናሪ ወጥተው ወደ አገልግሎቱ ከገቡ በኋላ መሆኑን አስረድተዋል:: ይህ እንግዲህ በአሁኑ ጊዜ የሚሰጠው የመሪነት ሥልጠና ትምህርት አጥጋቢ አለመሆኑን የሚጠቁም ነው::

> 14ኛ ጥያቄ:- በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከሠለጠኑበት መንገድ የምንማራቸውን ነገሮች ዘርዝር::

እግዚአብሔር ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪዎች እንዲሆኑ ለማዘጋጀት ሲጠቀምባቸው የሚችላቸው አያሌ መሣሪያዎች አሉ:: እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች፣ ኮሌጆችና ሰሚናሪዎች ያሉ መደበኛ ትምህርት ቤቶች የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው:: ነገር ግን እንደ ት.መ.ማ. የአገልግሎት ሥልጠናዎችን የሚሰጡትን መሣሪያዎችም መናቅ የለብንም:: ከሁሉም በላይ፣ ወደ ኋላ መለስ ብለን እግዚአብሔር በዓመታት ውስጥ እንዴት የመሪነት ሥልጠና ሲሰጥ እንደ ነበረ መመልከት አለብን:: ንድፈ-አሳባዊ እውቀት ጠቃሚ ነው:: ነገር ግን በአገልግሎት ውስጥ የእግዚአብሔር ትልቁ ትኩረት መንፈሳዊ ባሕርያትንና የአገልግሎት ክህሎቶችን መፍጠር ነው:: እርሱ

አገልጋዮችን የሚያዘጋጅበት ትልቁ መንገድ መንፈሳዊ አገልግሎትን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በምሳሌነት የሚያሳዩ አገልጋዮች አዳዲሶቹን እንዲያሠለጥኑ ማድረግ ነው። ሰዎች የአገልግሎት ኃላፊነት የሚሰጣቸው የመጽሐፍ ቅዱሳዊ እገልጋይ መሪነትን ባሕርይና ሰዎች በእምነታቸው በሳል እንዲሆኑ የሚያግዙትን ክህሎቶችካሳዩ በኋላ ነው። ምናልባት ዛሬ ከመንፈስ ቅዱስ አሳብ ጋር እየተስማማን መሆናችንን ለማረጋገጥ የሥልጠና ልምምዶቻችንን መመርመር ይኖርብን ይሆናል።

## ሁለተኛ ቀን

## ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ብስለት እንድታድግ የሚያግዙ አስፈላጊ አገልግሎቶች ዝርዝር

> *15ኛ ጥያቄ፡- በትምህርት ዘጠኝ ስለ በሳል ቤተ ክርስቲያን የተሰጠውን ትምህርት ከልስ። ሀ) ቤተ ክርስቲያን በሚዛናዊ መንገድ በሳል እንድትሆን ትኩረት ሊደረግ የሚገባቸው ዐበይት አቅጣጫዎች ምን ምንድን ናቸው? ለ) ቤተ ክርስቲያን በእያንዳንዱ አካባቢ እንድታድግ የሚያደርጉትን ነገሮች ዘርዝር። ሐ) እያንዳንዱ የአገልግሎት ክፍል እንዲያድግ ኃላፊነት ያለባቸው መሪዎች የትኞቹ ናቸው?*

አያሌ አብያተ ክርስቲያናት፣ «የሽማግሌ ሥራ ምንድን ነው? የመጋቢ፣ የወንጌላዊ ወይም የዲያቆን የሥራ ድርሻ ምንድን ነው? እነዚህ መሪዎች እርስ በርሳቸው የሚዛመዱት እንዴት ነው? ሽማግሌዎች ልክ እንደ ማንኛውም ድርጅት ሥራ አስፈጻሚ ቦርድ ቤተ ክርስቲያንን የሚያስተዳድሩ፣ ምን መደረግ እንዳለበት የሚወስኑና ውሳኔያቸውን ለምእመናን የሚያሳውቁ ናቸው ወይስ ቤተ ክርስቲያንን በእረኝነት ማገልገል ያለባቸው ናቸው? መጋቢው በቀዳሚነት ቅጥር ሠራተኛ ነው ወይስ ከሽማግሌዎች አንዱ ነው?» የሚሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ያነሣሉ። እነዚህ ጥያቄዎች እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሖዎችን በማጤንና ቤተ ክርስቲያን በብስለት እንድታድግ የሚያግዙትን መንገዶች በማጤን በጥንቃቄ ልታጠና የሚገቧት ናቸው።



ይሁንና፣ «የትኛው መሪ ምን ማድረግ አለበት?» በሚለው ጥያቄ ከመጀመር ይልቅ፣ «ምእመናን በመንፈሳዊ ብስለት እንዲያድጉ፣ ወንጌሉ ሳልደረሳቸው ወንጌሉን እንዲያዳርሱ፣ በማኅበረሰባቸው ውስጥ ፍቅርን እንዲያሳዩና ታላቁ አምላካችንን በእውነትና በመንፈስ እንዲያመልኩ ለማገዝ በቤተ ክርስቲያናችን መከናወን ያለባቸው ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?» በሚለው ጥያቄ መጀመሩ የተሻለ ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለምእመናን ተገቢው እንክብካቤ እየተደረገላቸው መሆኑን፣ እንደ ንጽሕት ሙሽራ ሙሽራውን ኢየሱስን እየተጠባበቁ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅር ለሁሉም ምእመናን በቂ የእረኝነት አገልግሎት ለመስጠት የማያስችል ከሆነ፣ «መጋቢው ምን ይሠራል? የእርሱ ሥልጣን ከእኛ በላይ ነው ወይስ በታች?» በሚሉ ጥያቄዎች ላይ ትኩረት ማድረጉ ዋጋ የለውም።

ለመሆኑ ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ብስለት እንድታድግ የሚያግዙ መከናወን ያለባቸው ዐበይት አገልግሎቶች ምን ምንድን ናቸው? ከዚህ በታች ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ብስለት እንድታድግ ያስችላሉ ብዬ ያሰብኳቸውን ነገሮች በአስተዋጽኦ መልክ አቅርቤአለሁ። በዚህ ዝርዝር ውስጥ ልንጨምር የምንችላቸው ሌሎችም ብዙ ነገሮች አሉ። የቤተ ክርስቲያን መሪ ዎች ቤተ ክርስቲያን ወደ መንፈሳዊ ብስለት እንድታድግና በሚዛናዊ ሕይወት እግዚአብሔርን እንድታከብር የሚያስችሉትን ነገሮች መርምረው ማወቅ አለባቸው። ይህም በሳል ቤተ ክርስቲያን ለመገንባት እግዚአብሔር የሚፈልገውን ነገር እንዲያውቁ ይ ረዳቸዋል። ከዚያም እነዚህን ኃላፊነቶች ተግባራዊ ለማድረግ የተ ለያዩ መንፈሳዊ ስጦታዎች ያሏቸውን የተለያዩ ሰዎች ሊመድቡ ይችላሉ። በተጨማሪም መሪዎች ቤተ ክርስቲያናቸው እግዚአብሔ ር በሚፈልገው መንገድ በሚዛናዊ ሁኔታ እያደገች መሆኗን መርም ረው መረዳት አለባቸው።

1. ከአምልኮ ጋር የሚዛመዱ አገልግሎቶች፡-

ሀ. ሁሉም አማኞች እግዚአብሔርን በእውነትና በመንፈስ ያመልኩ ዘንድ የቤተ ክርስቲያንን አምልኮ መከታተል።

ለ. አምልኮን የሚመሩ ሰዎችን መርጦ ማሠልጠን:: ይህም የአምልኮ መሪዎችን፣ የመዘምራን አባላትንና የሙዚቃ ተጫዋቾችን መርጦ ማሠልጠንን ይጨምራል:: ይህ በተጨማሪም እንደ ድምጽ ማጉያዎች፣ የመዘምራን ልብሶች፣ ወዘተ. . . ያሉት የአምልኮ መሣሪያዎች በሚፈለጉበት ጊዜ መገኘታቸውን ማረጋገጥን ያካትታል::

ሐ. የመዘምራን አባላትና የአምልኮ መሪዎች መንፈሳዊ መቀታቸውን (ግለታቸውን) እንዳያጡ፣ ብቃት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡና የሁሉንም ምእመናን የአምልኮ ፍላጎቶች በሚያረካ መንገድ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል ተገቢውን ክትትል ማድረግ::

16ኛ ጥያቄ:- ሀ) በአሁኑ ሰዓት ይህንን አገልግሎት የሚከታተል መሪ ማን ነው? ለ) አምልኮ በበለጠ ውጤታማ እንዲሆን ኃላፊነት የተሰጠው መሪ (ወይም መሪዎች) እነማን ናቸው?

**2. ከወንጌል ስርጭት ጋር የተያያዙ አገልግሎቶች:-**

ሀ. የወንጌል ስርጭት በቤተ ክርስቲያን:- ከክርስቶስ ጋር የግል ሕይወት ከመመሥረት ይልቅ ለደኅንነት በወላጆቻቸው እምነት ለሚተማመኑ ልጆች ወንጌልን መመስከር::

ለ. የወንጌል ስርጭት በማኅበረሰብ:-

1) በማኅበረሰቡ ውስጥ ላሉት ልዩ ልዩ የዕድሜ ክልሎች ወንጌልን በመመስከር ወደ ክርስቶስ መመለስ:: ከሽማግሌዎች ይልቅ ለወንጌሉ ልባቸውን ለሚከፍቱት ወጣቶች ልዩ ትኩረት መስጠት ያሻል:: ይሁን እንጂ፣ በሁሉም የዕድሜ ክልል ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች ወንጌሉን ማካፈል አስፈላጊ ነው::

2) በማኅበረሰቡ ውስጥ ላሉት ለሁሉም ጎሳዎች ወንጌሉን መመስከር:: ኢየሱስ ወንጌሉን ለአሕዛብ ሁሉ ስበኩ እንዳለ (ሉቃስ 24:47)፣ እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን ባህልን ከግምት ውስጥ ባስገባ መንገድ ለሁሉም ጎሳዎች ወንጌልን መመስከር ይኖርባታል:: ምእመናን ለራሳቸው ባህል ሰዎች ብቻ ወንጌሉን ለመመስከር መፈተን የለባቸውም::



3) በማኅበረሰቡ ውስጥ ላሉት የሁሉም ሃይማኖት ቡድኖች (ክርስቲያናዊም ሆኑ ክርስቲያናዊ ላልሆኑ ሃይማኖቶች) ወንጌሉን ማካፈል:: ብዙውን ጊዜ አንዳንድ ሃይማኖቶች ለወንጌሉ ክፍት ሲሆኑ፣ ሌሎች ግን ያን ያህል ወንጌሉን የመቀበል ፍላጎት የላቸውም:: ምእመናን ወንጌሉን በቀላሉ በሚቀበሉት ላይ ብቻ ትኩረት ከማድረግ ይልቅ፣ ለሁሉም ቡድኖች እንዴት አድርገው እንደሚያካፍሉ መማር አለባቸው::

4) ወንጌሉን በማኅበረሰቡ ውስጥ ላሉት ሁሉም የኢኮኖሚ ቡድኖች ማካፈል:: የተማሩና ያልተማሩ፣ የተከበሩና የተናቁ (ሴተኛ አዳሪዎች፣ ሸክላ ሠሪዎች) ሁሉ ወንጌሉን የመስማትና የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን ዕድል ሊሰጣቸው ይገባል::

ሐ. ከቅርብ ማኅበረሰብ ውስጥ ላሉት መመስከር:- ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ ገጠራማ አካባቢዎችና በሌሎችም አገሮች ውስጥ ላሉት ሰዎች ወንጌላውያንን ወይም ሚሲዮናውያንን በመላክ በወንጌል ምስክርነት ትሳተፋለች::

መ. ሥልጠና:-

1) ምእመናን ከላይ ለተጠቀሱት የማኅበረሰብ ክፍሎች ወንጌሉን በብቃት እንዲያካፍሉ ሥልጠና መስጠት::

2) እግዚአብሔር በማኅበረሰባቸው ውስጥና ከዚያም አልፎ የሙሉ ጊዜ ወንጌላውያን እንዲሆኑ ለጠራቸው ሰዎች ሥልጠና መስጠት::

ሠ. ወንጌሉ በማኅበረሰቡ ውስጥ ወዳሉት ሰዎች ሁሉ እንዲዳረስ የቤተ ክርስቲያንን የወንጌል ስርጭት ሥራዎች ማቀናጀት::

17ኛ ጥያቄ:- ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ይህንን አገልግሎት የሚከታተለው ማን ነው? ለ) ይህንን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መከታተል ያለባቸው የትኞቹ መሪዎች/አገልጋዮች መሆን አለባቸው ትላለህ?

**3. ከምእመናን መንፈሳዊ ብስለት ጋር የሚዛመዱ አገልግሎቶች:-**

ሀ. እያንዳንዱ አዲስ አማኝ የደቀ መዝሙርነት ትምህርት ተሰጥቶት ኢየሱስን መከተል ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ

እንዲገነዘብ ይደረጋል:: ጥምቀት በመውሰድም ንቁ የቤተ ክርስቲያን አባል ይሆናል::

ለ. እያንዳንዱ አማኝ፣ በዕድሜ ክልሉ፣ ተገቢውን የደቀ መዝሙርነት ትምህርት ቀጣይነት ባለው መንገድ በማግኘት ወደ መንፈሳዊ ብስለት ያድጋል:: ልጆች፣ ወጣቶች፣ ሴቶችና ወንዶች ሁሉ እንዴት ክርስቶስን መከተል እንዳለባቸው ይማራሉ::

ሐ. ሁሉም አማኞች መንፈሳዊ ስጦታዎቻቸውን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲጠቀሙ በሚያስችል መንገድ ማስተማርና ማሠልጠን::

መ. የእያንዳንዱ አማኝ ፍላጎቶች ይሟሉ ዘንድ ጉብኝት በማድረግ መንፈሳዊ ምክሮችን መስጠት::

ሠ. ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡትን የሐሰት ትምህርቶች ሁሉ መከላከል::

ረ. በመንፈሳዊ እምነታቸው የሚደክሙትን፣ በክርስቶስ ባላቸው ሕይወት አየዛሉ ያሉትን፣ እንዲሁም በችግር ውስጥ ያሉትን ሰዎች መምከር::

ሰ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን የግንኙነት ችግሮች ማስተካከል::

ሸ. እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ ለመኖር የማይፈልጉትን ሰዎች መቅጣት::

ቀ. ምእመናን እርስ በርሳቸው በጸሎት እንዲደጋገፉና በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲሳተፉ ማድረግ::

ሸ. መሪዎችን ለተለያዩ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ማዘጋጀት::

> 18ኛ ጥያቄ:- ሀ) ከእነዚህ አገልግሎቶች በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ እየተከናወኑ ያሉት የትኞቹ ናቸው? ለ) ለእነዚህ አገልግሎቶች ኃላፊነት ያሰባቸው የትኞቹ አገልጋዮች ናቸው? ሐ) እነዚህን የተለያዩ አገልግሎቶች መከታተል ያሰባቸው የትኞቹ መሪዎች መሆን አለባቸው ትላለህ?



4. ክርስቲያናዊ ፍቅር የማሳየት አገልግሎት:-

ሀ. የኢኮኖሚ (የምጣኔ ሀብት) እና የጤና ችግር ላለባቸው አማኞች መጸለይና ድጋፍ ማድረግ::

ለ. በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ሰዎች፣ በተለይም ድሆችን መርዳት::

ሐ. የቤተ ክርስቲያኒቱ አቅም በፈቀደ መጠን፣ የልማት ፕሮግራሞችን በመጠቀም ማኅበረሰቡ ከምጣኔ ሀብታዊ ችግሮች እንዲላቀቅ ማገዝ:: (ማስታወሻ:- በዚህ የጥናት መምሪያና ማብራሪያ መጽሐፍ ደራሲ አመለካከት፣ ልማት እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ለማኅበረሰቡ ፍቅር እንድታሳይ የተሰጣት መሣሪያ ነው:: ይህ አማኞች የራሳቸውን ፍላጎት ለማሟላት ወይም ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ገንዘብ ለማግኘት የሚጠቀሙበት መንገድ ሊሆን አይገባም:: ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ትሰጣለች እንጂ፣ ከማኅበረሰብ አገልግሎት ወይም ገንዘብ መቀበል የለባትም::)

> 19ኛ ጥያቄ:- ሀ) ቤተ ክርስቲያናችሁ በማኅበረሰቡ ውስጥ ላሉት አማኞችና አማኞች ያልሆኑ ሰዎች ፍቅርን እያሳየች ያለችው እንዴት ነው? ለ) ለዚህ ተግባር ኃላፊነት የተሰጠው የቤተ ክርስቲያን መሪ የትኛው ነው?

5. የቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች አስተዳደር:-

ሀ. ለቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ራእይና ዕቅዶች ማዘጋጀት::

ለ. አገልግሎቶችን ማስተባበር::

ሐ. የመንግሥትና የማኅበረሰብ ግንኙነቶችን ማጠናከር::

መ. የአገልግሎት ወጪዎችና ደመወዝ የመሳሰሉትን ክፍያዎች መፈጸም::

ሠ. የአዳዲስ ሕንጻዎችን ግንባታዎች መከታተል::

ረ. አዳራሹንና የተለያዩ ክፍሎችን ለአምልኮና ለትምህርት ማጽዳትና ዝግጁ ማድረግ::